ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን የራሱ የሆነውን አሰብን ከነጣቂዎች ለማዳን ቆርጦ እንደተነሳና የአሰብ ጥያቄ የአፋሮች ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደሆነ አቶ ማህሙድ በተለያዩ ጊዜአት አስገንዝበዋል። አቶ ማህሙድ በመቀጠል "አፋር ኢትዮጵያዊ ነው። አሰብም የአፋር ነው" በማለት የኢትዮጵያ መንግሥት በቅኝ ግዛት ውሉች ተመስርቶ አሰብን እስከ ወዲያኛው አሳልፎ በመስጠቱ መብረጃ የሌለው ደም መፋሰስ እንዲከተል ከማድረጉ በፊት በኢትዮጵያዊነታችን የምናምን ዜጎችና ሰላም የሚሹ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ድምጻቸውን ሊያሰሙ የሚገባ የመጨረሻው ሰዓት ቢኖር አሁን መሆኑን አቶ ማህሙድ ጋአስም አሳስበዋል። አቶ ማህሙድ በመቀጠል ዘሔግ ተሰይሞ የኤርትራና የኢትዮጵያን የወሰን ውዝግብ የሚዳኘው ኮሚሽን የአፋርን ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምና መብት ከግምት ሳያስገባ የሚያስተላልፈው ውሳኔ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት ሊያሰፍን እንደማይቻል ቀደም ሲል ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊና ለጸጥታው ምክር ቤትና ለሌሎችም ዓለም አቀፍ ተቋማት መልእክት ማስተላለፋቸውን ገልጸዋል[162]።

## 9.7. የኦሮም ብሔራዊ ኮንግሬስ ፓርቲ

የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ ሊቀ መንበር ተባባሪ ፕሮፌሰር መራራ ጉዲና የፓርቲአቸውን አቋም ሲገልጹ "የቅኝ ግዛት ውሎችን በተመለከተ የኢሕአዴግ መንግሥት የሚያቀርባቸው ክርክሮች አስደናቂና የሚያስገርሙ ናቸው። የፈረንጅ ጠበቃ ገዝቶም አልገዙም [ክርክሮቹ] የኤርትራ መሪዎች ቢያቀርቡአቸው ያምርባቸዋል" በማለት በተለመደው አዝናኝ አገላለጻቸው አስረድተዋል[163]።

[162] ክብሪት የካቲት 7 ቀን 1994

[163] ጉትሳት የካቲት 27 ቀን 1994 ዓ.ም ገፅ 3



## 9.8. የቀይ ባህር አፋር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት

የቀይ ባህር አፋር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ያሲን ሞሃመድ አብደላ የአሰብ ወደብ፣ የዳህላቅ ደሴቶችና ምጽዋን ጨምሮ በኤርትራ መያዛቸውን በመቃወም እነዚህ ግዛቶች በሙሉ የቀይ ባህር አፋሮች ንብረት መሆናቸውን የአውሮፓና የአሜሪካ ባለስልጣናትን አስገንዝቡ።

## 9.9. የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ

የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ ሊቀ መንበር ኢትዮጵያ የባህር በር እንደሚያስፈልጋት ከገለጹ በኋላ የአፋር ሕዝብና የመልክአ ምድር አቀማመጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆነ አሰብ የኢትዮጵያ ነውና ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነትዋን ማረጋገጥ እንደሚገባት ገልጸው ወደፊት በሰላማዊ መንገድ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ፓርቲአቸው እንደሚሠራ ቃል ገቡ።

## 9.10. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር

አቶ ግርማይ ሐደራ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ደሞክራሲያዊ ግንባር ሊቀ መንበር በ1985 ዓ.ም. በኤርትራ በተካሄደው ሬፈረንደም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይጠየቅ የኤርትራ ጉዳይ ሲወሰን ኢትዮጵያ በባህር በር ባለቤትነቷ እንዲያበቃለት መደረጉ ሕዝብን ያሳዘነና አንገት ያስደፋ ጉዳይ እንደነበረ እያስታወሱ ፓርቲአቸው አሰብን ለማስመለስ የሚታገልበት ስልት መንደፉን ገልጸዋል[164]።

## 9.11. የአፋር አብዮታዊ ዴምክራቲክ ግንባር (አርዱፍ)

የአፋር አብዮታዊ ዴሞክራቲክ የተባበሩት ግንባር (አርዱፍ) ሊቀ መንበር አቶ ሞሃመድ ገአዝ የኢትዮጵያና የኤርትራ የወሰን

[164] ዝኒ ከማሁ

ውዝግብ ጉዳይ የያዘው ዘሔግ የሚገኘው የድንበር ኮሚሽን የአሰብን የኢትዮጳያና የአፋር የተፈጥሮ የባህር በርነት ከግምት ውስጥ ካላስገባ ዳግመኛ ስህተት መፈጸሙን መረዳት እንዳለበት አስገንዝበዋል። [የመጀመርያው ስህተት የቅኝ ግዛት ውሎች ለውሳኔው መሠረት ማድረጉ ነው]። በስደት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ ድርጅቶችንና ተቆርቋሪ ዜጐችን አውሮፖና አሜሪካ በመመላለስ ሲቀሰቅሱ የነበሩት አቶ ሞሃመድ ገአዝ የድንበር ኮሚሽኑ አሰብን ወደ ወራሪዋ ኤርትራ ካካለለ የአፋር ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጳያውያን ወንድሞቹ ጋር በመሆን የተነጠቀው ወደቡን ለማስመለስ መስዋዕትነት ለመክፈል እንደሚገደድ ከአስገነዘቡ በኋላ ይህ ከመሆኑ በፊት ግን የድምበር ኮሚሽኑ አሰብን አስመልክቶ የማያሻማ ውሳኔ መስጠት እንዳለበት አሳስበው ነበር። ድርጅታቸው አርዱፍም የአሰብን ጥያቄ ፍትሐዊነት ባለው መልኩ ካልተመለሰ ትግሉን እንደሚቀጥል ለመንግሥታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ በጻፉት ደብዳቤ ማስታወቃቸውን አቶ ሞሃመድ ገአዝ ገልጸዋል[165]።

## 9.12. የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅት

አቶ መለስና መንግሥታቸው የአሰብ ጉዳይ ያለቀለት ስለሆነ አትከራከሩ ቢሉንም ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት ሲመሠረት ጥያቄው መነሳቱ የማይቀር መሆኑ የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅት ዋና ጸሐፊ ገለጹ ።ዋና ጸሐፊው አቶ ቦጋለ አሰፋ ከአዲስ አድማስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ የአሰብ ኤርትራዊነት ተቀበሉ ማለት መራራ ኮሶ እንደመጋት ነው ሲሉ ገልጸውታል። አቶ መለስ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውን ያልወገኑ መሆናቸውን የገለጹት ዋና ጸሐፊው አቶ መለስ የአንድን አገር አካል ቆርሶ ለሌላ የመስጠት መብት እንደሌላቸው አቶ ቦጋለ አስረድተዋል[166]።

---

[165] ጦቢያ የካቲት 14ቀን 1994 ዓ.ም

[166] አዲስ አድማስ ሚያዝያ 12 ቀን 1994



## 9.13. የሲቪክና፣ የኃይማኖት ተቋማት በውጭ አገር ያደረጉአቸው ትግሎች

### 9.13.1 በተለያዩ አካላት የተደረጉ ትግሎች

በውጭ አገር በተለይም በአሜሪካ የሚገኙ ልዩ ልዩ ኢትዮጵያውያን፤ የሲቪክና ሕዝባዊ ድርጅቶችና ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፤ ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አቢያተ ክርስቲያናት ካህናት፣ ሞአ አንበሳ የኢትዮጵያ የዘውድ ምክር ቤት አባላት፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ የተግባር ሊግ ወኪሎች፣ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት ተወካዮች፤ የትግራዊያን የዓለም አቀፍ የአንድነት ለፍትሕና ለዴሞክራሲ አባላት፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ሕብረት ፓርቲ ተወካዮች፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ አባላት እንዲሁም ብዙ ኢትዮጵያውያን የተገኙበት በተባበሩት መንግሥታት ጽህፈት ቤት ደጃፍ እ.አ.አ የካቲት 8ቀን 1994 ዓ.ም. ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጐ ነበር። በዚህ ሰልፍ ተሰላፊዎቹ "የኢትዮጵያ የባህር በር አይዘጋም" "አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊት ግዛት ነች" "የአፋር ሕዝብ አንድነት ይከበር" "የአፋር ሕዝብ የራሱን ዕደል በራሱ የመወሰን መብቱ መከበር አለበት" የሚሉ በእንግሊዝኛ የተፃፉ መፈክሮችን ይዘው ነበር። በዚሁ ሰልፍ ኢዴፖ አሰባሰቦት የነበረ 158 ሺህ ኢትዮጵያውያን የፈረሙት የኢትዮጵያ በባህር በር እንዳይዘጋ የተማጽኖ ዳብዳቤ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለሚስተር ከፊ አናን ተሰጠ፡

ከሰልፉ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ በቡድን በቡድን በመከፋፈል የጸጥታው ምክር ቤት አባላት ተወካዮች ቢሮ ድረስ በመሄድ የኢትዮጵያ የባህር በር በተመለከተ ታሪክን፤ ሕግንና የአካባቢውን ሰላም በዋቢነት በመጥቀስ ሰፊ ማብራሪያ ሰጡ። ይህ ጸሐፊ የአሜሪካና የፈረንሳይ ተወካዮችን ያነጋገረውን ቡድን በመምራት

ለብዙ ዘመናት ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሲኳትኑ የኖሩት አቶ ቾሩ ተሬፈንና ሌሎችንም ጨምሮ አሜሪካኖች ቢሮ በማምራት ከአሜሪካኑ ባልሥልጣን ጋር በተደረገው ውይይት የአሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍ ኢፍትሐዊነት፤ ሊያስከትለው የሚችል መዘዝ እንዲሁም ለአሜሪካ መርከቦች ሰላማዊ እንቅስቃሴ ከአካባቢው ካሉ ወደቦች በሙሉ በኢትዮጵያ እጅ ያለች አሰብ ብቻ መሆንዋን አስረዳን። የአካባቢው ወደቦች በሙሉ ለሽብርተኞች የተጋለጡ ሲሆኑ ይህም ለአሜሪካ መርከቦች አደገኛ መሆኑን ገልፀን ከጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ዩኤስኤስ ኮል (USS Cole) የተባለው የአሜሪካን የጦር መርከብ በየመን ወደብ በኤደን አሸባሪዎች አፈንድተውት 17 አሜሪካኖች ሞተው 39 ቆስለው እንደነበረ አስገንዝበን፡ ስለዚህ በአካባቢው ሳአሜሪካኖች አስተማማኝ ወደብ አሰብ በኢትዮጵያ እጅ ስትገባ መሆኑን ለማሳመን ጥረት አደረግን። የአሜሪካኑ ተወካይ በተመሰጠ ካዳመጠን በኋላ ይህንኑ በጽሁፍ እንድናቀርብለት በጠየቅን ጊዜ ጥያቄአችንን አስመልክቶ ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ የነበረ ጽሁፍ በእጃችን ስለነበር በሰጠነው ጊዜ የመገረም ስሜት በፊቱ ይታይ ነበር።

ያነጋገርናቸው የሌሎቹ አገራት የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት አባላት የአሜሪካኑም ጨምሮ የሰጡን መልሶች የሁሉም ተመሳሳይ ነበሩ ማለት ይቻላል። የተባበሩት መንግሥታት የነፃና ሉዐላዊ አገራት ተወካዮች ማለት የአምባገነኖችም ይሁን የዴሞክራሲያዊ መንግሥታት ስብስብ እንደመሆኑ መጠን ጉዳዩ በኢትዮጵያ መንግሥት ለድርጅቱ እስካልቀረበ ድረስ ጥያቄዎቻችን ክብደት ያላቸው መሆናቸው ቢቀበሉም ለጥያቄዎቻችን አዎንታዊ ምላሽ ሊሰጡን እንደማይችሉ ገለጹልን

## 9.13.2. የቀይ ባህር ድንበር አስጠባቂ ኮሚቴ

ይህ ኮሚቴ በአቶ በላይ አባይ አስተባባሪነት እ.አ.አ በ1993 ዓ.ም በዋሺንግተን ዲ.ሲ. ተቋቋመ። የዚህ ኮሚቴ ዋና ዓላማውና ተግባሩ የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን አስመልክቶ ለዓለም ሕብረተሰብና ለአሜሪካ ኮንግሬስ አባላት ግንዛቤ ለማስጨበጥ፤ በተለይም በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዲያስከብሩ



በኢሕአዴግና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሬፑብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች ላይ ግፊት ለማድረግ ነበር። በዚሁ መሠረት ኮሚቴው "ጣልያን እራሱ ያፈረሳቸው ውሎች በሥልጣን ያለው መንግሥት እንደ ሕጋዊ ማስረጃ መጥቀሱን ትቶ በታሪክና በሕግ የአገሪቱ ንብረት የሆነውን የአሰብ ራስ ገዝ የቀይ ባህራችን ከሻቢያ ጋር በሚያደርገው ድርድር ወደ ኢትዮጵያ ማስመለስ እንደሚኖርበት በአጽንኦት በማሳሰብ" ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለምክር ቤቶቹ ደብዳቤ ጽፎ ነበር። ኮሚቴው በፋክስ ከዋሺንግተን ለተላከው ደብዳቤ ከጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች መልስ አለማግኘቱን ገልጾ መብቱን የተገፈፈ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነገ እንደሚጠይቃቸው አሳሰበ። በመቀጠልም ኢትዮጵያ በሕግና በታሪክ የራስዋ የሆነውን ወደብና አውራጃ እንደቀላል እቃ ለኤርትራ ሲሰጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም አለምንም ድርድርና ሕዝባዊ ውይይት ለሌላ ሰጥቶ ኢትዮጵያ ለጥቃት ስትጋለጥ ኮሚቴው ዝም እንደማይል አሳሰበ። የተወካዮች ምክር ቤትም በታሪክና በሕግ የአገሪቱ የሆነውን ራስ-ገዝ አስተዳደር ቀርቶ የሕዝብ ንብረት የሆነውን ሁሉ የማስጠበቅ ግዴታ እንዳለበት ኮሚቴው ጠቅሶ ከዚህ የበለጠ ኃላፊነት ሊኖር ስለማይችል ከሻቢያ ጋር በሚደረገው ድርድር የቀይ ባህራችንን ለማስመለስ የምክር ቤቱ አባላትና ምክር ቤቱ ይህንን ታሪካዊና ሕጋዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ኮሚቴው ጥሪውን አቅርቦአል[167]።

## 9.13.3. የኢትዮጵያውንና የአሜሪካውያን መድረክ (Ethiopian American Forum)

የኢትዮጵያንና የአሜሪካውያን መድረክ (Ethiopian American Forum) በአሜሪካ የተቋቋመ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና አሜሪካውያንን በአባልነት ያቀፍ ድርጅት ሲሆን እነዚህ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የአሜሪካን ዜጐች በአሜሪካ ለሚደረጉ የፌዴራልም ሆነ የክልል ምርጫዎች ገንዘብ

[167] "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀይ ባህር ድምበራችንን ለማስመለስ ግዴታቸውን እንዲወጣ ተጠየቀ" ሪፖርተር ህዳር 28 ቀን 1993 ዓ.ም

ስለሚያዋጡና ድምጽ ስለሚሰጡ በአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣናት ተሰሚነት ያላቸው ናቸው።

ይህም ድርጅት የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ያሳሰበው መሆኑን የዚህ ቡድን አባል ዶ/ር አርአያ ወልደጊዮርጊስ በጻፉት መግለጫ ገልጸዋል። በጽሁፋቸው ኢሕአዴግ ስህተቱን አምኖ አሰብን እንዲይዝ ያሳስባሉ። ይህንን ለማድረግ ኢሕአዴግ በአሁኑ ጊዜ እድል እንዳለውም ያመለክታሉ። አሰብን ለማስመለስ ኢሕአዴግ በሌላ መንግሥት እስኪተካ መጠበቅ ሳይኖርብን አሁኑኑ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ እንዲያስመልስ ኢሕአዴግን መማጠን አለብን ይላሉ፡ ኢትዮጵያ አሸባሪነትን ለመዋጋት እጅግ በጣም አስፈላጊአቸው ስለሆነች ምዕራባውያን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል ድጋፋቸውን እንደሚለግሱ ዶ/ር አርአያ ያምናሉ። ስለሆነም ኢሕአዴግ ኤርትራን ከኢሣያስ አፈወርቂ የጭቆና ቀምበር ነፃ አውጥቶ መሳው የአፋር ሕዝብ ውሳኔ እንዲያደርግ ቢፈቀድለት የአፋር ሕዝብ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር እንደሚቀላቀል አይጠራጠሩም። በመሆኑም ዶ/ር አርአያ ኢትዮጵያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አሜሪካኖች ኢሕአዴግ ከላይ የተጠቀሱትን እርምጃዎች እንዲወስድ እንዲማጠኑ ያሳስባሉ።[168]

## 9.13.4. የዛላአንበሳና የኢሮብ አካባቢ ጊዜያዊ ኮሚቴ

ይህ ኮሚቴ በበኩሉ ባወጣው መግለጫ የአልጀርስ ስምምነት የኤርትራን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ ያለመ ነው ብሎታል። የኢሮብ፣ የጾረና፣የኩናማ፣ የዛላአምበሳን እና የአፋርን ሕዝብ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የባህር በር ባለቤትነት መብት ያላወቀ ውሳኔ በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል ያለው ችግር በዘላቂነት እንደማይፈታ በመግለጫቸው አስገንዝበዋል[169]።

[168] See www.ethiopianamerikcanforum.com, Accessed on 29 April 2011

[169] ዝኒ ከማሁ




## 9.13.5. የትግራውያን ዓለም አቀፍ ትብብር ለፍትሕና ለዴሞክራሲ

የትግራውያን ዓለም አቀፍ ትብብር ለፍትሕና ለዴሞክራሲ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በጻፈው ደብደቤ የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በተለይም የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት የሚቃወም መሆኑን ገልጾአል[169]።

በአሁኑ ወቅት እነዚህ ድርጅቶችና ተቋማት የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እውን ለማድርግ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የቀዘቀዘ ነው። ሆኖም ግን ይህ ጉዳይ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሥነ ልቦና ተቀርጾ የሚገኝ ነገር ነው። ምናልባትም ይህ ችግር በአንድ ጀምበር የሚፈታ ሆኖ ኢትዮጵያ በቅርብ ቀን የባህር በር ባለቤት ላትሆን ትችላለች። ሆኖም ግን ጊዜ የሚያመጣው አይታወቅም ዋናው ነገር ይህንን የባህር በር ባለቤትነት ጉዳይ ጊዜ እስኪፈታው ኢትዮጵያውያን ከልባቸው እንዳይፍቁትና የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ያስፈልጋል። የዚህም ኣላፊነት የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነው።

[169] ሪፖርተር ዝኒ ከማሁ 166.



HAP15
592
ASEB
13N
43E

## ምዕራፍ 10

# 10. አሰብ - የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር

## 10.1 አሰብና ታሪኳ

በአንድ ጉዳይ በፍሬ ነገሩ ለመስማማት በቃላት ትርጉም የጋራ ግንዛቤ መጨበጥ የግድ ይላል፤ ስለሆነም "አሰብ" ስንል ምንን እንደሚያካትት፥ "የባህር በር መብት" ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ መግለፅ ያስፈልጋል። በተለምዶ አነጋገር "አሰብ" ሲባል ብዙዎች ቃሉ ወደቡን ብቻ የሚሸፍን አድርገው ይወስዱታል። በዚህ ፅሁፍ "አሰብ" ስንል ግን ከወደቡ ዓለም አቀፍ የባህር በር ሕግ እንደሚደነግገው 12 ኖቲካል ማይልስ ወደ ባህር ዘልቆ ገብቶ ላይ ታቹን የባህርና የመሬት አካባቢን (Red Sea littoral) የሚሸፍን ሲሆን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት "የአሰብ አውራጃ"፤ በደርግ ዘመን ደግሞ "የአሰብ ራስ ገዝ" ይባል የነበረውን ውሀውና መሬቱን ደሴቶቹንም ያጠቃልላል።

እንዲሁም በተለያዩ ፅሁፎች፤ በተባበሩት መንግስታ ሰነዶችም ጭምር "የኢትዮጵያ ወደ ባህር የመዝለቅ መብት" (access to the sea) የሚል ሐረግ ይነበባል። ይህም ማለት ኢትዮጵያ በራስዋ ወደብ በአሰብ አድርጋ ወደ ባህር መዝለቅ ማለት እንደሆነ አንባብያን ሊገነዘቡት ይገባል። ወደብ አልባ አገር ባለወደቡ አገር የሚጠይቀውን ክፍያ እስከ ፈፀመና ሌሎችም ባለወደቡ አገር የሚያስቀምጣቸውን ሕጋዊ ግዴታዎችን እስካሟላ ድረስ በሌላው አገር ወደብ የመጠቀም መብት በተለያዩ ... አቀፍ ሕጎች የተደነገገ ስለሆነ ኢትዮጵያም ይህ መብት ከመላው ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ጋር የምትጋራው በመሆኑ በጅቡቲ አድርጋ ወደ ባህር ለመዝለቅ የተለየ ፈቃድ አያስፈልጋትም[171]።

[171] See Vienna Convention on the Law of the Sea, Article 25, 1982



ስዊዝ ካናል በወደብነት ተዘጋጅቶ ሥራ በሚጀምርበት ጊዜ የጣልያን መርከቦች የሚያርፉበት አንድ የንግድ ማዕከል፤የሸቀጣሸቀጥ፤ የነዳጅና የከሰል መጋዘን፤ ወደ ሩቅ ምስራቅ ለሚመላለሱ መርከቦችም ማረፊያ የሚያገለግል ወደብ በቀይ ባህር ማግኘት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ተረድቶ አመቺ ወደብ ፍለጋ ቀይ ባህርን ሲያስስ የነበረው የካቶሊክ ቄስ ጁሴፔ ሳፔቶ ከጓደኛው ከአክተን ጋር በ1869 አሰብ ደረሱ[172]። ቦታው ለፈለጉት ግልጋሎት ተስማሚ ሆኖ ስለአገኙት ከመሬቱ ባለቤቶች ከወንድማማቾቹ ከሱልጣን ኢብራሂም በን አህመድ እና ከሱልጣን ሀሰን በን አህመድ በአሰብ የሚገኝ አንድ ትንሽ ቦታ በስድስት ሺህ ማርያ ቴሬዛ ብር ለመግዛት ተስማሙ። ግዥው የተከናወነው በሩባቲኖ ኩባንያ ስም ነበር[173]።

ከአሰብ ፊት ለፊት የሚገኙ ደሴቶችንም ከአሰብ ጋር መቀላቀል ቁሱ አስፈላጊ ሆኖ ስለአገኙት ከደሴቶቹ ባለቤት ከሱልጣን አብደላ ሻሺም ጋር ተስማምተው ሦስቱም ሱልጣኖች እኩል የሚካፈሉት 8100 ማርያ ቴሬዛ ብር ሲቀበሉ የሩባቲኖ ኩባንያ ወዲያውኑ ከራስ ሉማህ አላላህ ተብሎ ከሚጠራው የባህር ዳርቻ እስከ ጋንጋ ተራራ ድረስ ያለውን መሬትና ደሴቶቹን ተረከበ። የጣልያን ባንዲራም ተሰቅሎ 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ። የቀረው ነገር ከአሰብ ፊት ለፊት ይገኙ የነበሩት ሌሎችም ዋና ዋናዎቹ ደሴቶች ጣልያኖች መያዝ ስለፈለጉ የደሴቶቹ ባለቤት ብርሃን ከሚባለው የራሄይታ ሱልጣን ጁሴፔ ሳፔቶ ደሴቶቹን ገዛ። ሳፔቶ በ1870 ዓ.ም ወደ አገሩ ሲመለስ ጥሩ አቀባበል ቢያገኝም ቅሉ የጣልያን ጋዜጦች፣ መፅሔቶችና የፖለቲካ ሰዎች አሰብ የተቃጠለ አገር ነው፤ ሙቀቱም ኃይለኛ በመሆኑ ሰው ሊኖርበት አይችልም፣ ዕፅዋትም አያበቅልም እያሉ ተዘባበቱበት[174]።

[172] ዶ/ር ተወልደ ትኩዕ ዝኒ ከማሁ 31 ገፅ 195.

[173] ዝኒ ከማሁ

[174] ዝኒ ከማሁ ገፅ 196

አሰብ ለ10 ዓመት በሙሉ ተረስቶ ከቆየ በኋላ የኢጣልያ መንግስት ከሩባቲኖ ኩባንያ ተረክቦት በአፍሪካ ቀንድ የመጀመሪያዋ የጣልያን ቅኝ ግዛት ሆነች፡፡

አሰብ የሩባቲኖ ኩባንያ ሲገዛው ከዚያም በኋላ ለብዙ ጊዜ ትንሽ መንደር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ጣሊያኖች ሲገዙት በቀይ ባህር ለሚተላለፉ የጣልያን መርከቦች ከሰል ለማቅረብ አስበውት ስለነበር ለወደብነት እጅግም ትኩረት አልሰጡትም ነበር፡፡ በአካባቢው ከነበሩ ወደቦች የጣልያኖችን ትኩረት የሳበው ምፅዋ ስለነበር ምጽዋን በወደብነት ማሳደግ ተያያዙት፡፡ በ1920ዎቹ አካባቢ በአሰብና በዙርያው ይኖር የነበረው ሕዝብ ከሦስት ሺህ የማይበልጥ ሲሆን ከእነዚህም አውሮፓውያን በተለይም ጣልያኖች ከ100 እስከ 140 ይደርሱ እንደነበር ተዘግቦአል[175]፡፡

የጣልያኑ ካቶሊክ ቄስ ሳፔቶ ለሩባቲኖ ኩባንያ አሰብን በገዛበት ጊዜ አሰብ የኢትዮጵያ አካል እንደነበረች አንድ የአፋር ፀሀፊ ዘግቦአል[176]፡፡ አጼ ምኒልክም የኢትዮጵያን ዳር ድምበር ለዓለም ሕብረተሰብ ለማስታወቅ ለንግሥት ቪክቶሪያ በፃፉት ደብዳቤ የአፋሩ ሱልጣን "ጥንታዊ ዜጋቸው" መሆኑን ግዛታቸውም በምሥራቁ በኩል የቀይ ባህርን ይዞ ደቡብ እንደሚደርስ አስታውቀው ነበር፡፡

በጊዜው በነበረው የመገናኛ ችግሮች የአፋር በረሃማነትና ከማዕከሉ በመራቅ እንደዛሬው የኢትዮጵያ መንግሥት በአፋር ላይ ሙሉና የቀን ተቀን ቁጥጥር ነበረው ማለት ባይቻልም የአፋር ባላባቶችን ግብር ማስከፈሉ አፋር የኢትዮጵያ አካል ነበረች ሊያሰኝ የሚችል በቂ ምክንያት ነው፡፡ ስለሆነም የአፋር ሱልጣን አሰብን ለሌላ መንግስት አሳልፎ የመስጠትም ሆነ የመሸጥ መብት አልነበረውም፡፡ ሱልጣን ኢብራሂምም አሰብን ለጣልያኖች በመሸጡ "ሱልጣን ኢብራሂም አሰብን የሸጠ" በመባል በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ ከሃዲ ተቆጥሮአል፡፡ በጊዜው በዚሁ በምሥራቅ ሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ይሯሯጡ የነበሩት የቱርኮች ተጠሪዎች ግብጾች

[175] Richard Pankhurst, An Introduction to the Economic History of Ethiopia From Early Times to 1800 (1961), p.307

[176] የግርጌ ማስታወሻ ቁ.36 ማየት ይቻላል



የአፋር ሱልጣን አሰብን የመሸጥ መብት የለውም በማለት ሽያጩን ተቃውመውት ነበር፡፡

አሰብን የገዛው የሩባቲኖ ኩባንያ አሰብንና ደሴቶቹን በሙሉ ለጣልያን መንግስት አስረክቦ "የጣልያን ቅኝ ግዛት" ተብለው በጣልያን መንግሥት እጁ ገቡ፡፡ በዚህ ጊዜ ጣልያን በሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ ሁለት ቅኝ ግዛቶች ነበሯት ማለት ነው፡፡ ሩባቲኖ ኩባንያ አሰብን ከገዛ ከአሥር ዓመታት በኋላ "አሰብ የጣልያን ቅኝ ግዛት" የሚለውን ስም ቀርቶ እ.ኤ.አ. በጃንዋሪ 1ቀን 1890 ዓ.ም በቀይ ባህር የሚገኙ የጣልያን ይዞታዎች "የኤርትራ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች" ተብለው አንድ ላይ ተጠቃለሉ፡፡ በጊዜው አሰብ በጣልያን እጅ እንዳትገባና የጣልያን ቅኝ ግዛት እንዳትሆን የተቃወሙ ጣልያኖችም ነበሩ[176]፡፡

የሩባቲኖ ኩባንያ አሰብንና ደሴቶቹን ሲገዛም ሆነ ወደ ጣልያን መንግሥት ሲያስተላልፈው ኢትዮጵያ የምታውቀው ነገር አልነበረም፡፡

አሰብ ከቀረው ኤርትራ ተለይታ ጣልያኖች ቅኝ ግዛት ሲያደርጉአት ከኤርትራ በባህልም ሆነ በዘር ወይንም በቋንቋ የተለየች አገር ነበረች፡፡

አሰብ ከምፅዋ ወይንም ከዘይላ ጋር ስትወዳደር በዕድሜ ለጋ ወደብ ነች ማለት ይቻላል፡፡ እድገትዋም ከስዌዝ ካናል መከፈትና ከአጼ ምኒልክ የግዛት መስፋፋት ጋር የተያያዘ ነው[177]፡፡

አሰብ ኤርትራ በጣልያን ግዛት ስር በነበረች ጊዜ ሳይቀር ትስስርዋ ከወሎ ጋር እንጂ ከኤርትራ ጋር አልነበረም፡፡ ጣልያን ኤርትራን በሚያስተዳድርበት ጊዜ ሁሉ የቀይ ባህር አፋሮች በሙሉ ግንኙነታቸው ከሃይማኖት መሪአቸው ከአውሳው ሱልጣን ጋር ሆኖ በመሃከላቸው የወሰንም ሆነ የአስተዳደር ልዩነት እንዳልነበረ የአፋር አዛውንቶች ይናገራሉ፡፡ አሰብ ከደሴ ጋር

[176] Moges Solomon, supra note 91.

[177] ዶ/ር ተወልደ ዝኒ ከማሁ 31 ገፅ 158.

በመኪና መንገድ ስትገናኝ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከአሥመራ ጋር የሚያገናኛት መንገድ ስላልነበረ ከአሰብ አሥመራ ለመሄድ ከአሰብ ወደ ደሴ ተመልሶ ከዚያ በኋላ ነበር ወደ አሥመራ ማቅናት ይቻል የነበረው።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ እንግሊዞች ኤርትራን ለአሥር ዓመታት ከአስተዳደሩ በኋላ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መሃከል ፌዴሬሽን ተመሥርቶ ኤርትራን ለቅቀው ሲሄዱ ፋብሪካዎችን ነቃቅለው ሕንጻዎችን አፈራርሰው ሊሸጥ የሚቻለውን ሁሉ ለጎረቤት ሱዳን ሲሸጡ የባቡር ሃዲዱም አልቀራቸውም ነበር። የወደብ መሣርያዎችንም ከምጽዋና ከአሰብ እየነቃቀሉ ወስደው የደረቅ ወደብ መገልገያዎችን (dry docks) በታትነው ለሱዳን ስለሸጡ አሰብ በፌዴሬሽን ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ስትዛወር ምንም ዓይነት የወደብ ግልጋሎት ልትሰጥ የማትችል "የወደብ ምድረ በዳ" ነበርች ማለት ይቻላል[179]።

## 10.2. የአሰብ እድገት

አሰብ ከኢትዮ-ኤርትራ ፌዴሬሽን በፊት እዚህ ግባ የማይባል ጥቅም ብቻ የምትሰጥ ማንም ትኩረት ያልሰጣት ትንሽ ወደብ ነበረች። የተሟላች ወደብ ሆና ማገልገል የጀመረችው ከአርባ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ እጅ ከገባች ወዲህ ነው። የኢትዮጵያና የኤርትራ ፌዴሬሽን እንደፈረሰ አሰብን በሰፊው መገንባትና ማስፋፋት ተጀምሮ በመጀመርያ ሞግራድ በሚባል የዩጎዝላቪያ ኩባንያ ሥራው ሲጠናቀቅ ለዚህም ሥራ 26 ሚሊዮን ብር በዛሬው ተመን ምናልባት ከ260 ሚሊዮን ብር በላይ ኢትዮጵያ ወጪ አውጥታለች[180]።

በደርግ አገዛዝ ዘመንም ወደቡ ከፍተኛ መሻሻል ተደርጉለት እንደነበርና ለዚህም ከመነሻው ጀምሮ ኢትዮጵያ ለአሰብ ግንባታ እስከ 3 ቢልዮን ዶላር የሚደርስ ወጪ እንዳደረገች በአንድ ወቅት የአሰብ አውራጃ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ጌታቸው በቀለ ለዚሁ ጸሐፊ ገልጸውለታል። ቀጥሎም ወደ አንድ ሚልዮን የሚጠጉ

[179] Shumet Sishagne,Professor, supra 43 P.53
[180] Ibid



ኢትዮጵውያን ያለቁበት ትልቁ ረሃብ በተከሰተ ጊዜ የእርዳታ እህል ለማስተላለፍ ብቁ እንዲሆን አሰብ በብዙ ሚልዮን ዶላር የሚጠጋ መሻሻል ተደርጉለታል[181]። በተጨማሪም ኢሕአዴግና ሻቢያ በፍቅር እፍ ባሉበት ወቅት ኢትዮጵያ ከሚሌ እስከ አሰብ ድረስ የሚወስደውን መንገድ በራስዋ ወጪ አሠርታ መንገዱን የሠራው የፈረንሳይ ኩባንያ ገንዘቡ ስላልተከፈለው ኢትዮጵያን ከስሶ እንደነበረ ይታወሳል። ለዚህ መንገድ ኢትዮጵያ ወደ 25 ሚልዮን ዶላር ወጪ እንዳደረገች ይነገራል። ኢትዮጵያ በአሰብ ከተማ የተለያዩ የመንግሥት ሕንፃዎችን፣ መንገዶችን፣ ተማሪ ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችንና መርከብ ማሳረፊያዎችን እንዲሁም አንድ ትልቅ የነዳጅ ማጣርያ አሠርታ ነበር። ለእነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያ በብዙ ቢልዮን ዶላር የሚገመት ወጪ ያወጣች ሲሆን ለዚህ ሁሉ ንብረት ኤርትራ አሰብን ስትወስድ ቤሳ ቤስቲኒ ለኢትዮጵያ አልከፈለችም። እንዲያውም አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት እስከ ዛሬ አሰብን በነፃ ስተጠቀምንበት ኤርትራውያን ሂሳብ እናወራርድ እንዳይሉን ስጋታቸውን ገልጸዋል። አሰብ ከፌዴሬሽኑ በኋላ በተደረገላት መሻሻል ትላልቅ መርከቦችን ለማስተናገድ ችላ ለመሃሉና ለደቡብ ኢትዮጵያ ዋናዋ የባህር በር ሆና ታገለግል ነበር።

ወደቡ ከነበረበት በጣም አድጎ ኢትዮጵያ ለቅቃው ስትወጣ በግምት 2.8 ሚሊዮን ቶን ጭነት ሊያስተናግድ የሚችል አቅም ነበርው። በአሁን ወቅት አሰብ ዘመናዊ ከተማ ስትሆን በውስጥዋም ብዙ መስኪዶችና ቤተክርስቲያናት፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የሕዝብ መገልገያዎች፣ የተሟሉ መንገዶች ሲኖሩአት፣ ከኢትዮጵያም ጋር በአስፋልት መንገድ ተያይዛለች። የአሰብ ወደብ በአሁን ጊዜ ሰባት ትልልቅ መርከቦች ሊያቆም ሲችል ባህረ ሰላጤው በጣም ትራፊክ ከሚበዛባቸው የዓለም ባህረ ሰላጤዎች አንዱ ነው። አብዛኛዎቹ በቀይ ባህር የሚያልፉ መርከቦች በአሰብ በኩል አድርገው ሲሆን በዓመት ወደ 20,000 የሚጠጉ መርከቦች

[181] Panel Vallily "Assab, "The Life line that could Feed Ethiopa, Report from Asseb", May 1, 2000.

7,000 ሚልዮን ቶን (ሰባት ቢልዮን) የሚጠጋ ጭነት ይዘው ይገዛሉ[182]።

## 10.3. ጁቡቲ አሰብን አትተካም

የጅቡቲን ወደብ መጠቀም ከብዙ ችግሮች ጋር ተያይዞ ይመጣል። በመጀመርያ የጅቡቲ እርቀት ከአሰብ ጋር ቢመዛዘን ስመሃል አገሩ በይበልጥም ለሰሜን ኢትዮጵያ በጣም ሩቅ ከመሆኑም በለይ ይኸም ለመኪና ሹፌሮች አድካሚ ሲሆን የትራንስፓርት ወጪውንም ያንረዋል። የጅቡቲ የወደብ አገልግሎት ታሪፍ በሌላ ቦታ እንደተጠቀሰው እለት በእለት እየጨመረ መሄድ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋ አስወድዶአል። በአሁኑ ወቅት ለተከሰተው እና ሕዝብን ለከፍተኛ ስቃይ የዳረገው ከውጭ ለሚገቡ ዕቃዎች የዋጋ ንረት የወደብ ታሪፍ መጨመር አስተዋጽኦ እንዳለው አያጠያይቅም። በጅቡቲና በኢትዮጵያ መካከል ታሪፍን አስመልክቶ የጋራ ስምምነት ቢኖርም ጅቡቲ ስምምነቱ ከመጤፍ ሳትቆጥር የወደብ አገልግሎት ታሪፍ የጨመረችባቸው ጊዜአት አሉ። በአንድ ወቅት ይህንን ጭማሪ ለማሰረዝ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር እራሳቸው ጅቡቲ ድረስ በመሄድ የተጣለው ታሪፍ እንዲነሳ ማድረጋቸው ይታወሳል።

ለጉምሩክ ሠራተኞች ‘ትርፍ ሰዓት እየተባለ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረጉ ነው። በጅቡቲ ወደብ ላይ ስለሚሰረቁና ብልሽት ለሚርስባቸው የኢትዮጵያ ዕቃዎች የወደቡ ሠራተኞች አላፊነቱን አይወስዱም[183]። ጭነት ወደ ኢትዮጵያ በሚያንጉዙ ሹፌሮች ላይ የሚደርሰው ወከባና እንግልት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ የዘር መድልዎ እንደሚደረግባቸው ሹፌሮቹ በተለያዩ ጊዜአት ተናግረዋል[184]። ጌት ፓስ (gate pass) ዴመሬጅ

---

[182] Araia Tseggai የኤርትራ ወደቦች አላፊ ሀአንድ ኤርትራ የወሬ ወኪል የሰጡት ማብራርያ

[183] በዛብህ አስፋው ዶ/ር ከፍጥጫው በስተጀርባ አዲስ አበባ የኅትመት 1997 ገጽ 83-84.

[184] ከአቶ በለጠ ማሞ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፤አዲስ አበባ (ጥቅምት 20 ቀን 2003) ዓ.ም



(demurrage) ስቶሬጅ (storage) እያሉ የሚያስከፍሉት በየ15 ቀናት ይቀይሩታል። ሱር ታክስ፣ ባጌጅ ታክስ፣ ረቬንዩ ታክስ፣ የክሬን ኪራይ እያሉ በየጊዜው የሚጨምሩት ክፍያ ጅቡቲ ወደብን የሚያስተዳድረው ዱባይ ወርልድ ኩባንያ በቀውስ ውስጥ በመሆኑ በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀስ ሲሆን እንቅስቃሴው የዘረፋ ዓይነት መሆኑን አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ አስገንዝበዋል[185]።

ከዚህም አልፎ የጅቡቲ ወደብ በአሁኑ ወቅት በችግር ላይ መሆኑ ይነገራል። ወደቡን ለማስተዳደር እ.አ.አ. ጁን 20 ቀን 2000 ዓ.ም የሃይ ዓመት ውል ከጅቡቲ ባለሥልጣናት ጋር የተፈራረመው የዱባይ የዓለም ወደብ ኩባንያ ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቁ ተዘግቦአል። ውሉ እንዲሰረዝለት የጠየቀበት ምክንያት በእርግጠኝነት ባይታወቅም ኩባንያው ለጁቡቲ ባለሥልጣናት የገባቸው ቃል አክብሮ ባለመገኘቱ ነው ይባላል[186]።

## 10.3. ኢትዮጵያ የባህር በር (አሰብ) እንዳይኖራት የሚጠነሰሰው ሤራ

ግሬጕሪ ኮኘሌይ (Gregory Kopley) የተባለ የአፍሪካ ኤክስፐርት ጋዜጠኛ ስለ ኢትዮጵያና ግብጽ ግንኙነት ሲጽፍ የሚቀጥለውን አስፍሮአል። “የግብጽ የአፍሪካ ቀንድ ዋነኛው ፖሊሲ ኢትዮጵያ በአካባቢው የበላይነት እንዳይኖራት ከባህሩ ዙርያ ማግለል ነው። ይህም ዓላማዋ በኤርትራና በኢራን አማካይነት እያስፈጸመች ነው። ግብጽ የኤርትራ የነፃነት ንቅናቄዎችን በመርዳት ቀደም ሲል የኢትዮጵያ የባህር ኃይል ይቆጣጠረው የነበረው የቀይ ባህር ደቡብ ክፍል ከኢትዮጵያ እጅ በማውጣት ኤርትራ ነፃ እንድትወጣና ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር አካባቢ ተገልላ በተፈጥሮም ሆነ በባህልም መቼም የኤርትራ አካል ሆና የማታውቀው አሰብንም እንድታጣ አደረገቻት[187]። ግብፅ

---

[185] አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብርአናንያ ዝኒ ከማሁ 24.

[186] "Djiboutl Port may Dirorce DPWorld, Capital Vol. 13. No 65 1 june 15,2011.

[187] Copley Gregory R. "Transforming the Age of Gas Begins in Earnest'"http://oibprice_.com_geo_politics/Africa_Energy_and_Security, Accessed 21 February 2011.

የአረብ መሪነትዋ በመጠቀም ሱዳን ፣ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ የመን፣ ሊብያና ሳውዲ አረቢያን በማቀነባበር ኢትዮጵያን ለማዳከም በመጣር ላይ ነች:: ግብጽ ይህንን የምታደርገው ጠንካራ ኢትዮጵያ በአባይ ውሃ ላይ ያላት መብትና የባህር በር መብትዋን ልታስከብር ትችላለች ከሚለው ፍራቻ በመነሳት ነው:: ግሬጉሪ ኮኘሌይ በመቀጠል እንደሚሉት አሁን ኢትዮጵያ ምንም ነገር ወደ አገርዋ ለማስገባት ብትፈልግ የጅቡቲ በጐ ፈቃድ ያስፈልጋታል:: ስለሆነም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ጦርነት ቢፈነዳ ግብጽ በጦርነቱ በግልጽ በመግባት ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የነበራትን ሥፍራ መልሳ እንዳትይዝ መከላከልዋ አይቀርም በማለት ይገልጻሉ::[188]

በመቀጠልም አሰብ አካባቢ የሚገኘው የአፋር ህዝብ የግድ ከኤርትራ ጋር በመቀላቀሉና በኤርትራ ቁጥጥር ስር በመዋሉ ከፍተኛ ቅሬታ እንደተሰማውና ከኤርትራ ቁጥጥር ለመውጣት ብረት አንስቶ እንደሚፋለም ኮፕሌ ፅፈዋል::[189] በጥቅምት 2003 ዓ.ም አቶ መለስ ዜናዊ ግብጽ በአባይ ወንዝ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ብትከፍት እንደማታሸንፍና ጦርነት የከፈቱም እንዳላዘለቀላቸው ከገለጹ በኂላ ግብጽ የኢሕአዴግ መንግስትን ለማናጋት ተቃዋሚዎችን ትረዳለች በማለት በከሰሱ ማግስት የኤርትራው ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ግብፅ ሄደው ከግብጽ ፕሬዝዳንት ሙባራክ ጋር በካይሮ ተገናኝተው መመካከራቸው የኮፕሌን አባባል አመኔታን ያጐናፅፈዋል::

ከሞምባሳና ለኢትዮጵያ ግልጋሎት እየተዘጋጀች ነች ከምትባለዋ የኬንያ ወደብ ላሙ በስተቀር ሌሎች ኢትዮጵያ ልትጠቀምባቸው የምትችል ወደቦች በሙሉ በአረብ ሊግ ውስጥ ሲሆኑ በድንበር አቋራጭ ወንዞችዋ ወይንም በሌላ ምክንያት ኢትዮጵያ ከአንድ አረብ ጋር ,በተለይም ከግብጽ ጋር ውዝግብ ውስጥ ብትገባ ግብጽ በአረብ አገሮች ላይ ባላት ተሰሚነትና የአረብ ሊግ አባላት ባላቸው ስምምነት መሠረት የአካባቢው ወደቦች በሙሉ ለኢትዮጵያ ዝግ ሊሆኑ ይችላሉ፡

[188] Ibid

[189] Ibid



የጅቡቲ ወደብ የሚተዳደረው በአንድ የዱባይ ኩባንያ ሲሆን ነገ የወደቡ አስተዳደር ወደ ግብጽ ቢዞርስ የሚለውን ማሰብ ብቻ በራሱ ስጋት ውስጥ ይጥላል:: የጅቡቲ የባህር በር ለአንድ ሳምንት ብቻ ለኢትዮጵያ ዝግ ቢሆን በኢትዮጵያ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ችግር መገመት አስቸጋሪ አይደለም::

ኢትዮጵያ በሕዝብም ቁጥር ብዛት ፣ባላትም የመሬት ስፋት በጠቅላላው ተፈጥሮ በለገሳት እምቅ ሃብትና በሕዝብዋ ታታሪነት የራስዋ የባህር በር ቢኖራት ታላቅ አገር የመሆን እድል ይኖራት ነበር:: ወደብ አልባ ሆና ግን ድህነትን እንኳን ማሸነፏ አጠራጣሪ ሲሆን ድህነትን ብትቀንስም እንኳን በዘለቄታ እይታ ታላቅ አገር ልትሆን አትችልም:: ወደብ አልባ ሆኖ ታላቅ የሆነ አገር የለም::

ኦስትሪያ፣ ስዊዘርላንድና ሉክሰምቡርግ ወደብ አልባ ቢሆኑም ሀብታም እንጂ ታላቅ የሚባሉ አገራት አይደሉም:: እነዚህ አገራትም ቢሆኑ ጐረቤቶቻቸው ሃብታሞች በመሆናቸው በቅርባቸው ሰፋፊ ገበያ ከመኖሩም በላይ የመገናኛ አውታሮቻቸው የደረጁ ሲሆኑ ግንኙነታቸውም በሰለጠነ መንገድና በሕግ ተደንግጉ የተያዘ ስለሆነ እነዚህ ሦስት አገራት በወደብ አልባ ከሆኑ አገራት ጐን ማሰለፍ አይገባም::

## 10.4. አሰብ ፣ሰላምና ልማት፣ የቀይ ባህር አፋሮች ኢትዮጵያዊነት

የልማት ሊቃውንት ለአንድ አገር መበልጸግ በአገሩ ለረጅም ዓመታት የሰላም መስፈን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ይገልጻሉ:: ለልማት ሊውሉ የሚችሉ ግብዓቶች እንደልብ ቢገኙ ሰላምና መረጋጋት ከሌለ ልማትና ብልጽግና ሊኖር እንደማይችል ግልጽ ነው:: ኢትዮጵያ ሳያቋርጥ ተያይዞ ለረጅም ዓመታት ይቅርና ለአምሳ ዓመታት እንኳን ሰላም አጣጥማ እንደማታውቅና ለዚህ ኢትዮጵያ ለተጫናት ድህነት ከዋናዎቹ ምክንያቶች አንዱ ከጦርነት አዙሪት መውጣት አለመቻሏ መሆኑን የታሪክ ምሁራን ይነግሩናል::

የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ምሁራንና ሌሎችም በኢትዮጵያ ለሰላም መደፍረስና ለግጭት መንስኤዎች የአባይ ወንዝ ውሀ

ፍትሐዊ አጠቃቀምና የኢትዮጵያ የባህር በር በተለይም የአሰብ ባለቤትነት ጉዳይ እንደሚሆን ሳያመነቱ ይናገራሉ። በፕሮፌሰር ጌታቸው በጋሻው እይታ ኢትዮጵያ በራስዋ ወደብ አድርጋ ወደ ባህር የመዝለቅ መብት በሰላም መፍትሔ ካልተሰጠው ወደ ፊት ብሔራዊ ስሜት ያለው መንግሥት መንበሩን ሲይዝ አሰብ ለጦርነት መንስኤ እንደምትሆን አያጠራጥርም ይላሉ።ይህንን አደገኛ ሁኔታ ለማስቀረት ለጋስ አገሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ድርድር መደረግ እንዳለበት ፕሮፌሰር ጌታቸው ያሳስባሉ።[190]

የድርድሩም ውጤት መሆን የሚገባውን አሰብን አለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ሲሆን ይህም ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን የጦርነት መዓት ያስቀራል ይላሉ ፕሮፌሰር ጌታቸው። እያድርገውና ለወደፊቱ በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል ግጭት ቢፈጠር መንስኤው የወሰን መከላከል ጉዳይ ሳይሆን በአሰብ ባለቤትነትና በአፋር ህዝብ አንድነት ላይ ያጠነጠነ እንደሚሆን የተለያዩ ምሁራን ያስገነዝባሉ። አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ የፕሮፌሰር ጌታቸው አቋም በማጠናከር የሚከተለውን ብለዋል።

*"የአሰብ ጉዳይ የተደፈነ እሳት ማለት ነው። አማራጭ እያለህ ዝም ብለህ የምታካሄደው ጦርነት (War of Choice) የምርጫ ጦርነት ሊሆን አሁን ያጋጠመን ግን ልንሸሸው የማንችል አስገዳጅ ጦርነት (War of necessity) ነው። ምርጫ የሌላት አገር አስገዳጅ ጦርነት ለማካሄድ ትገደዳለች። የኢትዮጵያና የኤርትራ ችግር አሁን የድምበር ብቻ አይደለም፤ የመሬትም ጉዳይም አይደለም፤ ዋናው አንኳሩ የባህር ወዳብ ጉዳይ ነው።ሁላችንም ቁጭ ብለን ችግራችንን መፍታት ያለብን በተለይም ደግሞ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ይሄ ችግር መኖሩን አውቀው ከኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጋር በግልጽ መነጋገር አለባቸው። ምክንያቱም እነርሱም ወደ ሥልጣና የመ... እንደሆን ከእነርሱም ጋር ጦርነት መግጠማችን አይቀርም። ኢሕአዴግ ካላደረገው ቀጥሎ የሚመጣው መንግሥት ይሄንን ጥያቄ እንደሚያነሳና ኢሕአዴግንም እንደሚወቀስ እምናለሁ።[191]*

[190] Getachew Begashaw, supra note 6

[191] ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ ዝኒ ከማሁ 24.



አሰብ ጥንትም አሁንም የአንድ ብሔረሰብ የአንድ ኃይማኖት ተከታይ የሆነውን ከጥንታዊቷ ከሱሲ (ድንቅነሽ) ብንጀምር ምናልባት የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን መሬት ነች። በአፋሮች ዘንድ የኢትዮጵያ፤ የኤርትራ፤ አፋር የሚባል ነገር የለም። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል የተፈጠረው ክፍፍል አፋሮች በጽኑ ይቃወሙታል። የሃይማኖትና የዓለማዊ ጉዳዮች አሳፊ የአሳይታው ሱልጣን ሲሆኑ እኚህ ሰው የአፋሮች ሁሉ አባትና መሪ ተደርገው የሚቆጠሩ ከቅርብ ሳምንታት በፊት ያረፉትና የጅቡቲው ጠቅላይ ሚኒስትር በክብር የቀበሩአቸው ቢትወዳድ ሱልጣን አሊሚራህ ሀንፋሬ ናቸው። ክቡር ቢትወደድ በአፄ ኃይለ ሥላሴ የአገዛዝ ዘመን የአውሳ (አሰብ) አውራጃ አስተዳደሪ ቢሆኑም ከሌሎች የኢትዮጵያ አውራጃ አስተዳዳሪዎች የተለየ ሥልጣንና ለንጉሠ ነገሥቱ ቀረቤታ ነበራቸው። የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትም በአፋር ውስጣዊ ጉዳዮች ጣልቃ አይገባም ነበር[192]።

አሰብ ምን ጊዜም በታሪካም ጭምር ከኤርትር የተለያች ብትሆንም ጣልያኖች ከኤርትራ አካል በግድ ቢቀላቅልዋትም ምን ጊዜም ቢሆን ሕዝቡ የኤርትራ አካል መሆኑን አልተቀበለውም። በኤርትራ የሚታየው ከፍተኛ የሆነ የኤርትራዊነት ብሔራዊ ስሜት በአፋሮች ዘንድ አይታይም። ክቡር ቢትወደድ ሱልጣን አሊ ሚራህ ሌሎችም የአፋር መሪዎች በተለያዩ ወቅቶች እንደገለፁት ኢትዮጵያዊነታቸውን አጥብቀው የያዙ ሕዝቦች ናቸው።

ክቡር ቢትወደድ አሊ ሚራህ ለዶክተር ፍቅሬ ቶሎሳ በሰጡአቸው ቃለ ምልልስ እንዲህ ብለው ነበር። "የአፋር ሕዝብ እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን ወዳድ ነው በታሪኩና በባህሉም ይኮራል። ኢትዮጵያዊነታችንም ማንም ሊነፍገን አይችልም የአፋር ሕዝብ ጠላቶች ብቻ ናቸው አፋርን የተለዩች አድርገው የሚቆጥሩት። እነኚህ ጸረ ሕዝቦችን እናጋልጣቸዋለን። ይኸም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲባል መደረግ አለበት"[193]። እንዲሁም

[192] የአንድ አፋር አዛውንት ለፀሐፊው የነገሩት ፣ አዲስ አበባ ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

[193] ክቡር ቢትወደድ አሊ ሚራህ በሐምሌ ወር በ1983 ዓ.ም አዲስ አበባ በተደረገው የሰላም ጉባዔ የተናገሩት

ክቡር ቢትወደድ አሊ ሚራህ በሐምሌ ወር 1983 ዓ.ም ኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ለማደራጀት በጠራው ጉባዔ ላይ ተገኝተው አቶ መለስና አቶ ኢሣያስ ባሉበት "የአፋር ሕዝብ ወሰን ቀይ ባህር ነው። ግመሎቻችን እንኳን የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውቁአታል" ብለው ነበር[194]። እንዲሁም በሽግግሩ ቻርተር ስብሰባ ላይ ለቀድሞው ቺፍ አቭ ስታፍ ሌተና ጀኔራል ጻድቃን ገብር ትንሣኤ በሰጡት ቃለ ምልልስ የቀይ ባህር አፋሮች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው እንዲወስኑ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው እንደ ነበር ጀኔራል ;ብበ በጽሁፋቸው ገልጸውታል[195]። የራሴን ዕድል በእራሴ እወስናለሁ በማለት ለብዙ ዓመታት ተዋግታ ይህንኑ ያስከበረችው ኤርትራ የቀይ ባህር አፋሮችን የግድ ከኤርትራ ስር. ትሆናላችሁ በማለትዋ እንደማንኛውም ለመብቱ ተቆርቋሪ ሕዝብ የአፋር ሕዝብም ነፃ ለመውጣትና ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል ያለው መብት ማንም ሊገድበው አይችልም።

ከላይ ' በተለያዩ ምሁራን እንደተገለጸው ወደፊት በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ግጭት ቢነሳ መንስኤው ኤርትራ እዚህ አንድ ኪሎ ሜትር እዚያ ሌላ አንድ ኪሎ ሜትር የኢትዮጵያን ወሰን ጥሳ ገባች በሚል ሳይሆን (ያም የማይፈቀድ ቢሆንም) ኢትዮጵያ የባህር በር ተዘግቶባት ልማቷ፤ ደህንነትዋና ሉዓላዊነትዋ አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ነው። ኢትዮጵያ ለ40 ዓመታት በከፍተኛ ወጪ የገነባቻችው የባህር በሮች አንድ የነበረ አገር ለሁለት ተከፍሎ አንዱ ሁሉቱንም የባህር በሮች ጠቅልሎ ሲይዝ ሌላው ደግሞ ባዶውን ይቅር ማለት ፍትሕና መልካም ጉርብትና የማይቀበለው ጉዳይ ስለሆነ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሰላም አሰብን ወደ ኢትዮጵያ በማካለል ላይ መንጠልጠሉ ያለ ማመንታት መተንበይ ይቻላል።

በመጨረሻም ኤርትራውያንስ የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን በተለይ አሳብን አስመልክቶ ምን ይላሉ የሚለው ጥያቄ መፈተሽ ያለበት ጉዳይ ነው፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት ነች እያሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጽሁፎች ሲያወጡ በየአጋጣሚው ሲከራከሩ ኤርትራውያን ለዚህ ለኢትዮጵያውያን አቋም መልስ ሲሰጡበት ብዙ ጊዜም

[194] ዝኒ ከማሁ

[195] Abebe, T. Kahsay, supra note 3



አልተደመጠም። ይህ ጽሑፊ አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት ነች በማለት ለጻፈው ወሎ ተወልደው ያደጉትና የቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የአንትሮፖሎጂ መምህር የነበሩት በአሁኑ ጊዜ የሻቢያ አባልና የአሥመራ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር አሥመሮም ለገሠ መልስ ሲጸፉ የሚከተለው ብለው ነበር።

> *"አሰብ ወደብ የኢትዮጵያ ነው ብለው በአሁኑ ጊዜ የሚከራከሩት ትምህርት የሚይለውጣቸው ጊዜ የማያስተምሯቸው የአማራ ባለሥልጣናት የነበሩ ናቸው። አሰብ የኢትዮጵያ ነው እያሉ የሚከራከሩ ነፍጠኞች አንዳንድ የወያኔ መሪዎችን በመስበክ ኢትዮጵያና ኤርትራ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑና የትግራይ ልጆች እርስ በርሳቸው ተናንቀው ተሳልቀው ሲያበቁ የአመረር ክፍተት ስለሚፈጥር ምንም ሳይዋጉ ወደ ሥልጣናቸው የመመለስ ድብቅ አጀንዳ ያላቸው ናቸው"* [196]

ፕሮፌሰሩ የኢትዮጵያ ችግሮች በሙሉ በአማራ ላይ ማላከክ ልማድ ሆኖባቸው ነው እንጂ ጸሐፊው ኢትዮጵያዊ እንጂ የአማራ ነፍጠኛ የሚባል ነገር ካለ "የአማራ ነፍጠኛ" እንደልሆነ በተገነዘቡ ነበር። ለኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መከራከር ነፍጠኛ የሚያሰኝ ከሆነ በ1997 ዓ.ም በኢሕአዴግና በተቀዋሚዎች በተደረገው ክርክር ነፍጠኛነቱን እንዳገለጸ ሁሉ ይህ ጽሐፊ አሁንም ነፍጠኛ ነው።

ይህ አቋም የፕሮፌሰሩ የግላቸው ሲሆን በአቶ ኢሣያሰ ተቃዋሚዎች በኩል ምንም የተደመጠ ነጋር የለም። ሆኖም የአቶ ኢሣያስ ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ መንግሥት እንደመደገፋቸው ወደብን አሰመልክቶ ከኢሕአዴግ ጋር አንድ መግባቢያ እንደቀየሱ መገመት ይቻለል።

[196] ልትኩርት ጥቅምት 14 ቀን 1993 ዓ.ም

## ምዕራፍ 11

## 11. በአግባቡ የተስተናገደ የካሜሩንና የናይጀርያ የድንበር ውዝግብ

ብዙ አገራት ድምበር ውዝግብ ውስጥ ገብተው ጦር ከተማዘዙ በኋላ እንኳን ውዝግቡን ሕግና ሥርዓትን በተከተለና በሰለጠነ መንገድ ፈትተው በመሃከላቸው የኢኮኖሚ የሰላልና የፖለቲካ መስተጋብሮችን ፈጥረው በመልካም ጉርብትና ይኖራሉ። ከዚህ በታች ያለው የናይጀርያና የካሜሩን የወሰን ውዝግብ አፈታት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። በካሜሩንና በናይጀርያ መሃከል የነበረው የድምበር ውዝግብ አፈታት በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል ከነበረው የድምበር ውዝግብ አፈታት ፍጹም የተለየ ነው። የኢትዮጵያና የኤርትራው ውዝግብ ገና በጅምሩ የተሰረዙ የቅኝ ግዛት ውሎች መሠረት አድርጎ ሲነሳ የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን ሲሰርዝ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ጥቅሞችን ያላገናዘበ መሆኑ ግልጽ ነበር። ስለሆነም ውሳኔውና አፈጻጸሙ ችግር ቢገጥመው አያስገርምም። የአገሩ መሠረታዊ ጥቅሞችን አገናዝቦ ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ በትክክለኛ መድረክ በየአገሮቻቸው ተወላጆች የተመራ የካሜሩንና የናይጀርያው የድንበር ውዝግብ ክርክር ምን እንደሚመስል ከኢትዮጵያውና ከኤርትራው ጋር ማወዳደር እንዲቻል በዚህ ፁሁፍ አካትቼዋለሁ[197]።

እ.አ.አ በ1970ዎቹ የናይጀሪያ አንዷ ክልል የሆነችውን ቢያፍራን ለመገንጠል በተሞከረ ጊዜ የናይጀርያው ፌዴራል መንግሥት በመቃወሙ የእርስ በእርስ ጦርነት ተቀሰቀሰ ካሜሩን በጦርነቱ የፌዴራል መንግሥቱን በመርዳትዋ የወቅቱ የናይጀርያ

[197] ስለካሜሩንና ናይጀርያ የወሰን አካለል የተወሰደው ከዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔ አጠቃለይ ዝርዝር ዘገብ 94 (International Court of Justice, General list 94). International Court of Justice, The Case Concerning The Land and Maritime Boundary Between Cameroon and Nigeria, (Cameroon Vs Nigeria, Equatorial Guinea intervening, 10 October 2002



መሪ የነበሩት ጄኔራል ያኩቡ ጋዎን ሁለቱ አገራት በይገባኛል ይጨቃጨቁበት የነበረው በተለያዩ ጊዜያት ጦር የተማዘዙበት ባካሲ የተባለ የባር ሰላጤ (Peninsula) ለካሜሩን ሰጡ። በዚሁ ቁጭት የተነሳ የናይጀሪያ የጦር ኃይል ጋዎንን ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከሥልጣን አባረሩአቸው። ጄኔራል ጋዎንን የተኩት ጄኔራል ሙርታላ መሃመድ ስምምነቱን ወዲያውኑ ሰርዘው የናይጀሪያን ጦር አሰፈሩበት።

በሙርታላ መሃመድ እግር የተተኩት ፕሬዚዳንት አባሳንጆም ደግሞ በዚሁ ስለጸኑ ካሜሩን ውዝግቡ ዘሔግ ወደሚገኘው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በከሳሽነት አቀረበችው።

ከስምንት ዓመታት ሙግት በኋላ ለውሳኔው አርባ ቀናት ሲቀር የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሀፊ ኮፊ አናን የሁለቱን አገራት ፕሬዚዳንቶች ስለ ባካሲ ለመወያየት ፓሪስ ጋብዙአቸው በውይይቱ መሃከል ኮፊ አናን ሁለቱን ፕሬዚደንቶች የፍርድ ቤት ውሳኔ ምንም ይሁን ምንም እንዲያከብሩ ቃል አስገቡአቸው።

ፍርድ ቤት እ.አ.አ 10 አክቶበር 2002 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ባካሲ ለካሜሩን ተሰጠ። የታወቀው ንቁ የናይጀርያ መገናኛ ብዙሃን በተለይ ጋዜጠኞች ውሳኔውን አውግዘው በሰፊው ጻፉ በሕዝቡም በኩል ከፍተኛ ቅዋሜ ቢነሳም አባሳንጆ በቃላቸው እረጉ።

የባካሲ ነዋሪዎችም በበኩላቸው "ለእኛ ባካሲ ሕያው ነው። ባካሲ ወንዶች፣ ሴቶችና ሕፃናት ማለት ነው.......የናይጀርያ ዜጎች ነን። በቤታቸውና በመሬታቸው ላይ ስለሚኖሩ ሰዎች ነው የምንነጋገረው ሲሉ ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ ተቃውመዋል። የእነርሱ አቋም የገለፁበት ቋንቋ እንግሊዝኛው በቅጡ ይገልጸዋል። "For us Bakasi is real. It is men, women and children. It is people living in their homes, on their land. We are Nigerian citizens. We do not have any other place to go." የእነዚህ ሰዎች አባባል በድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ወደ ኤርትራ የተጠቃለሉት የኩናማ፣የባድመ፣ የአፋርና የኢሮብ ሕዝቦች ከሚሉአቸው ጋር ተመሳሳይነታቸው አስገራሚ ነው።

በዚሁ ፍርድ ቤት በጊዜያዊ ዳኝነት (Judge ad hoc) በናይጀርያ ተመድበው ከአሥራ አምስቱ ዳኞች አንዱ የነበሩት በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የነበረው ውዝግብ ለመዳኘት በኢትዮጵያ የተመረጡት ናይጀርያዊ ልዑል ቦለ አጂቦላ (Prince Bola Ajibola) ነበሩ። ባካሲ የማን ነው በሚለው ክርክር አጂ ቦላ እንግሊዝና ናይጀርያንና ፋረንሳይ ካሜሩንን የተካፋፋሉበት የቅኝ ግዛት ውል ውድቅ በማድረግ ከሌሎች ዳኞች በመለየት ባካሲ ለናይጀርያ ትገባለች በማለት ለአገራቸው ለናይጀርያ ፈረዱ።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል በነበረው የድምበር ኮሚሽን ክርክር ጊዜ ግን እኚህ ሰውዬ ኢትዮጵያ መርጣቸው በዳኝነት ተቀምጠው የቅኝ ግዛት ውሎችን በማጽደቅ የ90 ሚልዮን ሕዝብ የባህር በር ሲያዘጉ ቅርም አላላቸውም። "በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት" ዓይነት ሲሆን ለነገሩ እርሳቸው ምን ያድርጉ? "ባለቤቱ ያቀለለው እምሴ ባለዕዳ አይቀበለውም" እንዲሉ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ከመጤፍ ያልቆጠሩት የባህር በር ጉዳይ የውጭ ዜጋ ለምን አልተጨነቀለትም ብሎ መውቀስ ትክክል አይደለም። ውሳኔ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ወሰን አካልሉ ችካል ለመትከል አልተሄደም። ተቃውሞውን ለማብረድ ሲበል የተባበሩት መንግሥታት ወኪሎች ይህንኑ ጸሐፊ ጨምሮ የናይጀርያና የካሜሩን ተወካዮች የሚገኙበት አንድ የጋራ ኮሚቴ ተቋቋመ።

በኢትዮጵያና በኤርትራ፤ በናይጀሪያና በካሜሩን የወሰን መከለል የዳኝነት ጉዳይ የጐሉ ልዩነቶች አሉ። ዋነኛው በካሜሩንና በናይጀሪያ መሃከል የነበረው ውዝግብ ከጅምሩ አንስቶ እስከ ድምዳሜው ድረስ ሕዝብ የተጠያየበት፤ አላፊነቱ በውጭ አገር ዜጐች ላይ ሳይሆን በአብዛኛው በየአገራቱ ዜጐች ላይ የተጣለበት ሁኔታ ሲሆን በኢትዮጵያ ግን መንግሥት የአልጀርስን ስምምነት ሲፈርም ሕዝቡ ሳይጠያይቅበት የኢትዮጵያ ምሁራን አስተያየት ተንቆ ሥራው በሙሉ ማለት ይቻላል ለውጭ አገር ዜጐች የተተወበት ሁኔታ ነበር።

ሌላው ልዩነት በአብዛኛው በዓለም ዙርያ እንደሚደረገው የመሬት ይገባኛል የወሰን ውዝግብ ካሜሩንና ናይጀርያ እንዳደረጉት ለዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ይቀርባል እንጂ ብዙም ጊዜ ምንም



ተጠያቂነት ለሌለባቸው ግለሰቦች አይተውም። በአመዛኙ የድንበር ውዝግብ ለግልግል ኮሚሽን የሚቀርበው ጉዳዩ ብዙም አጨቃጫቂ ሳይሆን ግልጽ ሆኖ በተለይም ጉዳዮ በቶሎ እልባት እንዲሰጠው ሲፈለግ ወይንም አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲኖሩ ነው።

የተኩስ አቁም ታውጆ የሕይወት መጥፋትና የንብረት መውደም እስከሌለ ድረስ ኢትዮጵያ ለውሳኔ የምትጣደፍበት ምንም ምክንያት አልነበረም። በተለይም ኢትዮጵያ የባህር በር ከሚዘጋ የሚበልጥ ያህል ትልቅና ወሳኝ ብሔራዊ ጉዳይ ይገጥማታል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው። ስለሆነም ጉዳዩ ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መሄድ ሲገባው ለማንም ተጠያቂ ባልሆኑ ግለሰቦች ለተቋቋመ ኮሚሽን ተሰጠ። ለአብነት ያህል የወሰን ውዝግባቸው ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ከወሰዱ አገራት ጥቂቶቹ ኒካራጓ፣ ኮሉምቢያ፣ ሆንዱራስ፣ ኢንዶኒዝያ፣ ማሌዥያ፣ ናሚብያ፣ ቦትስዋና፣ ቻድ፣ ሊብያና ሌሎችም ብዙዎቹን መጥቀስ ይቻላል።

ኢትዮጵያ ግን ለማንም ግልጽ ባልሆነና ማንም ሊገባው ባልቻለ ፍጹም እንቆቅልሽ በሆነ ምክንያት ማንም ሳያስገድዳት የምትገኝበት ሕግን (በተለይ የቅኝ ግዛት ውሎች) መርጣ ይግባኝ ሊባል በማይቻልበት መድረክ ዳኞችን ሰይማ ውሳኔውን የተባበሩት መንግሥታት፣ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት፣ የአሜሪካ መንግሥት፤ የአውሮፖ ሕብረትና ሌሎችም እንዲያስፈጽሙ ተስማምታ ራስዋን በማይፈታ ማነቆ እግር ተወርች ተብትባ በሉዓላዊነቷ ላይ እንዲወስኑ በአላፊነት ሊጠየቁ ለማይችሉ ግለሰቦች አስረከበች። ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል እንደሚባለው ውጤቱም ለጦርነቱ መንስኤ የሆነው፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን ያለቁበት ባድመንና ሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች ኮሚሽኑ ለኤርትራውያን ጋር ሲሰጥ ውዝግቡ እልባት ሳያገኝ እነሆ ተንጠልጥሎ ከኤርትራዊያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር መልካም ጉርብትና ከመፍጠር ፋንታ ደመኛ ጠላትነት ተመሠረተ።

ናይጀራያ የተባበሩት መንግሥታት ፍርድ ቤት ውሳኔ ከብዙ ማመንታት በኋላ ተቀብላ ባካሲን ለማስረከብ ፈቃደኛ ብትሆንም እንኳን ጉዳቱ ለናይጀሪያ እምብዛም ነበር። ምክንያቱም ከባካሲ በተጨማሪ ናይጀርያ ብዙ ትላልቅ ሕደቦች ያሉአት አገር ናት።

ባካሲ የናይጀርያ ብቸኛ ወደብ ብትሆን ኖሮ በምንም ዓይነት ባካሲን ለካሜሩን እንደማታስረክብ የዚሁ ጸሐፊ አንድ የሥራ ባልደረባና ከኮሚሽኑ የናይጀሪያ ተወካዮች አንዱ አረጋግጠውለታል። ሌላው ልዩነት ናይጀርያና ካሜሩን የፍርድ ቤቱ ውሳኔዎቹ በሕዝቡ በኩል ተቀባይነት እንዲያገኙ የተደረጉ ጥረቶች ናቸው።

በካሜሩንና በናይጀሪያ መሃከል የነበረው የፍርድ አፈጻጸም ለመከታተል የናይጀርያ፣ የካሜሩንና የተባበሩት መንግሥታት ባልደረቦች የሚገኙበት የተለያዩ የጋራ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ኮሚቴዎቹ ወደ ድንበሮቹ በመሄድ ውሳኔውን ለሕዝብ እያስረዱና፣ እያረጋጉ እንዲሁም የድንበሩ መስመር የሚያርፍበት ቦታ ተማሪ ቤቶችን፣ መስጊዶችንና ቤተክርስቲያናትን የመሳሰሉት የሚከፋፍል ከሆነ ኮሚቴዎቹ ይህንን እያስተካከሉ አንድም ቀን ውዝግብ ሳይፈጠር እነዚህ ኮሚቴዎች 22 የናይጀርያ ትናንሽ የድምበር ከተሞችና ባካሲን ለካሜሩን አስረከቡ። እነዚህ ኮሚቴዎች በካሜሩንና በናይጀሪያ ወሰኖች ለሚገኙ ሕዝቦች የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔ ለማስረዳትና ሕዝቡን ለማረጋጋት ለሳምንታት እየተጓዙ ያልረገጡት የሁለቱ አገራት ድምበሮች የሉም ማለት ይቻላል። ወደ ሕዝቡ ለመድረስ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር የመኪና ጉዞ ይደረግ እንዳነበራና እነዚህም ጉዞዎች ምን ያህልም አድካሚ እንደነበሩ ይህ ጽሐፊ ያስታውሰዋል። የኮሚቴው አባላት በእነዚህ በሁለት እህትማማች አገራት መሃከል በአፍሪቃ እንድተለመደው ውዝግባቸው በጦር ኃይል መፍታት ሳይሆን በጠርጴዛ ዙርያ እንዲፈቱ በመርዳታቸው በሥራቸው እጅግ ይኮሩና ይረኩ ነበር።

በኢትዮጵያና በኤርትራ ድምበር አካለል በነበረው ግን ድምበር እንዲያካልል ሕዝቡን እንዲያግባባ ጉራማይሌ ሁኔታ ሲያጋጥም እርማት እንዲያደርግ ሁለቱም ወገኖች ሥልጣን የሰጡት የጋራ ኮሚሽን ሳይኖር የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በቀጥታ በሕዝብ ጉሮሮ ውስጥ እንዲሽነቈር ተወሰነ። ቀይቶም የናይድርያን የካሜሩንና የተባበሩት መንግሥታት የጋር ኮሚሽን ምሳሌነት በመከተል ይመስላል አቶ መለስ የጋራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ድንበር አካለሉ ችካል ይትከል የሚል ሃሳብ ቢያቀርቡም ኤርትራ በመቃወምዋ በኮሚሽኑ በኩል ጥያቄችው ተቀባይነት አላገኝም።



የባካሲ ሕዝብም ቢሻው ናይጀሪያዊ ዜግነቱን እንደያዘ ቢሻው ደግሞ ካሜሩንያዊ ሆኖ በነበረበት መሬት እረግቶ እንዲኖር ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው እስከ ዛሬ አንድም ሰው ከቤት ንብረቱ ሳይፈናቀል ሕዝቡ በሰላም ይኖራል።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ባለው፤ የድንበር ኮሚሽኑ የሚያካልለው መሬት ሕዝብ የሰፈረበት እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ ችግሮች መፈጠራቸውና የኮሚሽኑ ውሳኔ ቃል በቃል ለመተግበር ችግር እንደሚፈጥር ባለመረዳት ወይንም ችላ በማለት የኮሚሽኑ ውሳኔ በግርድፉ በሕዝብ ጉሮሮ ውስጥ ለመሸንቆር ተሞክሮአል። ስለሆነም የኤርትራና የኢትዮጵያ የወሰን መካሰል ችግር ላይ መውደቅ እጅግም አያስገርምም።

የናይጀርያና የካሜሩን ውዝግብ ሕግን ተከትሎ ሕዝብን አሳትፎ በሰለም በመጠናቀቁ ሁለቱም አገራት በዓለም አቀፍ ሕብርተሰብ ዘንድ ክብርና ሞጋሰ ያጉናጸፋቸው ሲሆን ኤርትራንና ኢትዮጵያ ግን ለሕግ ተገዢ ሆነው የድምበር ውዝግቡ ለመፍታት ብቃቱም ሆነ ፍላጐቱ ስላሳሳዩ በዓለም አቀፉ ሕብረተስብ ፊት እንደሚዋረዱበት አያጠራጥርም።

## ምዕራፍ 12

# 12. የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ መደምደሚያና አንዳንድ የመፍትሔ ጥቆማዎች

ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን በደም፣ በቋንቋ፣ በባህልና በሃይማኖት የተሳሰሩ ለመሆኑ ተደጋግሞ የተባለ ነገር ነው። ምናልባት ተደጋግሞ ያልተባለ ነገር ቢኖር ስውርም ይሁን ግልጽ በቃላት አይገለጥ እንጂ ሁለቱም ሕዝቦች አንዱ ለአንዱ ያለው የውስጥ ትስስርና የወገናዊነት ስሜት ነው። ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ቀጥሎ የሚቀሰቅሳቸው ነገር ቢኖር ከሌላ ከየትኛውም አገር በፊት የኤርትራ ጉዳይ ነው። ምናልባት ብዙ ኢትጵያውያን የኤርትራ መገንጠል ጊዜያዊ ቁጣ ቢያሳድርባቸውም የነበረው ችግር ከመገንጠል በመለስ ሊፈታ ይችል ነበር የሚል እምነት ቢኖራቸውም መገንጠሉ ያ ልዩ ውስጣዊ ስሜትን ሊሰርዘው አልቻለም። ስንቶቻችን ነን ከኤርትራውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር አንድ ክፍል ቁጭ ብለን የተማርን፣ ስንቶቻችን ነን አንድ ማዕድ ቁጭ ብለን እንጀራ የቆረስን፣ ከዚያም አልፎ ስንቶቻችን ነን በራሳችን ወይንም በልጆቻችን የደም ስር ኤርትራዊ ወይንም ኢትዮጵያዊ ደም የሚንቆረቆረው?

ኢትዮጵያውያን ይሸሽጉት እንደሁ እንጂ ለኤርትራውያን ያላቸው ስሜት ለኬንያውያን፣ ለሱዳናውያን ወይንም ለሶማሌያውያን ካላቸው ስሜት ፍፁም የተለየ ነው። ኤርትራውያንም እንዲሁ ጊዜያዊ ጥላቻቸው የወንድማማች ስለሆነ አንዳንዴ በከረረ መልኩ ቢገለፅም ዘላቂነት ግን የለውም። ይህ ስሜት በሳይንስ መርምሮ ተንትኖ ምን እንደሚመስል ማስረዳት አይቻልም፤ ስሜት ስለሆነ። ሆኖም ስሜቱ ምን እንደፈጠረው ግን መረዳት ይቻላል። "ዘር ከልጓም ይስባል" የሚለው ብሂል የኢትዮጵያንና ኤርትራውያን ሁኔታ እውነትነቱን ሲያረጋግጥ ታሪክ፣ ባህል ቋንቋ ወዘተ... ለትስስሩ ገመድ ተደራቢ ናቸው። ኤርትራን በውል ለመደምሰስ የሚታጣ ኃይል ቢነሳ ኤርትራን



ለመታደግ ኢትዮጵያውያን ወደ ዘማቾች ማግኘት አይቸግርም። በኤርትራውያን በኩልም ይኸው ነው። ነበርም። ለዚህም ዘርአይ ድረስ፣ አብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም ሌሎችም ለኢትዮጵያ ነፃነት የተዋደቁት እጅግ ብዙ ኤርትራውያን ሕያው ምስክሮች ናቸው። በኤርትራ ሙዚቃ ስሜቱ የማይነካ ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያ ሙዚቃ መንፈሱ የማይረካ ኤርትራዊ ይገኛል? ምናልባት ከአረብ አገራት ውጪ እንደ ኢትዮጵያውያንና እንደ ኤርትራውያን ለሁለት የተከፈል ተመሳሳይ ሕዝብ በአፍሪቃ የለም ማለት ይቻላል። ተመሳሳይ ፊደል፣ ተመሳሳይ ቋንቋ፣ ተመሳሳይ አለባበስ፣ ተመሳሳይ ምግብ፣ ተመሳሳይ የፀሎት ስርዓት፣ ተመሳሳይ የሙዚቃ መሳሪያና ሙዚቃ፣ ተመሳሳይ መልክ፣ ተመሳሳይ ስሞች፣ ተመስሳይ አቱራረስ፣ ተመሳሳይ የኑሮ ዘይቤና ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያላቸው ሁለት አገራት በዓለም ጥቂቶች ሲሆኑ በአፍሪቃ ከኤርትራና ከኢትዮጵያ ውጭ ሌሎች የሉም ማለት ይችላል። ይህም ሲባል በኤርትራም ሆነ በኢትዮጵያ ከዚህ በተመሳሳይነት ከተሰለፉት ሕዝቦች ውጭ ሌሎች ለየት ያሉ ቋንቋም ሆነ ባህል ያላቸው ሕዝቦች የሉም ማለትም አይደለም።

የእነዚህ የሁለቱ አገራት የዘለቄታ መፃኢ እድል የተሳሰረ መሆኑ ግልፅ ነው። "በሃበሽ" ላይ ከተሰነዘረ ጥቃት ይውል ያድር እንደሆን እንጂ ኤርትራም አታመልጥም። በኤርትራም በኩል እንዲሁ። የአንዱ ጠላት የሌላው ጭምር መሆኑ የአረብ ካባ የደረበ ጊዜያዊ ማሞካሸት ሃቁን አይሽረውም።

ከአፍንጫቸው አርቀው ሊያዩ ባልቻሉ ወይንም ሕሊናቸውን ሥልጣን በጋረደው አንዳንድ መሪዎች ምክንያት በሁለቱ ወንድማማችና እህትማማች ህዝቦች መሃከል የተሸነቆረው ጠላትነት በሕዝቡ ውስጥ ሊሰርጽ አለመቻሉ አላፊነት በጎደለው መልኩ አንዳንድ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ በተባረሩ ጊዜ ሕዝቡ ሊያስጥላቸው ሳይችል ሲቀር በእምባ እየተራጨ እንደሸኛቸው በቂ ማስረጃ ነው። እንዲሁም ፍጹም ሰብአዊ እርህራሄ በራቀው መልኩ ሻቢያ አሥመራን በተቆጣጠረ ማግስት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ከኤርትራ ሲያባርር ሕዝቡን አማክሮ ሳይሆን እንዲያውም ከሕዝቡ ሸሽጎ ነው።

የሁለቱም አገራት መሪዎች ይህንን ወንድማዊና እህታዊ ትስስር እንደማይፈልጉት ከአንድ ምሳሌ ማረጋጥ ይቻላል። የኤርትራ ሕዝብ "ነፃነት" ትመርጣለህን ተብሎ ለሚቀርብለት ጥያቄ ማለትም ለሬፈረንደሙ ጥቂት ቀናት ሲቀሩ የሕዝቡን ትስስርና ታሪኩን በጥልቀት የሚያውቁ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን "በሰላምና ልማት ኮሚቴ" አዘጋጅነት በቪዲኦ (video) የተቀረጸ ውይይት አድርገው ነበር። እነዚህ ታዋቂ ግለሰቦች ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎ፣ ዶክታር ደጃአዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም፣ አቶ ተፈሪ ብርሃኔ፣ ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋና አቶ ኅሙኤል ዓለማየሁ ሲሆኑ ውይይታቸው ያተኮረው በኢትዮጵያ ሕዝብና በኤርትራ ሕዝብ መሃከል በነበረውና ባለው ትስስር ላይ ሆኖ ይህንኑ እጅግ በሚመስጥ መልኩ ካስረዱ በኋላ ይኸ ትስስር በጊዜው ሆይ ሆይታ እንዳይበጠስ በእጅጉ ተማፅነው ነበር። በመቀጠልም ሁለቱ አገራት ለጊዜው በነበረው ትስስር የማይቀጥሉ ከሆነ መተላለቅ እንዳይኖር ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተማጽኖአቸውን አቀረቡ። ይኸ በጥልቅ እውቀት የተከሸነ ስሜትን የሚቀሰቅስ ምልጃና አቤቱታ በከፍተኛ ወጪ በቪዴዩ ከተቀረጸ በኋላ በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ መገናኛ ብዙሃን ለሕዝቡ እንዳይተላለፍ ታገደ።

የታገደውም ቀደም ሲል በመሪዎች ተወስኖ የነበረው ኤርትራን የመገንጠል ሂደት ያደናቅፋል ከሚል ነበር። እንዲያውም ይህንኑ ውይይት ባዘጋጀው በዚሁ ጸሐፊ ላይ ከፍተኛ ወቀሳና ውግዘት ደርሶበታል።

ለኤርትር ሕዝብ የቀረበለት ጥያቄ በራሱ የኤርትራና የኢትዮጵያ መሪዎች የፈለጉት ውጤት የሚያስገኝ ሲሆን ሕዝቡ በመገንጠሉ ሊከተል የሚችለው አደጋ፤ የሚቀርበት የጋራ ጥቅም፤ እንደ አገርነቱና እንደ ሕዝብነቱ ምን ያህልስ እንደሚያሳሳው በሚገባ ባልተገለፀለት ሁኔታ ሕዝቡ መገንጠልን ቢመርጥ ምንም አያስገርምም። አርቆ አስተዋይ መሪዎች ኖረው ሁለቱ አገራት በሆነ ትስስር ተያይዘው ወይንም ተዋህደው የኤርትራ አምስት ሚሊዮን ህዝብ ከኢትዮጵያው 90 ሚሊዮን ጋር ተደምሮ ሁለት ስትራተጂክ የሆኑ የባህር በሮች፤ ሰፊ ለም



የእርሻ መሬት፤ መጠነ ሰፊ የውሃ ሃብት ያለው ይህ ፌዴራላዊ ወይንም አሃዳዊ አገር ምንኛ ጠንካራ፤ የማይበገርና የበለጸገ አገር ሊሆን ይችል እንደነበር በምናባችን ስንቃኘው በራሱ ያማልላል።

በቅርብ ጊዜ አንዳንድ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን በውጭ አገር የኢትዮጵያና የኤርትራ የወዳጅነት መድረክ አቋቁመው ይህ የሁለቱ አገራት መሪዎች የበጠሱት የትስስር ገመድ እንዴት መቀጠል እንደሚቻል በሰከነ መንፈስ የጀመሩት ውይይት ደብል የሚያሰኝ ነው። የዚሁ ውይይት ዋነኛ ቀስቃሽ የሆኑት ፕሮፌሰር ተስፋ ፅዮን መድሃኔ በአንድ ወቅት የኢትዮጵያና የኤርትራ ትስስር መቀጠል አለበት በማለት የዓፉት የአንድነት ጥሪ አቶ መለስ ዜናዊ "የኤርትራ ትግል ቁልቁል አይደፋም" በሚል የመልስ ምትና ሌሎችም ጸረ አንድነት ኃይሎች ፕሮፌሰሩን ማብጠልጠላቸው ፕሮፌሰር ተስፋ ፅዮን ከቁብ ሳይቆጥሩት ዛሬም ይህንኑ ትግል በግምባር ቀደምትነት ሲጀምሩት በአርቆ አሳቢነታቸውና በድፍረታቸው እናደንቃቸዋለን። ይህ የሚችለው አሰቃቂ መዘዝ ከማምከኑም በላይ ምናልባትም ዓላማ ቢሳካ የኢትዮጵያን የባህር በር መዘጋት ሊያመጣ በምሥራቅ አፍሪቃ አንድ የበለጸገች የታፈራችና የማትበገር ፌዴራላዊ ወይንም አሃዳዊ አገር ብቅ ትል ይሆናል።

አሁን ያለው ነባራዊ ሁኔታ እንደሚያሳየን ኢትዮጵያ የባህር በር ተዘግቶባት ሕልውናዋና ልማትዋ አደጋ ላይ ወድቆ ይገኛል። ይህ በሆነበት ሁኔታ ኢትዮጵያውያን የባህር በርን በተመለከተ አፋቸውን ዘግተው መቀመጥ ለአገራቸው ያለባቸው ግዴታ መጣስና አባቶቻቸውና እናቶቻቸው የጣሉባቸውን አደራ መብላት ነው በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ምክንያት ኢትዮጵያውያን የሚያሰሙትና የሚያንፀባርቁት እጅግ የከረረ ምሬትና ቁጭት ኤርትራውያን ከፍትሃዊነት ከወንድማማችነትና ከመልካም ጉርብትና አንፃር ማየት ይጠበቅባቸዋል። ኤርትራና ኢትዮጵያና አንድ አገር ሆነው ለአርባ ዓመት አብረው በቆዩበት ጊዜ ሁለት የባህር በር የነበራት አገር ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ በተባበሩት መንግስታት ፊት ቆመው አድማጩን ባስደመመ ንግግራቸው ኤርትራ ሁለት የባህር በር ሲኖራት ኢትዮጵያ

እንዴት ወደብ አልባ ትሁን ብለው የጠየቁት ጥያቄ ዛሬም አግባብነት ያለው ሆኖ ብቅ አለ።

ለመሆኑ ኢትዮጵያውያን በኤርትራ መገንጠል ምን ይሰማቸዋል ቢባል የእያንዳንዱ ግለሰብ ስሜት ለአገሩ ካለው ፍቅር ጋር የሚመጣጠን ነው ማለት ይቻላል። ለአንዳንዱ የአገር መቁረስ ከዳቦ መቁረስ አስበልጦ የማያየው ሲሆን ሌላው ደግሞ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም እንዳሉት "ብዙ ሰዎች [መገንጠልን] በጣም ይጠላሉ፤ እንደሞት ይፈሩታል"[199]።" ስለሆነም አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የወንድሞቻችንና የእህቶቻችን መለየት አሳዝኖታል ቢባል በበቂ አይገልፀውም። ያም ሆኖ ግን ዛሬ የኤርትራን መገንጠልን ብዙ ኢትዮጵያን ተቀብለውታል። አምባሳደር ዘውዴ ረታ ስለኤርትራ ነጻ መንግሥት ሆኖ መቋቋም ያሉት ዛሬ የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ስሜት ያንጸባርቃል ማለት ይቻላል። አምባሳደር ዘውዴ ኤርትራውያን በቅጡ አስበውበት ከሆነ "ኢትዮጵያዊነት ጎድቶናል፤ ነፃ መሆን ይጠቅመናል ብለው ለብዙ ዓመታት ተዋግተው መለየትን የመረጡት ወንድሞቻችንና [እህቶቻችን] ኤርትራውያኖች ስለሆኑ ምርጫቸውን እንቀበለዋለን"[199]። ሆኖም ኢትዮጵያውያን አንድ የማንቀበለው ነገር ቢኖር ከቀይ ባህር በእግር መንገድ እርቀት የሚገኘውን አሰብን ለቀቀን ሕልውናችንና እድገታችን ለአደጋ ለማጋለጥ ፈቃደኛ ባንሆን ተወቃሽ አንሆንም።

በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ከኢትጵያውያን የሚደመጠው ምሬት ኤርትራውያንን ማስከፋት አይገባውም። ኤርትራውያን ስለ አገራቸው የሚሰማቸውን ያህል ሁሉ ኢትዮጵያውያንም ይሰማናል። እኛም እንደ ኤርትራውያን አገራችንን እንወዳለን። አቅማችን በፈቀደ መብትዋና ሕጋዊ ጥቅሞችዋን ለማስጠበቅ እንጥራለን። በተለይም አንዲት ጋት መሬት በሌላው የማያስነካው የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያ ተቀርቋሪ ስለሌላት ብቻ የባህር በር ይቀርቀርባት ማለት ኢትዮጵያውያን መቼም ቢሆን የማይቀበሉት በደል ከመሆኑም

[199] መስፍን ወልደ ማርያም፣ ፕሮፌሰር፣ ዝኒ ከማሁ 37. ገፅ 96
[199] ዘውዴ ረታ (አምባሳደር)፣ ዝኒ ከማሁ 95. ገፅ 79



በላይ ለዘለቄታውም ቢሆን ለኤርትራም የማይበጅ ነገር ይሆናል። ኢሕአዴግን የሚተካው መንግስትም ቢሆን ቅንጣት ያህል ብሔራዊ ፍቅር ካለው የባህር በር ጉዳይ እንደ ኢሕአዴግ በቸልታ ሊያልፈው ሕዝቡ አይፈቅድለትም። የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት ዋነኛ አጀንዳው ካላደረገው በስልጣን ሊቆይ የሚችለው በጠመንጃ ኃይል ብቻ ይሆናል። ስለዚህ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን አሰብ ወደ ኢትዮጵያ የሚታጠፍበት ሰላማዊና ፍትሐዊ መንገድ ቀይሰው አቋማቸውን ይፋ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አማራጩ ከዚህ በፊት እንደታየው አሳስፈላጊ የሆነ የወንድማማቾችና የእህትማማቾች መተላለቅና እንደገና እንዳለፈውም የዓለም ሕብረተሰብ መሳለቂያና መዘባበቻ መሆን ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብን ጥያቄ ሊመልሱ የሚችሉ ሦስት ፍትሐዊ አማራጮችን መጠቆም ይቻላል። በእነዚህ በሦስት አማራጮችም ሆነ በሌሎች መፍትሔዎች ዙርያ ኢትዮጵያውያን ተወያይተው አንድ የጋራ አቋም ቢይዙ ለጥያቄአቸው ጥንካሬ ይሰጣል።

12.1. አሰብን ከነደሴቶቿና ሕጉ የሚፈቅደው 12 ኖቲካል ማይልስ ወደ ባህሩ ገባ ብሎ ያለው ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍና ሁለቱም አገሮች ጤናማ ግንኙነት መሥርተው ሕዝቡ ከአንዱ አገር ወደ ሌላው በነፃ እንዲንቀሳቀስና ሰፊው የኢትዮጵያ ገበያ ለኤርትራውያን ክፍት ሆኖ ኤርትራ የኤሌትሪክ ኃይልና የምግብ ሰብሎች ወዘተ ከኢትዮጵያ በዘመድ ዋጋ እንድትገዛ መፍቀድ። እንዲሁም ኢትዮጵያ የኤርትራ ምርቶችን እንድትገዛ መስማማት አንዱ አማራጭ ነው።

12.2. ኤርትራ የእርሻ መሬት እንደሚያስፈልጋት ሁሉ ኢትዮጵያም የባህር በር ያስፈልጋታል። አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋ ከላይ የተዘረዘሩት ሕጎች ቢደነግጉም ለሰላምና ለመልካም ጉርብትና ሲባል ሁለቱም ሃገራት የወሰን መሸጋሸግ አድርገው ኤርትራ የተወሰነ የእርሻ መሬት ተሰጥቶአት አሰብ ከላይ በተገለጸው መልኩ ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ሌላው

አማራጭ ነው። እዚህ ላይ በአጽንኦት መነገር ያለበት ይህ አማራጭ ሃሳብ የቀረበው ለሰላምና ለመልካም ጉርብትና ሲባል እንጂ የአሰብ ኢትዮጵያዊነት በምንም መልኩ ጥያቄ ውስጥ አያገባም።

12.3. አሰብ ከነደሴቶቹ ሁለቱም አገራት ማለት ኢትዮጵያና ኤርትራ በጋራ ይዘውት ሁለቱም ጣምራ ሉዓላዊነት (Joint Sovereignty) እንዲኖራቸው መስማማት ይችላሉ። የጣምራ ሉዐላዊነት ዝርዝር ከሌሎች አገራት ተሞክሮ በመነሳት ምን ምንን እንደሚያጠቃልል በቅድሚያ በድርድር ሊወሰን ይችላል። ይህ ጣምራ ሉዐላዊነት ተመሳሳይ ችግር ባላቸው አገሮች የባህር በሮችንና ደሴቶችን አስመልክቶ የሚሠራበት ሲሆን ጥቂት ምሳሌዎችንም መጥቀስ ይቻላል።

አሰብን አስመልክቶ በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ያለው አቋምና ስሜት በእስራኤሎችና በፍልስጤማውያን መሃከል ካለው አቋምና ስሜት ጋር ይመሳሰላል። ኢየሩሳሌም በይሁዳውያን ልብ ሰርፃ እንደገባ ሁሉ አሰብም በኢትጵያውያን ዘንድ በተመሳሳይ ስሜት ይንፀባረቃል። ስለሆነም እስራኤላዊያን ኢየሩሳሌምን በምንም ዓይነት ለፍልስጤማውያን እንደማያስረክቡ ሁሉ ኢትዮጵያውያንም መቼም ቢሆን አሰብ የኤርትራ ግዛት ነች ብለው አይቀበሉም።

እስራኤልና ፍልስጤምን አስመልክቶ ብዙ ሰዎች ሁለቱ አገራት በሰላምና በመልካም ጉርብትና እንዲኖሩ ከተፈለገ በኢየሩሳሌም ላይ ጣምራ ሉዓላዊነት የሚሰጣቸው ቀመር ያስፈልጋል ይላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያና ኤርትራ በሰላምና በመልካም ጉርብትና እንዲኖሩ ከተፈለገ በአሰብ ላይ ጣምራ ሉዓላዊነት ኖሮአቸው የአሰብ ውስጣዊ አስተዳደር ራሱን በቻለ በሕዝብ በተመረጠ ካውንስል እንዲተዳደር ማድረግ ይቻላል። በዓለም ዙርያ በሁለት አገራት ጣምራ ሉዓላዊነት ስር የሚተዳደሩ ብዙ ከተሞች ወይንም ክልሎች ይገኛሉ። ለምሳሌ ቻንዲጋር (Chandigarh) የተባለ ከተማ የሕንድ ሁለት ክልሎች



(States) ዋና ከተማ ሆኖ ሁለቱም ክልሎች በከተማው ላይ ያልተከፋፈለ ጣምራ ሉዓላዊነት አላቸው[200]።

እንዲሁም ሕንድና ፓኪስታን ካሽሚር ይገባኛል በሚል ውዝግብ ምክንያት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወታደሮች በየወሰኖቻቸው አሰልፈው የኑክሌር ጦርነት ለለባ ከመሆን፣ ብዙ ሰዎች ካሽሚርን ሁለቱም አገራት በጣምራ መያዝ ይበጃቸዋል ይላሉ። በተመሳሳይ መልኩ አንዶራ የተባለ አገር ፈረንሳይና ስፔን በጣምራ ከያዙት ከ700 ዓመታት በላይ ሆኖአል[201]።

አገራት ሌላው አጎራባች ወደብ አልባ አገር የባህር በር ባለቤት እንዲሆን ከግዛታቸው እንኳን ቆርጠው የሰጡባቸው ሁኔታች አሉ። የተባበሩት መንግስታትም ሆነ መላ ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ አገራት በሰላማዊ መንገድ የባህር በር ባለቤት እንዲሆኑ ይደግፋሉ። ምክንያቱም ፍትሐዊ ስለሆነ ነው። በዓለም ዙርያ አገራት በተለያዩ ምክንያት የባህር በር ባለቤት ሆነዋል። ዙርያዋን በመሬት ተከብባ የነበረችው የዛሬዋ የዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ወደ ባህር የሚያሸጋግር ከአንጎላ መሬት ተቈርጦ ተሰጥቶአት ዛሬ ኮንጎ ሪፐብሊክ የባህር በር ባለቤት ሆናለች።

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በቬርሳይ ውል መሠረት ፖላንድ ወደ ባህር የሚያዘልቃት መሬት ከጀርመን ተቆርሶ ተሰጥቶአት ወደብ አልባ የነበረችው ፖላንድ የወደብ ባለቤት ሆናለች። እነዚህ አማራጮች የምንጠቁመው ከሁሉም የተሻሉ መፍትሔዎች ናቸው በሚል እምነት ሳይሆን የግድ ሳንወድ ግን እነዚህ ሁለት እህትማማች አገራት ከመለያየታቸው በፊት ወደ ነበረው፣ ያም ካልሆነ ወደ ፌዴሬሽኑ ያም ካልሆነ በኮንፌዴሬሽን ተሳስረው ቢቆዩ ለዘላቂ ሰላማቸውና ለብልጽግናቸው የተሻለ መሆኑ ማንም አይስተውም።

[200] Fred E.Foldvary, Senior Editor of Progress Report, http:// progress. Org / fold 250. html
[201] Ibid

ኢትዮጵያ በአንድ ወይንም በሌላ መንገድ አሰብ ካልተመለሰላት ችግሩ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው እየተላለፈ በቦሊቪያ እንዳለው ሁኔታ ቁስሉ እያመረቀዘ ይሄዳል እንጂ ኢትዮጵያውያን መቼም የሚተዉት ጉዳይ አይሆንም። ቦሊቪያ በ1883 ዓ.ም ከቺሊ ጋር ባደረገችው ጦርነት የባህር ጠረፍ ግዛትዋ በቺሊ ተወሰደባት። ቦሊቪያ የባህር በር ሲወሰድባት ነፍሷ ከዚያው ጋር ሄደ እያሉ ቦሊቪያውያን ይገልጹታል። ቦሊቪያ የባህር ጠረፍ ግዛትዋ ከተወሰደባት ጊዜ ጀምሮ ወደ አምስት ሺህ የሚጠጋው የባህር ኃይሏ አንድ ቀን የባህር ጠረፍ ግዛታችን እናስመልሳለን በሚል ተስፋ እስከ ዛሬ በቲቲካ ሐይቅ የባህር ላይ ጦርነት ልምምድ ያደርጋሉ። እንደ ቢቢሲ ዘገባ ያቦሊቪያ ዜጋ ሁሉ ከልጅነቱ ጀምሮ ያደገው ቺሊ የባህር ጠረፋችን ሰረቀችን ሲባል እየሰማ ሲሆን እርሱም በተራው ለልጆቹ ይህንኑ እየነገረ ያሳድጋል። ማንኛውም ቦሊቪያዊ አገርህ ወደብ አልባ ሆነች ሲሉት በምንም ዓይነት የማይቀበለው ሲሆን ሕዝቡም በየዓመቱ "የባህር በር የተወሰደበት" ቀንን ዘክሮ ይውላል። ቅርብ ጊዜ ደግሞ ከ132 ዓመታት በኋላ የባህር በሬ በቺሊ ተወሰደብኝ የምትለዋ ቦሊቪ ጉዳዩን ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንደምትወስደው አስታውቃለች[202]።

የአሰብ ችግርም ለሁለቱም፤ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ በቶሎ ይፈታል አልያም እንደ ቦሊቪያው ችግር ተንጠልጥሎ ይቆያል እንጂ መቼም ቢሆን ኢትዮጵያውያን የሚተዉት ጉዳይ አይደለም። በመሃሉ ግን ለሁለት ወንድማማችና እህትማማች ሕዝብ ለእልቂት መንስኤ ሲሆን መቻሉ ግን አሳዛኝ ነው።

ኢሕአዴግ በዲፕሎማሲም ይሁን ወይንም በሌላ በማንኛውም መንገድ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲታጠፍ ፍለጐቱ እንደሌለውና ብሎም እንዲያውም እንደሚቃወም በከረሩ ቃላትና በብስጭት ስሜት በተደጋጋሚ ገልጾአል። ከዚህም አልፎ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማካለል የሚሞክር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ኃይል

[202] See http://www.bbc.co.uk/news/world_latin_America_12842978. Accessed on 3/3/2011.



ቢነሳ ኢሕአዴግ እርምጃ እንደሚወስድበት ከዚህ ቀደም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአጽንኦት አስጠንቅቀዋል።

ይህም ማለት ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ በሥልጣን እስከቆየ ድረስ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት የመሆን ዕድል ዜሮ ነው ማለት ነው። አልያም ቀይ ባህር የአፋር ክልልን ለሁለት ሰንጥቆ የባህር ሰላጤ የሚፈጥር መሆኑ በጂኦሎጂስቶች ስለተረጋገጠ በኢሕአዴግ ዘመን ኢትዮጵያ የባህር በር የሚኖራት ይህ ስንጥቅ በጥቂት ሺህ ዓመታት ወደ ፊት ማስቀደም ከተቻለ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ በአፋር በኩል በቀይ ባህር ቦይ ተቆፍሮ ውሃውን ወደ ኢትዮጵያ ማዝለቅ ይቻላል ይላሉ። እነዚህ ለፌዝ ይባሉ እንደሆነ ነው እንጂ ለአሰብ ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ለኤርትራም ይሁን ለኢትዮጵያ ይህን ያህል የሚከብድ ጉዳይ አይደለም። ጉዳዩ በኢሕአዴግ ዘመን መፍትሔ ካላገኘም በአገራችን አባባል "እርስት በሺህ ዓመቱ ለባለቤቱ" እንዲሚሆን አንጠራጠርም።

የሃርቫርድ ፕሮፌሰር ሩፐርት ኤመርሰን (Rupert Emerson) እንዳሉት "በአሁኑ ወቅት የአፍሪቃ አገራት ቅኝ ገዢዎች በቀየሱአቸው ወሰኖች መታሰር በቅኝ ግዛት ጊዜ የተተነበየውና የተፈለገውን አያንጸባርቁም። በቅኝ ግዛት ጊዜ የተተነበየው የአፍሪቃ አገራት ነፃ ሲወጡ እነዚህ በኢምፔርያሊስቶች በዘፈቀደ የጂኦግራፊ የኤኮኖሚ ገጠመኞችን በመሻር የተወሰኑ ድምበሮች ተሰርዘው አህጉሪቷ የተፈጥሮ መሰመርዋን ተከትላ የተፈጥሮ ቅርጽዋን ትይዛለች የሚል ተስፋ ነበር[203]"።

ሁለት አገራት አንድ ሆነው የተፈጥሮ ቅርጻቸው መያዝ ከሚገባቸው አገራት ኤርትራና ኢትዮጵያ በቀዳሚነት ማስቀመጥ ይችላል።

ይህ ከዚህ በላይ በሓርቫርድ ፕሮፌሰር ሩፐርት ኤመርሰን የተፃፋው እንግሊዝኛው በተሻለ ይገልጸዋል።

[203] See www.Ethiomedia.com /andanun/2432.htiml.

"The present consolidation of African states within former colonial borders runs counter to much of what had been predicted and desired during colonial era. It was widely assumed that as soon as Africans came to freedom they would sweep aside the abrbitrary boundaries imposed by imperialists which cut across tribes and override the dictates of geography and economics. The continent had been partitioned to meet colonial convenience, but it would be reshaped to realize its natural contours and return to its natural essnce[204]."

Erasing colonial imposed lines between Ethiopia and Eritrea will surely restore the natural contour and essence of this ancient region.

[204] ibd



## ምዕራፍ 13

## አባሪዎችና የተለያዩ የሕብረተ ሰቡ ክፍሎች አስተያየቶች

### 1. በኢትዮጵያ ሕልውና ላይ የተጋረጠ አዲስ አደጋ[205]

በዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም

ቀድሞውኑም ቢሆን በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ መቅሰፍት የሚታመሰው፤እጅግ አደገኛ በሆነው በአፍሪቃ ቀንድ ከዚህ በፊት ባልነበረና የአካባቢውን ፀጥታና ሰላም ከአሁኑ በበለጠ ሊያናጋ የሚችል በቀጭን ክር የተንጠለጠለው የጂኦፖለቲካውን ይዘት የሚያተራምስ፤ አካባቢውን በኑክሌር ጦርነት ቀለበት ውስጥ የሚዘፍቅ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል አዲስ ክስተት እየተፈጠረ ነው።

ይኸውም የኑክሌር ቦምብ ባለቤት ለመሆን በግልቢያ ላይ የምትገኘው ኢራን በቀይ ባህር በተለይም በአሰብ ላይ የጦር ሰፈር እንዳቋቋመችና ሚሳይሎችን እንደጠመደች በተለያዩ የዜና ምንጮች ተዘግቦአል።

የኢትዮጵያና የኤርትራ ትርጉም የለሽ ጦርነት በ1993 ዓ.ም. በኢትዮጵየ አሸናፊነት ተደምድሞ የአልጀርስ ስምምነት ከመፈረሙ ሳምንታት በፊት አሰብ ከሻቀጥ ማስተላለፊያነቱ በበለጠ ለኢትዮጵያ ሕልውናና ነፃነት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወትና አስገንዝበን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ የማያጥፍ ምንም ዓይነት ስምምነት የኢትዮጵያ ባለስልጣናት እንዳይፈርሙ ብዙዎቻችን አሳስበን ነበር። ከአልጀርስ ስምምነትም በኋላ ከቶም ምንም የማይሳናቸው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር "አሰብ የግመል ውኃ ማጠጫ ይሁን" ብለው ከረገሙ

[205] <u>በአዲስ ነገር</u> ጋዜጣ የወጣ፤ 1998 ዓ.ም (አካባቢ)

በኋላ ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡና ከኢትዮጵያ የሚወጡ ማንኛቸውም ሸቀጣ ሸቀጦች በጅቡቲና በሌሎች የአካባቢው ወደቦች በኩል እንዲገቡና እንዲወጡ ወሰኑ።

የቀይ ባህር ሰላጤ (Red Sea Iittoral) በአሳ ሀብት የበለፀገች፣ የቱሪስት መስህብ የሆነችና በማህፀንዋ ብዙ ዓይነት ማዕድናት ያቀፈች እጅግ ስትራቴጂክ የሆነችዋ የባህር ሰላጤ ነች ኤርትራ እራስዋ ካልተጠቀመችበት ለሌሎች ሲከፋም ለኢትዮጵያ ጠላቶች አሳልፋ ትሰጥ እንደሁ እንጂ የግመል ውኃ ማጠጫ እንደማትሆን በጊዜው አሳስበን ነገር። ብዙ ነበር ማለቱ ባያስደስተንም የተፈራው ደርሶ እነሆ በተባለው መልኩ ምናልባትም የኢትዮጵያ ጠላት መሆንዋ በውል ባይታወቅም ወደጅ መሆንዋ ያላልተረጋገጠው ኢራን በአሰብን ላይ ጦር አስፍራ ሚሳይሎች እንዳጠመዳች የዓለም ዜና አውታሮችና ልዩ ልዩ ምንጮች ዘግበዋል። በይዘቱ ይህን መጣጥፍ የሚመስል ሳሁፍ ይኸው ጸሐፊ ለአዲስ ነገር ጋዜጣ አቅርቦ ከታተመ በኋላ በኢትዮጵያ የኢራን አምባሳደር መልስ ሲሰጡ "ያዕቆብ የፅዮናውያን አሽከር ነው" ብለው ከመሳደብ ውጭ የኢራን ጦር አሰብ ላይ አልሰፈረም የሚል ማስተባበሪያ ከአፋቸው አልወጣም። ኤርትራ አሰብ ላይ የኢራን ጦር አልሰፈረበትም ብላ ብታስተባብልም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ለኤርትራ ምንም ጥቅም የማይሰጠው አሰብ እውነትም የግመል ውኃ መጠጫ ሆኖ ሲቀር ኤርትራ ስለማትፈቅድ ለለየላቸው የኢትዮጵያ ጠላቶችም ቢሆን አሳልፋ መስጠትዋ የጊዜ ጉዳይ ነው።

### 1.1 አቶ ኢሳያስ አሰብ ላይ የኢራን ጦር እንዲሰፍርና ሚሳይሎች እንዲጠመዱ ለምን ፈቀድ?

የድንበር ውዝግቡ እንዲዳኝ በኢትዮጵያና በኤርትራ ስምምነት የተሰየመው የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ አለመፈጸሙ ይታወሳል። በሂደትም ኤርትራ በተለያዩ ወቅቶች በኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ላይ ትንኮሳ በማካሄድ፤ የሰላም ቀጣናውን ጥሳ በመግባት የተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪ ኃይል ከኤርትራ በማባረር የአልጀርስን ስምምነት ጥሳለች። አንድ ዓለም አቀፍ ውል ውድቅ የሚሆነው አንዱ ወገን ውሉን ሲጥስና ሌላው ወገን



ከእንግዲህ ውሉ እንደማይገዛው ሲያስታውቅ ነው። የኢህአዴግ መንግስት በቂ ሕጋዊ ምክንያት ቢኖሩትም የአልጀርስ ስምምነት ውድቅ ሆኗል ለማለት ለምን ወኔው እንደከዳው አይታወቅም። ያም ሆነ ይህ የድንበር ውዝግቡ እልባት ባለማግኘቱ እነዚህ ሁለት አገሮች በጦርነት ይፋለሳጋሉ የሚል ከፍተኛ ስጋት አለ። ጦርነት ቢነሳም በኤርትራ ሽንፈት እንደሚደመደም መገመት ይቻላል። ይህም የሚሆነው የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል ከኤርትራ አቻው ጋር በጀግንነት ይበልጣል ለማለት ሳይሆን ሁለቱም ከአንድ ህዝብ አብራክ የመነጩ በመሆኑ የጦርነቱ ውጤት የሚወስነው የህዝብ ብዛትና የኢኮኖሚ አቅም ነው። አሸናፊው የኢትዮጵያ ጦርም ወደ አሰብ ዘልቆ አሰብን ይይዛል የሚል ስጋት በኤርትራውያን ዘንድ መኖሩ አያጠራጥርም። ጦርነት ባይነሳ መልካም ነው፤ጦርነቱን ማምከን ካልታቻለም ግን የኢትዮጵያ ሕዝቡ ከመከላከያ ኃይሉ የሚጠብቀው ይኸው ነው።

አቶ ኢሳያስ በቅርብ ጊዜ የኑክሌር ጦር መሣሪያ ልትታጠቅ ለምትችል ኢራን አሰብ ላይ ጦርዋን እንድታሰፍር ሲፈቅዱ ጦርነቱ ቢነሳ ኢትዮጵያ አሰብ ላይ ኢራንን ልትገጥም አቅሙ አይኖራትም ከሚል ስሌት ተነስተው የኢትዮጵያ ሕጋዊ የአሰብ ባለቤትነትን ለማምከን አስበው ያደረጉት ይመስላል።

አቶ ኢሳያስ የኢራን ጦር አሰብ ላይ እንዲሰፍርና ሚሳይሎችን እንዲያጠምዱ ሲፈቅዱ አሰብ ምንም የማያከራክር ያለቀለት የኤርትራ ግዛት ከመሆን አልፎ እንደፈቀዱ የሚያዙበት፣ ቢሻቸው አሳ የሚያሰግሩበት፤ ቢሻቸው የኑክሌር ሚሳይሎች ለሚያጠምዱበት አገሮች አሳልፈው ሊሰጡ የሚችሉ የግል እርስታቸው አድርገው ቆጥረውት ነው።

አሰብ ከሉሲ (ድንቅነሽ) ብንነሳ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን የአፋሮች የእነ ቢትወደድ ሡልጣን አሊ ሚራህ፣ የእነ ደጃዝማች ሃንፍሬ አገር መሆኑን አቶ ኢሣያስ የዘነጉት ይመስላል። የአሰብ ባለቤትነት ዛሬ የጥቂት ኢትዮጵያውያን ምሁራን ወይንም ፖለቲከኞች ጉዳይ ሳይሆን ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ ከምሁሩ እስከ ገበሬው የሚቆጠቁጠው ስለሆነ አዲስ አበባ ወይንም ገጠር ውስጥ አንድ መንገደኛ ቢጠየቅ የሚያረጋግጠው

ነው። ዛሬ ሕዝቡ በኢህአዴግ ዘመን ከደረሱ ጥፋቶች ሁሉ የትኛው ይበልጣል ተብሎ ቢጠየቅ ሳያመነታ የኢትዮጵያ የባህር በር መዘረጋት ነው እንደሚል በፍጹም አያጠራጥርም። ልክም ነው።

## 1.2. የኢራን ጦር አሰብ ላይ መስፈር ለኢትዮጵያ ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ስጋቱ እምን ላይ ነው?

ተስፈንጣሪዋ ኢራን ለኤሌክትሪክ ኀይል ማመንጫና ለመሳሰሉት ሰላማዊ ግልጋሎቶች ዩራኒየም አብላልታ በማጠናቀቅ ላይ እንደሆነች በተለያዩ መድረኮች በልበ ሙሉነትና በኩራት ተናግራለች። የኑክሊር ሳይንቲስቶች እንደሚያረጋግጡት ለሰላማዊ ግልጋሎት የተዘጋጀ ዩራንየም በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ጦር መሣሪያነት ማሸጋገር ይቻላል። ማን ይሙት አሁን በነዳጅ የተንበሸበሸችው ኢራን ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ከፍተኛ ወጪና ጥበብ የሚጠይቀው የኑክሊር ኃይል አስፈልጎአት ነው ኑክሊር ኘሮግራምዋን የጀመረችው? የኢራን ዓላማ የእስራኤልን የኑክሊር ጥቃት ለመከላከልና የተለያዩ ፍላጎቶችዋን ለመሜን ለምሳሌ አሰብን ከኢትዮጵያ እጅ ለማስጣል የሚያስችላት ጉልበት ለማግኘት መሆኑ ከወዲሁ መገመት ይቻላል። አሰብ ለምሥራቁና ለመሃሉ የአገራችን ክፍሉች እጅግ ቅርብ ስለሆነች በአካባቢው የሚኖረው ህዝባችን በእስራኤልና በኢራን መሃከል የኑክሊር ግጭት ቢፈጠር ህዝባችን ለኑክሊር ልውውጡ (Nuclear exchange) ሰለባ ሆነ ማለት ነው። እስራኤልና ኢራን ጦርነት ውስጥ ባይገቡ እንኳን እስራኤል የኢራን አፍሪቃ ውስጥ መስፋፋት ለማምከን ከኢትዮጵያ ጋር የተለየና የጠበቀ ወዳጅነት ትመሰርት ይሆናል። ይህም ቢሆን ባይሽሹም ዞር አሉ ዓይነት በማያባራው በእስራኤልና በመካከለኛው ምስራቅ ንትርክ አገራችን በምንትዳዋ ትዘፈቅ?

ከጥቂት ወራት በፊት ግብፅም ለሰለማዊ ግልጋሎት የሚውል የኑክሊር ኘሮግራም መጀመርዋ በይፋ ከአስታወቀች በኋላ አሁን ደግሞ ለግንቦታው ጨረታ አውጥታለች። (ሪፖርተር ጥር 15 ቀን 2003 ገጽ 1) ከእስራኤል ጋር በካምፕ ዴቪድ የሰላም ውል የተፈራረመችው ግብፅ ኑክሊር ኃይል ለምን አስፈለጋት የሚለው



በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ ጥያቄ እንደሚጭር ግልፅ ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህ አስተያየት የተጋነነ ነው፤ በዚያ በኩል እንደሚሉት ታምሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ብልህነት ነው። የሚመጣ አደጋ የለም ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም አበው

## 1.3. ኢትዮጵያን ከኑክሊር ስጋት ለማላቀቅ ምን መደረግ አለበት

ኑክሊር መሣሪያ በሰፊው ታጥቃ እንደነበረ ይነገርላት የነበረችው ደቡብ አፍሪቃ ነፃነትዋን ስትጎናፀፈ (አፓርታይድ ሲፈርስ) ማንም ሳያስገድዳት አፍቃሪ ከኑክሊር ነፃ ቀጠና እንድትሆን በማሰብ የኑክሊር መዋቅርዋን አፈራረሰች። አሁንም አፍሪቃ ከኑክሊር መሣርያ ቀጠና ውጭ እንድትሆን ኢራን ከአፍሪቃዊ ግዛት ከቀይ ባህር ጦርዋን እንድታስወጣ የአፍሪቃ ህብረት መጠየቅ ይገባዋል። በኤርትራ አጋዥነት በአፍሪቃ ውስጥ ኢራን የጦር ሰፈር እንዲኖራት መፍቀድ ለኩሩ ኤርትራውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን አሳፋሪ ሊሆን ይገባዋል።

70% በላይ የዓለም ነዳጅ መተላለፊያ በሆነችው በቀይ ባህር የኑክሊር መሳሪያ መኖር ለመርከቦችና ለኢንተርናሽናል የባህር ትራፊክ እጅግ አደገኛ በመሆኑ በኑክሊር ቦምብ የታጠቀች ኢራን ቀይ ባህር ላይ መስፈር ለዓለም ሰላምና ፀጥታ አስጊ በመሆኑ ኢራን አሰብ ላይ ያቋቋመችው የጦር ሰፈር ዘግታ እንድትወጣ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት አስገዳጅ እርምጃ እንዲወሰድ ኬንያ፣ ቢቻል ሱዳን፣ ጅቡቲና ኢትዮጵያ ጥያቄ እንዲያቀረቡና ግፊት እንዲያደርጉ ይገባል። አፍሪቃ ከኑክሊር መሣሪያ ነፃ መሆን አለባት የሚለው መርህ በግብፅ በኩል እንዳይጣስ እነዚህ አገሮች የተባበሩት መንግሥታት ክትትል እንዲያደርግ በየጊዜው ማሳሰብ ይገባቸዋል።

ይዋልም ይደር ኢትዮጵያ ለኑክሊር ጥቃት ልትጋለጥ እንደምትችል ግልጽ እየሆነ መጥቶል። በድንበር ተሻጋሪ ወንዞችዋ፣ በምትገኝበት የጂኦግራፊ አቀማመጥዋ፣ በሶስዮ ፖለቲካ ይዘትዋ (ባህል፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፣ ታሪክ ወዘተ) ምክንያት ኢትዮጵያ በአንድ ጀምበር እንድትፈርስ የሚፈልጉና ለዚህም ሌት

ተቀን በሚሠሩ ጠላቶች ተከብባለች። ስለሆነም ኢትዮጵያ ከጥቃት ለመከላከል የሚያስችላት ከጠላቶችዋ ጋር የሚመጣጠን ትጥቅና ኃይል ማዘጋጀት፣ ከዚህ በፊት ተጀምሮ እንደነበረው በጥናት ደረጃም ቢሆን ዝግጅቱን መጀመር አለባት። ሆኖም ግን የአገር ሉዓላዊነትና ሕልውና ማስከበር የሚቻለው በአንደኛ ደረጃ ሰብአዊ መብቶች ተከብረው የሕግ የበላይነት ተረጋግጦ ሕዝቡ በመንግስት ላይ እምነት ኖሮት ሲገኝ ነው።

ኤርትራውያን ለበጎም ይሁን ለክፉ ሊበጠስ በማይችል ሰንሰለት ተፈጥሮ ከኢትዮጵያ ጋር አቆራኝቶአቸዋል።አንዳንድ ከአፍንጫቸው አርቀው ሊያስቡ የማይችሉ መሪዎች አይገነዘቡት እንደሁ እንጂ የሁለቱም መጻኢ ዕድል አንድና አንድ ነው። ኢትዮጵያውያን ከኤርትራውያን ጋር፤ ሲሆን በጥምረት አልያም በመልካም ጉርብትና በወንድማማችነትና በእህትማማችነት በመረዳዳትና በመደጋገፍ ጠላትን በጋራ በመከላከል መኖርን እንደሚመርጡ በተለያዩ ወቅቶች ለምሳሌ አንዳንድ ኤርትራውያን ኃላፊነት በጎደለው መልኩ ከኢትዮጵያ በተባረሩበት ወቅት አስመስክረዋል። ኤርትራውያን ክፉ ቀን ባጋጠማቸው ጊዜ ሁሉ ወገናቸው ወደ ሆነው ወደ ኢትዮጰያ ነው የሚሰደዱት። ይህም ሲሆን ኤርትራዊያን በኢትዮጵያውያን እግር ተተክተው ሊያዩት የሚገባ ነገር አለ። ይኸውም መቼም ቢሆን ከ 90 ሚልዮን ሕዝብ በላይ በእግር መንገድ እርቀት የባህር መግቢያና መውጫ በር ተዘግቶበት ከዘጊው ጋር በሰላም ለመኖር እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል።

ኢትዮጵያ በአሰብ ላይ ያላት ሕጋዊ መብቶች የዓለም ሕግጋትን፣ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎችን፣ የራሱ የኤርትራ ሕዝብ ውሳኔ በማጣቀስ በሌላ ወቅት በሰፊው የተተቸ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም በዚሁ በቀይ ባሕር በኩል በተደጋጋሚ መወረራችን አሰብ ለኢትዮጵያ ሕልውና ወሳኝነት እንዳላት እንደዚሁ በሌላ ወቅት ተገልጿል። እንደሁም በ1960ዎቹ መባቻ ላይ አሰብን ያስተዳድሩ የነበሩ አንድ አዛውንት ለዚሁ ጸሐፊ እንዳረጋገጡት ኢትዮጵያ የአሰብን ወደብ ለመገንባት ከሶስት ቢልዮን ዶላር በላይ ወጪ ያደረገች ሲሆን፤ አሰብ በኤርትራ እጅ ከገባች በኋላም የኢህአዴግ መንግስት ከኢትዮጵያ ወሰን አንስቶ



ወደ አሰብ ወደብ የሚያስገባ መንገድ በ56 ሚልዮን ዶላር አሠርቶ ለሻብያ እንዳስረከበ ይነገራል።

ስለዚህ የአሰብ ጉዳይ በግድ ለሁለቱም አገራት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መፈታት አለበት። እነዚህ አገሮች በሰላም እንዲኖሩ ከተፈለገ ፈቃደኛነቱ ካለ ችግሩ የሚፈታበት ብዙ መንገዶች አሉ። (I) አንዱ መንገድ ኤርትራና ኢትዮጵያ ከ1983 ዓ.ም. ማለት ኤርትራ ከመገንጠልዋ በፊት ወደነበረችበት ሁኔታ መመለስ ነው። ኤርትራውያን ይህንኑ ባያስደስታቸው ወደ ፌደሬሽን መመለስ ሌላው መፍትሔ ሊሆን ይችላል። (II) ኤርትራውያን ብቸኝነቱ ከመረጡም ሁለቱም አገሮች አሰብን በጣምራ ሉዓላዊነት (Joint Sovereignty) ይዘው አሰብን ሊያስተዳድሩ ይችላሉ። ይኸ ሁኔታ ለሰላም ሲባል እንደመፍትሔ ሊቆጠር ይችላል እንጂ የኢትዮጵያ የአሰብን ባለቤትነትን አይሽርም። ዛሬ ዴሞክራቲክ ኮንጎ የምትባለው አገር በ1884—1885 ዓ.ም. በተደረገው ኮንፈረንስ ከአንጎላ ወደ ባሕር ሊያዘልቃት የሚያስችላት መሬት እንደተሰጣት ሁሉ ኢትዮጵያም ከወሰንዋ አንስቶ ወደገነባቸው ወደ አሰብ የሚያዘልቃት ካሪዶር ሊኖራት ይገባል። ይህም የሚሆነው የወደቡ ባለቤትነት በኢትዮጵያ እጅ ሆኖ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ከሁለተኛ የዓለም ጦርነት በኋላ በሸርሳይ ስምምነት መሠረት ፖላንድ እንደዚሁ በጀርመን ሙተላለፊያ ተሰጧት ወደ ባህር ለመዝለቅ የሚያሸትላት ሙተላለፊያና ወደብ እንዲኖራት ሆኗል።

## 1.4. መደምደምያ

የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እስከተረጋጠ ድረስ የኢራን ይሁን ወይንም የሌላ ባዕዳን አገር ጦር አሰብ ላይ የሚሰፍርበት ምክንያት አይኖርም። ስለዚህ የውጭ ኀይሎች ጣልቃ ገብነት ለማስወገድ በሁለቱ አገሮች መሃከል ሰላም ኖሮ ይህንን አሳፋሪ ድህነት በአስቸኳይ እንዲቀረፍ፣ ሁለቱም አገሮች በአንድ ጀምበር ጠፍተው ቢያድሩ ደስ የሚላቸው ኀይሎች በሃፍረት እንዲሟሸሹ፣ ለዚህ ሁሉ ቁልፍ አሰብን ወደ ባለቤቱ ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ነው፤ ወይንም በአንድ ወቅት አቶ ኢሣያስ እንዳሉት "የኢትዮጵያና የኤርትራ ወሰን በህዋው (Space) ላይ ነው ያሉትን ተከትሎ በሁለቱም መሃከል መኖር የማይገባው ሰው ሠራሽ የድንበር

መሰመር ማጥፋት ነው። ምናልባት ፌዴሬሽን ወይንም ውህደት በቅርብ ጊዜ እይታ ሕልመኛነት ነው ብሎ መፈረጅ ይቻል ይሆናል። ሆኖም ግን ማንኛውም ትልቅ ሃሳብ ከሕልም ይጀምራል። በመጨረሻም ለምንን በአሜሪካ በኢትዮጵያውያንና በኤርትራውያን የወዳጅነት መድረክን የሚደረገው ውይይት ይበል የሚያሰኝ ነው። አዘጋጆችንም በእርቀ አሰተዋይነታቸው ሊደነቁ ይገባል።



## 2. የባህር በር መብትና የፌዴራሉ ምክር ቤቶች ኃላፊነት[208]

የአፋር ሕዝብ አንድነትና የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋትን በተመለከተ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ችግሩንና መፍትሔውን በመጠቆም ያለተፈነቀለ ድንጋይ ያልተማሰ ሥር የለም ማለት ይቻላል። ምናልባትም እንደ የኢትዮጵያ "የባህር በር ይገባኛል" ጥያቄን ያህል፣ ታማኝነታቸው ወዴት እንደሆነ በውል ማወቅ ካዳገቱት ከአንዳንድ የኢሕአደግ ካድሬዎች በስተቀር፣ ሕዝቡ እንዲህ በአንድ አሳብና መፍትሔ የተስማማበትና የደመደመበት ኢትዮጵያዊ ጉዳይ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ስለዚህ የኢትዮጵያን ልማትና ሕልውና የቅንጣት ያህል ጉዳያቸው ባልሆኑ የውጭ አካሎች አደራዳሪነትና ውሳኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐት ከስሌት ሳያስገባ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ የሚፈረም የባህር በር መብትን የመያስከብር ስምምነት የተጻፈበት ወረቀት ያህል ዋጋ አይኖረውም። ጉዳዩም በአቶ መለሰና በአቶ ኢሣያስ ፈርማና አቅፍቅፍ የሚዘጋ ነገር አለመሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጾአል።

የዚህ የዛሬው አነስተኛ መጣጥፍ ዓላማ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ጉደይ በአንድ ወቅት የሚጋጋም በሌላው ጊዜ ደግሞ ደብዛው የሚጠፋ ጉዳይ መሆን እንደሌለበት ክርስቲያንና ሙስሊም ተስፋ አይቆርጥምና ትንሽ ያለችዋ አንድ የተስፋ ለወዳፊትም ለመጠቆምም ነው። በተገኘው ዓለም አቀፍ መድረኮች በሚደረጉ ውይይታች ሁሉ የሚነሳ ጉዳይ መሆን አለበት። ጉዳዩ በዓመት በሁለት ዓመት ወይንም በእኛ ዕድሜ ባይፈታ ለልጆቻችን መተላለፍ ይኖርበታል። የአገር ጥቅም ዛላቂ በዓመት በአሥር ዓመት አይሰላም፣ ዘላለማዊ ነው። አንድ ሕዝብ በአንድነት በእውነተኛና ፍትሐዊ በሆነ ዓላማ አምኖ ለዓላማው

[208] በዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ተጽፎ ሐምሌ 9 ቀን 1993 ዓ.ም ሀብረት ጋዜጣ ውስጥ ከወጣ ጽሁፉ የተወሰደ

በኬታማነት በጽናት ከታገለ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ምንም አይሳነውም። የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ደግሞ ዓለም የተስማማበት ፍትሐዊ ጥያቄ ነው። በአሁኑ ወቅት ዋናው ነገር ጉዳዩ ጊዜ እስኪፈታው እረግቶ እንዳይቀር ማንቀሳቀስ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ተግባር ነው። ይዋል ይደር እንጂ ጊዜው ሲደርስ ቦታውን የማይለቅ የለም። ኢሕአዴግም ቦታን ለቅቆ ውሉ አድሮ በታሪክ በሚገመገምበት ጊዜ ካለማቸውና ካጠፉቸው ጉዳዮች ሁሉ ገዝፎ የሚታየው አገሪቱን በጉሣ መከፋፈሉ አይደለም። ይኸ በጊዜው የሚታረም ጉዳይ ነው። የአገሪቱም አንዱን ክፍል ማስገንጠሉም አይደለም። ይኸም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ኤርትራውያን ከፍቶናል ከእናንተ ጋር አንኖርም ካሉም የአንድ ቤተሰብ መነጣጠል እንደሚያሳዝን ሁሉ ቢያሳዝነንም እንቀበለዋለን። ሆኖም ኤርትራውያን መቼም ቢሆን በኢትዮጵያዊነታቸው እስከአመኑ ድረስ ማንም የኢትዮጵያዊነት ዜግነታቸውን ሊነፍጋቸው አይችልም።

ከእነዚህ የኢሕአዴግ ድርጊቶች ሁሉ ገዝፎ የሚታየው በእኔ ግምት ለዝንተ ዐለም የኢትዮጵያ የባህር በር እንዲዘጋ መስማማቱ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድን መሪ አስተዳደር ያደረሰው ጥፋትም ሆነ ያመጣው ልማት ብዙ ቅጾች (Volumes) ሊጻፍበት በሚችል በአንድ ዐረፍተ ነገር አጠቃልሎ የማስቀመጥ ችሎታ አለው። ከልጅ ኢያሱ አንስቶ እስከ ዛሬ ያለው መንግሥት ሕዝቡ ጉልተው የሚታዩትን አንዱን ድርጊት በመጥቀስ ያጠቃልለዋል።

በኢያሱ ዳቦ ነው ትራሱ
በዘውዲቱ ተደፋ ሌማቱ
በተፈሪ ጠፋ ፍርፋሪ
በመንግሥቱ እሬሣ ጉትቱ
በመለስ አገር ተቈረሰ

ይኸ እንግዲህ የኢሕአዲግ የታሪክ ቅሪት (Historical Legacy) ሆኖ ሊኖር ነው። ሆኖም ግን ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ነውና ኢሕአዲግ ከዚህ የታሪክ ወቀሳ አሁንም ሊድን ይችላል። እኛ ግን "አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱትም አይሰማም"



ነውና ከእንግዲህ ለኢሕአዲግ መንግሥት የሥራ አስፈጻሚው ክፍል የምንለው የለንም።

ለሕግና አውጪው አካል ግን የምንለው ይኖረናል። በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት የበገኑት ኢትዮጵያውያን ሳንቃቸው እስኪሰነጠቅ በመጮሃቸው የተረፋቸው ነገር ቢኖር በሻዕቢያ ዓላማ አቀንቃኝነት፣ በጦረኛነትና በተስፋፊነት መፈረጅ ነው። ይኸ ግን የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚችሉትን ሁሉ ከማድረግ የትግል ክንዳቸውን ሊያዝል አይችልም። አጼ ሚኒሊክ ከጣልያኖች ጋር የተፈራረሙአቸው የወሰን መካለል ውሎች ውድቅ እንደሆኑ አሰብና አካባቢው የኢትዮጵያ የባህር በር የአፋሮች መሬት መሆኑን ከቶም ምንም ነገር የማይሳነው ኢሕአዲግ ቀርቶ በስም ሊጠቀሱ የማይችሉ የውጭ አገር የፖለቲካ ጠበብትና አምባሳደሮች ኢሕአዲግ የአገሩ የባህር በር መዘጋት እንዴት እሺ ብሎ እንደተቀበለ ያስገርማቸዋል። የባህር በር በተዘጋበት ጊዜ ለመቃወም አቅም አይፈቅድም ነበር ቢባል እንኳን ጉዳዩን አንጠልጥሎ "እስቲ ተከድኖ ይብሰል" ብሎ ለአመቺ ቀን ማቆየት የአባት ነበር።

አገርን አስገንጥሎ የባህር በርን አዘግቶ ለሉዐላዊነት ቆሜአለሁ ሲባል "ድንቄም ሉዐላዊነት" ያሰኛል። አገራዊ ሉዐላዊነት ያስከበረውስ፣ ኢትዮጵያን ከውርደት መንዝዘ ያወጣውስ፣ ክብራችንን በደሙ የዋጀው፣ ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን ነው። ከዚህ ሌላ ጀግና ደግሞ አናውቅም።

የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ ለአንዴና ለሁሌም እንዳይዘጋ የመጨረሻው መንጠልጠያ ኢሕአዴግ ሲያመቸው ጥካፋ ሊቸግረው በጭልፋ የሚዝቀው ሕገ መንግሥቱ ሊሆን ይችላል። ሟቹ የግብጽ ፕሬዝደንት ጋማል አብደል ናሥር "ግብጽን የሚጠቅም ከሆነ ከጂኒም ጋር እንኳን እደራደራለሁ" እንዳሉ ሁሉ ለአገራችንና ከጂኒ ጋር ባንዳራዳርም ለሕዝባችን ከጠቀመ በተደጋጋሚ በመንግሥት በተጣሰው ሕገ መንግሥት ከመጠቀም አናመነታም።

የኢትዮጵያ የባህር በር ለአንዴና ለሁሌም እንዳይዘጋ የመጨረሻው ኃላፊነት የወደቀው በተወካዮች ምክር ቤትና በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ላይ ነው። ፕሬዝ ሕሬራዊ ምክር ቤት

ብሔራዊ እንደመሆኑ መጠን የአገርና የሕዝብን ጥቅም ማስጠበቅ እንጂ የአንድን ፓርቲ ጥቅምና ፍላጎት ኩሊ መሆን የለበትም። አላፊነቱም በሙስና፣ በአምቻና ጋብቻ፣ በፓርቲ ወያኔነት፣ በወንዝ ልጅነት የሚዘረፈው ከውጭ የሚገኘው ብድር ከማጽደቅ የላቀ ነው። የኢትዮጵያ የባህር በር ከማስከበር የበለጠ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚነካ ጉዳይ መቼም ቢሆን በአጀንዳነት ሊቀርብለት አይችልም።

የሕግ መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንኡስ አንቀጽ 12 እና 18 የሕግ አስፈጻሚው ክፍል ማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ ካቢኔው የሚዋዋሉአቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች የማጽደቅ ወይንም ያለማጽደቅ ሥልጣን ለተወካዮች ምክር ቤት ሰጥቶአል። ምክር ቤቱ ከኤርትራ ጋር የሚያደርገው ስምምነት ሰላም የሚመሠርቱና ምንም የማያጠራጥረው ወሰኖችን የሚከልለውን ክፍል ብቻ አጽድቆ አሰብን አካባቢውን የተመለከተውን ክፍል ላለማጽደቅ ምንም የሚከለክለው ነገር የለም። ስምምነቱ በተወካዮች ምክር ቤት ካልጸደቀ ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

ከዚህ ኢትዮጵያን እግር ተወርች ከሚቀፈድደው ስምምነት ማምለጫ ሌላም ሕገ መንግሥታዊ መንገድ አለ። የፌደሬሽኑ ምክር ቤት በከፊል ሕግ አውጪ ሲሆን በከፊል ደግሞ ፍርድ ሰጪም ነው። ሕገ መንግሥቱ በምሁራን ካስነቀፉት ጉዳዮች አንዱ ቢሆንም ለዓላማችን ስኬታማነት ከጠቀመው እሰዬው ነው።

በሕግ መንግሥቱ አንቀጽ 62 (1) መሠረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥቱን የመተርጐም መብት ተሰጥቶታል። በአንዳንድ አገሮች ለምሳሌ ያህል በአሜሪካ እንዲህ ዓይነቱ ሥልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ነው። የፌዴራል ሕግ መንግሥት ሕግን በመተርጐም ሥልጣኑ ማንኛውም የሕግ አስፈጻሚው ክፍል የገባው ውል ወይንም ስምምነት እንዲሁም የመንግሥት አካላትም ሆኑ የተወካዮች ምክር ቤት ያወጡዋቸው ሕጐች ከሕገ መንግሥቱ ጋር የማይጣጣሙ መስሎ ከታየው ውድቅ አድርጎ ሊሠርዛቸው እንደሚችል ተደንግጓል። ሕገ መንግሥቱ ለሕግ አስፈጻሚው ክፍል ማለትም ለጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ ለካቢኔአቸው



የተለያዩ ሥልጣን ሲያድላቸው የኢትዮጵያን ግዛት ቆርሶ ለሌላ የመስጠት ሥልጣን እንዳላቸው ግን አይደነግግም። የኢሕአዴግ መንግሥት ማለት፣የሕግ አስፈጻሚው አካል ከኤርትራ ጋር በሚፈራረመው ስምምነት የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት የነበረችው አሰብን አሳልፎ ከሰጠ ድርጊቱ ከሥልጣኑ በላይ (Ultra Vires) ስለሆነ ምክር ቤቱ ስምምነቱን በሙሉም ሆነ በከፊል ሊሰርዘው ይችላል።

የደሞክራሲያዊ አስተዳደር በሰፈነባቸው አገሮች ብሔራዊ ሸንጐ የማያምንበት፣ የሕግ አስፈጻሚው ክፍል የተዋዋላቸው ስምምነቶች አለማጽዳቅ ወይንም መሻር በጣም የተለመደ አሠራር ነው። በቅርብ ጊዜ ፕሬዝዳንት ክሊንተን የአየር ብክለትን ለመቀነስ ከሌሎች የዓለም መንግሥታት ጋር በቶኪዮ ጃፓን የተፈራረሙት ስምምነት ብሔራዊው ሸንጐ (Congress) ስለአላጸደቀው በፕሬዝዳንት ክሊንተን እግር የተተኩ ፕሬዝዳንት ቡሽ ሰርዘውታል። እንዲሁም የአሜሪካው ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተለያዩ ወቅቶች ፕሬዝዳንቱ የወሰኑአቸው በርካታ ውሳኔዎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ብሔራዊ ሸንጐ ያወጣቸው አያሌ ሕጐችን ሕገ መንግሥቱን ይዳፈራሉ በማለት ውድቅ አድርጓአቸዋል።

እዚህ ላይ የእኛዎቹስ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባላት እንዲህ ዓይነት ወኔኖሮአቸው የአገርና የሕዝብ ጥቅም ለፓርቲአቸው ካላቸው ታማኝነት ያስቀድማሉ ወይ? አይታወቅም። ወላድ በድባብ ትሂድና ኢትዮጵያ ፈተና በገጠማት ጊዜ ሁሉ የቁርጥ ቀን ልጆችዋ ከደዋት አታውቅም። ጣልያኖች ካምፕ እየገባ የኢጣልያንን ጦር ስልሉ ለአጼ ምኒልክ መረጃ በማቅረብ ለአድዋ ድል የተባ አስዋጽኦ ካደረገው ከአውአሎም አንስቶ በጊዜአችንም የነፍስ ገዳዩ ደርግ ታንክ በድንጋይ የተጋፈጡት ወጣቶች የወለደች አገር ዛሬ መክናለች የምንልበት ምክንያት የለም። የሕዝብ ምክር ቤት አባሎች በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመንም ሆነ በደርግ ለአለው ኃይል ሳያጐበድዱ ሕዝብና አገር ይበልጥብናል ያሉበት ጊዜያትም አሉ።

ኢትዮጵያ በዘጠኝ ወደቦች የመጠቀም ዕድል አላት እየተባለ ጥያቄአችን ፈር ለማስለቀቅ ይለፈፍ የነበረው ዛሬ አይደገምም። ምክንያቱም ከአሰብ መዘጋት በኋላ ጀባ ባያደርጉም ትናንሽ

የጉሮሮ ማነቆዎች ሙከራ እንደተደረገብን፣ እነዚህ ትናንሽ የጉሮሮ ማነቆች በውጭ ንግዳችን ላይ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ በጉልህ በመታየቱ ነው። እነዚህ ወደቦች በከፋም በደጉም ወቅት እንዳሻን እንጠቀምባቸዋለን የሚሉ ስለአካባቢው ጂኦፖለቲክስ ስለአገራችን ምድራዊ አቀማመጥ፣ ስለ ታሪክ ሂደታችን ግንዛቤ የሌላቸውና ሰፈራችን (የአፍሪቃ ቀንድ) እጅግ አደገኛ አካባቢ መሆኑን ያልተረዱ የዋሃን ናቸው። በአፍሪቃ ምናልባትም ከአብዛኛው የዓለም አገሮች ከእኛ በላይ ጦር የተሰበቀበት አገር የለም። እኛ ግን በረዥሙ ታሪካችን አንድም ቀን ድምበር ተሻግረን የሰውን አገር ወርረን የያዝንበት ጊዜ የለም በየብስ የተከበቡ የበለጸጉ አገሮች ብዙ ናቸው የሚለውን ትተን ብናውቅበት ይበጀል። የአሰብ ወደ ኢትዮጵያ መቃጠፍ የባህር በር ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የሉዐላዊነት የማስከበርም አላፊነት መሆኑ መዘንጋት የለበትም።





## 3. <u>ግልፅ ደብዳቤ</u>

ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር
<u>አዲስ አበባ</u>

ክቡር ሆይ

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል ሲካሄድ የቆየው አሰቃቂ ጦርነት በመቆሙና ወደ ሰላም አቅጣጫ ዝግመት በመጀመሩ፣ ካልነኩት የማይነካው ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ መደሰቱን አልጠራጠርም። የጦርነቱ መቆም ተከትሎ በዲፕሎማሲው መስክ የሚደረገው ትግል እጅግ አስተዋይነትና ጥንካሬ እንደሚጠይቅ ግልፅ ሲሆን ፣ ይህንን ለተገነዘበው አላፊነቱ እጅግ ከባድ ነው። ምክንያቱም የድርድሩ ውጤት ለብዙ ተከታታይ ትውልድ የሚተርፍ ክፋም ሆነ በጎ አሻራ ጥሎ ያልፋልና ። የዚህም ድርድር ውጤት ጦርነቱ ለምን ተዋጋን? የደረሰብን ኪሳራ ምንድን ነው?፣ የብርቅዬ ወንድሞቻችንና ልጆቻችን ክቡር ህይወት ገብረን ያገኘነው ምንድን ነው? የከፈልነውስ መስዋእትነት ካገኘነው ማካካሻ ጋር ይመጣጠናል ወይ ብሎ ስሌት ሲደረግ መልስ የሚገኘው ከዚሁ ድርድር የመጨረሻ ውጤት ነው።

ሚልዮን ጦር ቢያሰልፉ ሀውልት ቢያንፁ እንደ መብረቅ ቢፈሩ ሁሉም ጊዜውን ጠብቆ አላፊ ነው። ከአፈር ገፊው ገበሬ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚህ ዓለም ሳያልፍ በምን እታወሳለሁ ብሎ እራሱን መጠየቁ አይቀርም። እርስዎም እንደ ጠቅላይ ሚኒስትርነትዎ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ አመራሬ መንግስቴ በምን አይነት ይታወሳል፣ በምንስ ይመሰገናል፣ በምንስ ይወቀሳል

ብለው መጠየቅ ያለ ነው። ታሪክ አድልዎ አያውቅምና ሁሉም እንደሰራው ሞገስም ሆነ ወቀሳ መለገሱ ደግሞ አይቀርም።

ለዘላለሚቷ አገራቸው ደህንነትና ክብር ለሕዝባቸው ነጻነትና ህልውና አንገታቸውን ለሰይፍ ደረታቸውን ለአረር የሰጡ መሪዎች ፍለጋ እሩቅ አንሄድም። በቤታችን አሉ። ባንጻሩ ደግሞ አውቀው በድፍረትም ሆነ ሳያውቁ በስህተት አገራቸውን በእጅጉ የጐዱ መሪዎችም ኖረውናል። የወቅቱ የኢትዮጵያ ባለስልጣኖችም ከእነዚህ አማራጮች አንዱን ማንሳት ይኖርባቸዋል። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የእርሶም መንግስት ከሚታወቅበትና ከሚገመገምበት ከዋነኛዎቹ ሚዛኖች አንዱ "አሰብን ለሌላ አስረክቦ ኢትዮጵያን ለዝንተ አለም ወደብ አልባ አድርጎ በየብስ የከረቸመ" ወይንም ደግሞ "በህግ በታሪክ የኢትዮጵያ አንጡራ ሃብት የሆነችዋን አሰብን በረቀቀ ዲፕሎማሲያዊ ትግል አስገኝቶ ለኢትዩጵያ ባህር በር ዋርዲያነት የቆመ" መንግስት ተብሎ ነው።ለማንም ቢሆን ሚዛን የሚደፋውም ምርጫ ሁለተኛው ለመሆኑ አያጠራጥርም። መንግስትዎም የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ለማስከበር የወሰደው ቁርጠኛ እርምጃ ማስረጃ ከሆነ ምርጫው የመጀመሪያው ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ። አለዚያም የኢትዮጵያ የባህር በር ቢዘጋ ኢህአዲግ እንዲህ አይነት ከባድ ኃላፊነት እንዴት ሊሸከም እንደሚችል ሲያስቡት እንኳን ይከብዳል። በኢትዩጵያ የተወከሉት ተደራዳሪዎችም የዲፕሎማሲያዊ ጥበብ መለኪያው ይኸው አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ ነው።

## ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ትግል ሰልሎ ኢሕአዲግ ወኔ ከድቶት ይህንን ሁሉቀመሳፍርት መስዋእትነት ለከፈለው ፣ ጦር መጣ ባሉት ጊዜ ለደቂቃ ሳያመነታ ጥሪውን አክብሮ ቀፎው እንደተነካ ንብ ተምሞ ለወጣው ለደጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ቢያንስ አንድ ሊያደርጉለት የሚችሉት ነገር አለ። መንግስትዎም አሰብን የኢትዮጵያ አንጡራ ሃብት ሊያደርግ ካልፈለገ ወይንም ካልቻለ ቢያንስ ቢያንስ ድንበር በሚከለልበት ወቅት የአሰብን ጉዳይ ከድርድሩ መዝዞ አውጥቶ "አልስማማም" ከማለት የሚያግደው ነገር ያለ አይመስለኝም። ሕጋዊነት እየተጠበቀ



ከዚያም አልፎ መሄድ ይቻለል። አለም አቀፍ ሕግ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ ይፈቱ ፣ ጦርነት ከፈነዳም ይቁም ይላል እንጂ የግድ ድንበር ተካለል ፣ የወዳጅነት ስምምነት ፈርም ፣ የንግድ ልውውጥ ውል ተዋዋል አይልም። መንግስትዎ የአሰብን ጉዳይ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እስኪፈታ ድረስ ድንበር አልካለልም እንኳን ቢል የአለም አቀፍ ህግን ጣሰ ማለት አይቻልም። በስምምነቱ አሰብን በተመለከተ "አልተስማማሁም" የሚል ክፍተት ቢተው የኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ኩብደት የሚታያቸውና የአገርና የህዝብ ፍቅር ከሁሉ በላይ የሚያስበልጡ መሪዎች ተፈጥረው ኢትዮጵያ የተከበረችና ጠንካራ አገር ከሆነች የባህር በር መብቷን ልታስከብር ትችል ይሆናል። ከአጼ ቴዎድሮስ ጀምሮ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክና አጼ ኃይለ ሥላሴ የደከሙለት በመጨረሻም በአጼ ኃይለ ስላሴ ዘመን እልባት ያገኘው የባህር በር ጉዳይ ዛሬ በችኮላ የአለም ሕብረተሰብ ዋስትናነት በተንተራሰ ውል ኢሕአዲግ የአሰብ ጥያቄ ቢለቅ የመጪው ትውልዶች መብት ከእግራቸው ስር ሰረቀ ማለት ነው።አሰብ ወደ ኤርትራ ሲካለል ነው የኢትዩጵያ የባህር በር እንዳይዘጋ የተዋደቁት የኢትዩጵያ ጀግኖች አፈሩ የሚከብዳቸው።

## ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

አሰብና የኢሕአዲግ አቋም በተመለከተ አንዳንድ ያልገቡን ነገሮች አሉ። አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ስለሆነች ለኢትዮጵያ ትገባለች የሚሉ የተባበሩት መንግስታት ማህበር፣ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ ፣ የራሺያ፣ የራስዋ የቅኝ ገዢ የጣልያን ዶክመንቶችና (በተለያዩ ፅሁፎች ጠቅሻቸዋለሁ) የጽሁፍ ማስረጃችዎች ዛሬ በየመዛግብት ቤቱ እያሉ ኢሕአዲግ በእነዚህ ዶክመንቶች በመንተራስ የአሰብ የባቤትነት ጥያቄ ለምን ማንሳት እንደማይፈልግ እንቆቅልሽ ሆኖብናል። ምናልባት እኛ ተራ ኢትዮጵያውያን የማናውቀውና በውስጡ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ነገር ካለ በከንቱ እንዳንባጅ ቢነገረን መልካም ነበር።

ኢትዮጵያ በጦርነቱ አሸንፋ በአካባቢዋ ባለው የሃይል ሚዛን ስትሰላ የተባ አቅም እንዳላት ለአለም ሁሉ አስረግጣለች። ሃያላን መንግስታትም ይህ ከፍተኛ ስትራተጂካል ጥቅም ያላት የነዳች

መተሳሰሬያና ከፍተኛ የንግድ መስመር ደህንነትና ዋስትና ልታረጋግጥ የምትችለው ቢያንስ በአፍሪካ ዳርቻ በኩል ባለው ከኤርትራ ይልቅ ኢትዮጵያ መሆንዋን አረጋግጠዋል። ይህም ሆኖ ግን "ሃያልነታችሁን አሳምናችሁናልና ቀይ ባህር ወይንም አሰብን እንኩ" የሚለን የለም። አንዳንዱ ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር አቋርጦ በቤታችን ያለው የአባይን ውሃ የእኔ ነው ሲል፣ እኛ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን የአፋሮች አገር ለአፋሮች ብሎም ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ይመለስ ብንል ምን ያስነውራል።

በጦርነት ማሸነፍ በዲፕሎማሲውም ዘርፍ ይሁን በሕግ ብዙ መብቶችን ያጎናጽፋል። ለምሳሌ በያዙት መሬት ላይ መርጋት የተወራረው ደህንነት (ሴኩሪቲ) የሚያረጋግጠው የመሬት መንሸራሸር ማድረግ፣ ሌሎችም፣ ሌሎችም። ከዚህ ጋር ተያይዞ ታድያ አሁንም ብዙዎቻችን ያልገባን ነገር አለ። በዘልማድ እንደሚነገረውና በሕግም ዋጋ ያለው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰማንያ ከመቶ "ይዞታ" መሆኑ ከታወቀ የኢትዮጵያ ጦር ወደ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ወደ ኤርትራ ዘልቆ የኤርትራ ግዛት መሆንዋ ምንም የማያከራክረው ተሰነይን ሲይዝ ብዙዎቻችን አንጡራ ሃብታችን ነች የምንላትን አሰብን 20 ኪሎ ሜትር ሲቀር ለምን ተዋት? አሁንም ለኢትዮጵያ ጥቅም ነው ከተባለ ዜጎች ብናውቀው መልካም ነበር።

ኢትዮጵያን የባህር በር አሳጥቶ ዙርያውን በየብስ ማጠር በኢትዮጵያ ላይ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት በእኔ አቅም ተዘርዝሮ አያልቅም። ኢትዮጵያን ከዚህ ቁልፍ ከሆነው ከቀይ ባህር አካባቢ ለማግለል የተደረጉ እጅግ ብዙ ደባዎች ኢትዮጵያ ከጦርነት አዙሪት እንዳትወጣ ከሆኑት ምክንያቶች አንዷና ነው። ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር "ጨዋታ" ከወጣች የምትናገረው የማይደመጥላት የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዋ ሽባ ሆኖ ተሰሚነት የሌላት አገር ትሆናለች። ይኸ ደግሞ በኢኮኖሚውና በጸጥታው ሊከተሉ የሚችሉ ከፍተኛ አደጋዎች ሳይጠቀሱ ነው፡

## ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

የአሰብን ወደብ በተመለከተ መንግስትዎ የተከተለው አቅጣጫ ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ለመጠቀም ብቻ የሚያስችላትን መብት ማረጋገጥ ይመስላል። ለዚህ ማንንም አናመሰግንም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በአሰብ በኩል ሸቀጣሸቀጥዋን ለማስተላለፍ ብትፈልግ ኤርትራ የምታስቀምጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎን ክፍያዎችንም እስካጠናቀቀች ድረስ ማንም ሊከለክላት አይችልም። በዛሬ ጊዜ በየብስ የተከበቡ አገሮች አንዳንድ ግዴታዎችን እስካሟሉ ድረስ ማንም የባህር በር ሊዘጋባቸው እንደማይችል ብዙ ዓለም አቀፍ ሕጎች ይደነግጋሉ። በዚህ አይነት የባህር በሩ ቢዘጋ አቅም ካላቸው በጦር ሃይል እንኳን የተዘጋውን የባህር በር አስከፍተው መጠቀም ይችላሉ። ኢትዮጵያውያን ከመነሻው ያለንን ጥያቄ ሸቀጣሸቀጥ የማስተላለፍ መብት ይጠበቅልን ሳይሆን እኛ የምንለው የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአፋሮች መኖርያ የሆነው የሉሲ (የድንቅነሽ) አገር አሰብ ይመለስልን ነው። በወደብ የመጠቀሙ መብት ብቻ ከመቶ አምሣ ዓመታት በፊት ለገናናው ንጉሰ ነገሥት ለአፄ ዮሐንስ አራተኛው አጥጋቢ እንዳልነበረ ዛሬ ለእኛም አጥጋቢ አይደለም። (ምጽዋ በቱርኮች ወኪሎች በግብጾች እጅ በነበረችበት ጊዜ በእንግሊዞች ማግባባት ኢትዮጵያ በወደቡ በነፃ ትጠቀም ነበር)

ኢሕአዴግ ደርግን ከመደምሰሱ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሕይወታቸውን ገብረው ለኤርትራ ነፃነት ከፍተኛ ትግል አካሂደው ኤርትራ ነፃ ወጥታለች። የኢትዮጵያ ህዝብ በሚያውቀው ግን ሕወሓት ከኤርትራ ጋር ድንበር ተካልሎ የኤርትራ በወርዱ ይህን ያህል ኪሎ ሜትር ነው፣ ቁመቱ ደግሞ ይህን ያህል ነው ያለበት ጊዜ የለም ። ምናልባት ሕወሓት በትግሉ ዘመን ለሻቢያ አሰብ ከኤርትራ ጋር እንድትጠቃለል ያደረገው ስምምነት ሊኖር ይችል ይሆናል። ይሆናል ብንል እንኳን ሻቢያ በኢትዮጵያ ላይ ብሎም በሕወሓት ላይ የጥቃት ጦርነት (aggressive war) ከፍቶ የጦር ወንጀል ፈጽሞአል። በሌላው አገር ላይ የጥቃት ጦርነት ከፍቶ ወረራ መፈፀም ደግሞ በኑራምበርግ ፍርድ ቤት ውሳኔዎችና እ.ኤ.አ በ1998 ዓ.ም የአለም ወንጀል ፍርድ ቤት ለማቋቋም በተፈረመው ስምምነት (treaty) መሠረት የጦር ወንጀል መሆኑ በማያዳግም መልኩ ተረጋግጧል። በዚህ ሁኔታ ሕወሓት በገባው ውልም ሆነ በሰጠው ቃል የመፅናት ሕጋዊም ሆነ ሞራላዊ ግዴታ የለበትም። ስለዚህ ሕወሓትም ሆነ ኢሕአዴግ እንዲህ ዓይነቱ ግዴታዎች ገብተውም

ቢሆን እንኳን አንድ የፖለቲካ ድርጅት ቀርቶ የእርሶም መንግስት ሆነ የተወካዮች ምክር ቤት አንዲት ጋት የኢትዮጵያ መሬት ቁርሶ ለማንም የመስጠት መብት እንደሌላቸው እርስዎም አይስቱትም።

ግጭቱ "ሀ" ብሎ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የኤርትራውያን ፍላጎት ድንበር መካለል መሆኑን አልሸሸጉም። ደንበር መካለሉ ለወደፊት ግጭት እንደማይነሳ ባያረጋግጥም ግጭት በድጋሚ እንዳይነሳ በእርግጥ ከተፈለገ የድንበር መካለል ፍትሃዊ በሆነ መልኩ መከናወን አለበት። አሰብ በባለቤትነት ወደ ኢትዮጵያ እስካልተካለለ ድረስ ለግጭት ምክንያት የሚሆነው ዋነኛው ጉዳይ የእሳት ረመጥ ሆኖ ተዳፍኖ ይቆያል እንጂ ጠፋ ማለት አይደለም።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር

ድንበር መካለሉ ለኤርትራውያን እንጂ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን እጅግም አስፈላጊ እንዳልሆነ የሚያጡት ሐይመስለኝም። ለክቡርነትዎ በትሕትና ላሳስብ የምፈልገው ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የጦርነቱም ሆነ የድርድሩ አልፋና ኦሜጋ ድንበር መካለል አይደለም፤ የኢትዮጵያ የባህር በር <u>ባለቤትነትን</u> ማረጋገጥ እንጂ። የኢትዮጵያ ህዝብ የባህር በር ባለቤትነት ሉአላዊነት ከማስከበሩ አሳንሶ አያየውም። እንደ መራሄ መንግስትነትዎ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ማስከበር ካለብዎት ኃላፊነት የአሰብ የባህር በር ወደ ኢትዮጵያ የማጠቃለል ኃላፊነት ትልቁ ነው። ሆኖም ግን መንግስትዎ ወይንም ድርጅትዎ በአብዛኛዎቻችን ግምት የኢትዮጵያ መጻኢ እድል ወሳኝ የሆነው የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ አምኖበት ሊታገል ካልፈለገ "ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጣል" አይነት ስለሆነ ፍርዱን ለታሪክ ከመተው ሌላ ለአሁኑ ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ያዕቆብ ኃይለ ማርያም



## 4. <u>Border demarcation with Eritrea and the Question of Assab</u>
## <u>By Dr. Yacob H. Mariam</u>
## <u>November 18, 2007</u>[207*]

We heard the disturbing news recently that Ethiopian authorities are poised to sign a border delimitation and demarcation agreement based on three treaties Emperor Menelik signed with Italian colonial expansionists, affirming forever Eritrea's dominion over Assab – an Ethiopian sovereign territory and its natural outlet to the sea. The negotiations between the Ethiopian and Ertirian anthorities on border delimitation and demarcation have been conducted in such secrecy and stealth that would put American radar evading fighter plane to shame.

Before we gathered our breath, the EPRDF signed with Eritrea the most infamous treaty Ethiopia has ever been a party to. In quick succession the EPRDF submitted to arbitration at the Hague and the Arbitral

* This article originally appeared in the pro-government <u>Reporter</u> newspaper on January 9, 2002, Addis Ababa. Dr. Yacob Haile-Mariam was Department Head and Associate Professor of Business Law and International Management at Norfolk State University. The Ethiopian native was also a Senior Trial Attorney at the UN International Criminal Tribunal for Rwanda and later Senior Legal Advisor at the UN, Cameroon and Nigeria Mixed Commission. He resigned his post at the UN and ran for Parliament where he was elected by a landslide. Dr. Yacob later became one of the leaders of the popular Coalition for Unity and Democracy (CUD) opposition party, whose overwhelming victory at the rigged 2005 elections led to the arrest of CUD leaders by the Zenawi regime. He and his colleagues were released after 21 months in prison over what US congressman Donald payne described as the "Crime of being elected by the people."

Commission handed down its decision in a matter of months.

With the signature of a border agreement Eritrea becomes a state in earnest, which heretofore was only a concept, an idea or a stretch of some land north of the Ethiopian territory of Tigray. This agreement puts Eritrea on the world map and wrongly awards it Assab as its indisputable territory. Next to the Prime Minister's letter to the OAU and the UN urging them to grant recognition to the former Ethiopian breakaway province, this agreement is the most important step in the long struggle of the TPLF leadership in its role as a midwife in the birth of the Eritrean State.

It was in the eleventh hour that the Ethiopian Minister of Foreign Affaris broached the subject on the border demarcation where in a long winded interview where he said sweet nothing, he claimed that Ethiopia was awarded some territories by the Border Commission. He avoided like a plague apparently in a pere-arranged agreement with the "interviewer" – the most important issue in the boarder demarcation; namely Ethiopia's right of access to the sea through the port of Assab and the right of self-determination of the Red Sea Afars.

Without discussing Assab, the Foreign Ministr's interview was much ado about nothing. Few things in recent memory have gripped the imagination and anxiety of the Ethiopian people as the frightening prospect of losing Assab and being landlocked. No Ethiopian issue in recent memory has galvanized the otherwise fractious Ethiopian intellectuals with such unprecedented unanimity.

Yet the Minister of Foreign Affairs had nothing to say about Assab and Ethiopia's right of access to the



sea. Whatever anybody says, however, the question of Assab is not going to be put to rest by mere signatures of their "Excellencies" Ato Meles and Mr. Isayas followed by the obligatory bear hug. It would be belaboring the obvious to dwell on the fact that borders are sacrosanct for Ethiopians. Need we make head-counts of lives lost at the Welwell, Dogali, the Ogaden, Badme and innumerable other theatres of war to show what the sanctity of borders means to Ethiopians?

For most Ethiopians, border demarcation with Eritrea is not whether Eritrea has made an incursion of a kilometer here or a kilometer there-though that is important too. Border demarcation with Eritrea for most Ethiopians is nothing more or nothing less than ensuring Ethiopia's right of access to the sea through its own port of Assab, period.

After WW II, recognizing Ethiopia's right of access to the sea, the 5- nation UN mandated commission that convened to come up with measures for the disposition of Eritrea has underlined its recommendation by clearly stating, that "Taking into account in particular Ethiopia's legitimate need for adequate access to the sea that Ethiopia and Eritrea should federate under the Ethiopian Crown." Furthermore, in its recommendation, the Commission had warned, "The creation of a separate Eritrean State entirely on its own would contain all elements necessary to seriously prejudice the interest of peace and security in East Africa now and in the future." This is a moot question now and obviously the fear is unfounded.

At the Paris Peace Conference on September 24, 1945, among the many world leaders who gave testimonials regarding Ethiopia's right of access to the sea, John Foster Dulles, head of the American

Delegation, said, "to avert the possibility of (Eritrea) being used at any time in the future as a base against Ethiopia, and to give that state access to the sea, the eastern part of Eritea including Massawa should be incorporated into Ethiopia." The British Delegate Mr. Mcnill also said, "The territory ceded to Ethiopia should include the Danakil Coast, the port of Assab." The French and Italians said more or less the same thing. Eventually by the Resolution of the United Nations 390 (IV). Eritrea became federated with Ethiopia under the Ethiopian Crown. This is where Ethiopia became the owner of two Red Sea ports of Assab and Massawa.

It is mind-boggling to learn any leader of a country would ever accept illegal colonial treaties, which were part and parcel of the same colonial scramble for Africa, as a basis for boarder demarcation. Yet in the same breath where EPRDF accepted colonial treaties as legitimate basis of border demarcation, the Ethiopian Minister of Foreign Affairs rightly condemned "maps that have been prepared by Italy, when Eritrea was its colony, [as] reflect [ing] the unilateral interest of the colonial power, and could not serve as an authorized international boundary." (The Ethiopian Hearald, December 20, 2001, p.1)

Whether the acceptance of colonial treaties as a basis for the border demarcation is a case of bad advice or there is something more sinister lurking under it, only time will tell. Ethiopian scholars at home and abroad dissected these so-called colonial treaties in their legal, historical, political and demographic contexts and concluded:

These treaties, driven by colonial ambition of Italy, were designed for the sole purpose of asphyxiating the only free and sovereign African State and the second



black free nation with Hait. A treaty whose purpose is to subjugate a free people is inherently illegal and therefore null and void.

It is an established doctrine both at international and municipal law that if a party to an agreement violates material intent or purpose of the agreement, the other party may exercise the right of abrogation. When Italy invaded Ethiopia in 1935/1936 and changed the boundaries creating Italian East Africa, and Ethiopia abrogated the treaties they became not only null and void, but also Italy was forced to pay war indemnity to Ethiopia in the form of Koka Dam, among others.

Agreements are binding between contracting parties or their authorized agents only. At the time when the so-called treaties were signed, Eritrea did not have legal existence. The theory of inheritance of earlier government action by a subsequent one does not apply here. Therefore Eritrea neither enjoys any rights emanating from the treaties nor is it subject to any obligations the treaty many impose on Italy.

According to all the treaties, Emperor Menelik in actual fact never ceded any territory to Italy. It is clearly and emphatically stated that if Italy for any reason whatsoever leaves Eritrea, the whole of Eritrea would revert back to Ethiopia.

The Wichalle Treaty, which later was renegotiated, reserves the Debre Bizen Monastery in the outskirts of Asmara along with its sister monasteries and large swath of land to Ethiopian's ownership. So if the Ethiopian authorities are going to live and die by defunct colonial treaties, how is it that they pick and choose those provisions that put Ethiopia at a disadvantage?

All these and many more facts could have been ammunitions in the arsenal of arguments available to

the Ethiopian authorities for reclaiming Assab and environs. We implored, pleaded, coddled and begged FPRDF leaders to assert Ethiopia's right of access to the sea. We pleaded with the EPRDF leaders to do no less than the Americans, the UN, the British, the French and others who at several forums acknowledged and pressed Ethiopia's right of access to the sea through the port of Assab.

Even as late as April 2001 the Arbitration Tribunal which awarded the Hanish Island to Yemen could not categorically refer to Assab as Eritrean territory. Rather it said, "Assuming the Bay of Assab as Eritrean internal Waters." Incidentally, Yemen was able to retain its fishing rights on the waters around Hanish Islands. Have Ethiopian authorities done even that much about Assab? No, the position Ethiopian authorities took is one of total capitulation and abdication of responsibility. What was EPRDF's response to our pleas, entreaties and appeals? EPRDF's response was to rub salt on our open wounds by the Prime Minister Ato Meles Zenawi, making unsolicited declaration and affirmation in front of the World press in Washington DC that Assab is Eritrean territory.

The threat the EPRDF dangles before us is: if Ethiopia refuses to sign the border demarcation agreement it will draw international ire in the form of economic sanctions, the banning of the Ethiopian Airlines international flights, etc. This arguments is hogwash because it has no basis in international law. International sanctions are imposed for violation of some tenet of international law or practice. While customary and conventional laws may prohibit use or threat of force for settling disputes between states, there is no law which requires states to enter into border demarcation agreements or sign friendship



treaties. What is to be done? The obvious question at this juncture is: what can citizens do at the 11th hour of signing the border demarcation agreement?

The only thing we can do at this time is to make yet another plea to the Prime Minister to desist from signing arguably the most infamous treaty Ethiopia has ever been a party to a treaty which may be guaranteed by the U.N, the U.S., OAU and which may be impossible to ever undo. We should flood the offices of the Prime Minister, the Minister of Foreign Affairs and the Speaker of the House with letters, faxes, e-mails, telephone calls denouncing the forthcoming treaty. If nothing else let them go to the signing ceremony with a cloud of illegitimacy hanging over their hands.

The Ethiopian people must express outrage over the border demarcation to the United Nations and the OAU. Silence on such matters of overriding importance may be construed as agreement with the government's action, which will shut off 85 million people from the sea and divide Afar families and communities. It may be foolhardy to expect the House of Peoples' Representatives and the House of the Federation, dismissed by many as a rubber stamp of a party, with the exception of few patriotic elements, to expect them to break ranks with the Executive and defend Ethiopia's interest. Miracles sometimes happen though. This is the last and the only oppoprtunity to rescind the agreement.

The constitutional right of rejecting Executive decisions, which is available to the House of Peoples' Representatives, and the power of judicial review, vested in the House of Federation, are at present the only escape route out of the fetters of the border demarcation agreement, which will seal off Ethiopia from the sea. A. Article 55, sub-articles 12, 17 and 18

of the Constitution empower the House of Peoples' Representatives to ratify or reject international agreements concluded by the Executive or question the Prime Minister or review the power thereof. The house of peoples' Representatives can therefore reject the border demarcation agreement when it is presented to it for ratification as being inimical to Ethiopia's interest. The agreement will then have no binding force on Ethiopia.

This is quite a common practice in democratic countries as exemplified by the recent Congressional rejection of the Kyoto Agreement which President Clinton had signed. Many such examples abound in most democratic countries where the people's representatives vot according to their conscience and the interest of their nation rather than cowtowing the party or government lines, which are one and the same in Ethiopia.

In the Ethiopian Constitution, the House of the Federation doubles as a legislative and judicial body, a rather curious mélange of constitutional authority for a constitution which purports to separate the three branches of Government. The House of the Federation, under article 62, has the power to interpret the Constitution-a function normally reserved for Supreme Courts or constitutional Courts in other jurisdictions. Through its interpretive power the House of the Federation can rule Legislative or Executive decisions as unconstitutional and therefore null and void following the procedures set out by the constitution.

Nowhere in the constitution has the Executive been given the power to cede any part of Ethiopian territory to any country. The demarcation agreement with Eritrea, which will forever bestow dominion over Assab - an Ethiopian territory and its national outlet to the sea – is above and beyond the authority granted



to the Executive by the Constitution. The House of Federation therefore has the duty of declaring such a flagrantly illegal agreement null and void. The house of Peoples' Representatives also must reject the agreement when it will be presented for ratification. This may be one great opportunity for the Representatives of both Houses to stand up and be counted and with a stroke of a pen capture the hearts of all Ethiopians which have so far been elusive to them. Let us remind them also the ceding any Ethiopian territory to any other country is a treasonous act which cannot be erased by statute of limitation nor is parliamentary immunity a defense.

## Conclusion

Assab in the hands of Eritrea will always be a menace to peace for Ethiopia as well as for Eritrea itself. Nobody can deny that Eritrean struggle for secession from the day of its inception has enjoyed material and diplomatic support of we know who, without whose support the secessions would have been a pipe dream. It is not farfetched to think that the piper may one day feel that she has to be paid, embroiling the horn of African in the Arab – Israeli conflict. In addition, since Eritrea has absolutely no use for the port of Assab, it may pass it over to enemies of Ethiopia providing yet another opportunity for Assab to become a flash point for conflict. I can also not imagine that any future generation of Ethiopians will ever acquiesce to Eritrean annexation of assab and let itself be asphyxiated. These statements should be construed as a plea for banishing war from our region. We Ethiopians want to live with our neighbors in peace and good neighborliness, particularly with Eritreans with whom we are inextricably intertwined for the better or worse a relationship which could be developed for mutual

benefit. The Eritrean and Ethiopian politicians who in my view could not see beyond the tip of their noses elected for separation of a people which should never have been torn asunder. Though we do not know the true sentiments of the Eritrean people regarding separation, we wish them peace and prosperity wherever they are. Nonetheless, we cannot afford to allow ourselves to be landlocked and condemned to perpetual poverty and approbation and cannot entrust our security to even our kith and kin, Erirreans.

The ball is on the Eritrean court. For us Ethiopians, access to the sea and the rights of the Red Sea Afars hold the key to the bliss that may await Ethiopia and Eiritrea. The Eritreans we hope will understand the emotion, sense of anxiety and loss Assab spells among Ethiopians, and we hope they will have the foresight and the maturity to see to it that this useless piece of property for Eritrea, yet a life-line for Ethiopia, will not forever be a wedge of hostility between these two sisterly African nations. There are myriad peaceful ways of incorporating Assab with Ethiopia, which are equitable, fair and just to all parties concerned. What is needed is goodwill on the Eritrean side and a little more interest on the part of the Ethiopian authorities to ensure that the largest recently landlocked country and yet the closest to sea anywhere in the world, has an access to the sea as it did for several millennia.



**"Ethiopia's border with Eritrea is drawn in space" Ato Issayas and he was right.**

**By: Yacob Haile-Mariam (Dr.)**

**Mr. Chairman, Ladies and Gentlemen**

Attendants of conference of this nature would rather have preferred a report on a subject researched with detached objectivity. My role however here, is going to be one of advocacy on behalf of my country-Ethiopia, basing myself on international law. I am here to make the case of my country to her own sea port and the preservation of the rights of the Afar people, rights so callously thrown away by irresponsible Ethiopian leaders who not even God knows where the loyalty of some of them lies, as an opposition leader once surmised. This is also a plea for durable peace and understanding in the region.

Few things in recent memory have gripped the imagination and foreboding of the Ethiopian people as the frightening prospect of being landlocked by the decision of mediators who would give a hoot about the security and prosperity of Ethiopia. I cannot recall in recent memory any issue that has galvanized Ethiopians everywhere as the question of Assab and the unification of the Afars. The sheer volume of literature on Assab

written by Ethiopians in and out of the country exceeds any heretofore produced. The question of access to the sea (perhaps couched as "sovereignty" of Ethiopia) may have been one of the issues that precipitated a crisis within the TPLF which almost brought down the government. These facts are indicative that the issue of Assab is going to bedevil Ethiopia for as long as it is not settled fairly and judiciously. And it is not going to be put to rest by a mere agreement between Melés and Issayas followed by the obligatory bear hug.

From the perspective of Ethiopians there is nothing more to add to convince the EPRDF to assert Ethiopia's right of access to the sea through its own sea port. EPRDF's refusal does not come from the conviction that Ethiopia has no right to the port of Assab, rather it is due to the nature of the EPRDF who has time again and consistently demonstrated arrogance and contempt for the wishes of the Ethiopian people. At the moment the EPRDF may be riding Ethiopia roughshod, but as someone said, power is something tricky, first you use it and then you abuse it and finally you lose it.

Rarely have Ethiopians displayed such unity of conviction as the belief that any settlement with Eritrea through the good offices of the UN, which does not recognize the unity and indivisibility of the Afars and not



just Ethiopia's right of access to the sea, but Ethiopia's ownership of the port of Assab and environs, is not worth the paper it is written on. The right of the Afar people to live under a system of their choice, is as important as it was for Eritreas' right of self-determination. As the saying goes what is good for the goose may also be good for the gander.

The EPRDF Government in flagrant defiance of the wishes of the Ethiopian people may go through the motions of signing any agreement it wishes, to appease international donors for some crumbs. However, any agreement, which is not anchored on the wishes of the people, will sooner or later be blown away like a chaff of wheat in the wind. The sanctity and the sovereignty of a country cannot be signed away by a government, least of all by a one party government, which holds monopoly of power. Only the Ethiopian people through referendum have the right to change the borders, particularly the North, which has literally been soaked with the blood of successive generations of Ethiopians who defended it. If Ato Meles signs away Assab it will not only be a treacherous act which will remain recorded in the Ethiopian history not only as "an act of infamy", but also as cowardice and criminal act which may exact consequences if and when that day of reckoning arrives.

There is however still time and opportunity for the EPRDF to extricate itself from the precipitous course it is following. Labeling Ethiopians who have raised the issue of Assab as EPLF lackeys is a case of a kettle calling a pot black. Such libelous cheap shot will not deter them from pursuing Ethiopia's interest until kingdom come if necessary.

If the EPRDF Government adamantly refuses to claim Asseb, then it has one last escape route before handing over Asseb to the EPLF in a silver platter and carry the stigma forever, as government which not only has helped in the breaking up part of its country but also ensured that it is also cut off from the sea . While international law mandates peaceful settlement of conflict between belligerent states, there is no law, which requires countries to demarcate their borders with their neighbors thereby putting their security and development,- possibly their very survival in serious jeopardy. International law also supports landlocked countries to have their own ports as long as they acquire it by peaceful means. While I persist in my belief that the cease fire currently in force should be observed scrupulously by both Ethiopia and Eritrea, the Ethiopia Government as the last resort should desist from signing this odious and inequitable agreement of border



demarcation which cedes Ethiopia's right of access to the sea through its own sea port and does not remove the iron curtain that has descended over the Afar people

Mr. Chairman Ladies and Gentlemen.

Asseb is not just a piece of real estate for Ethiopia .It is the homeland of the first Ethiopians, it is the first line of defense against our erstwhile and current enemies and its loss completes our encirclement with the possibility of being asphyxiated.

While I do not want to rehash the many historical, legal and geopolitical arguments so ably discussed and elaborated upon by many of my Ethiopia compatriots, suffice it here to say that on multiple legal grounds the treaties Emperor Menelik conclude with Italians were rendered invalid by the Italians themselves and Ethiopia exercised its right of abrogation .

These colonial treaties remained dead letters for more than fifty years until the EPRDF dug them up and resuscitated them. Never once were these treaties ever mentioned at any time or at any forum, including at the time when the Commission established by the UN was exploring the best means of disposing former Italian colonies, especially Eritrea. The rationale for UN Resolution 390(V) which recommend federation with

Ethiopia was "the wishes and the best means of promoting the welfare of the inhabitants taking in to account the right and claims of Ethiopia based on geographical, historical, ethnic or economic reason, in particular Ethiopia,s legitimate need for adequate access to the sea. Nowhere do the recommendations nor the *travaux preparatoire* mention the treaties apparently because the commission believed that the treaties had been defunct for over fifty years. Though history is not Ato Issaya's forte as he demonstrated it when he characterized Eritrean and Ethiopia's relationship as a myth or *"teret teret"* he was quite correct through, when he asserted that Ethiopia's and Eritrea's border is drawn in space, meaning the colonial treaties never demarcated the borders between Ethiopia and Eritrea.

Mr. Chairman, Ladies and gentlemen

Ethiopia has the dubious distinction of being the largest country in the world to be land locked followed by Uzbekistan with less than 20 million people. The distance between the sea and the Ethiopian border town of Mille is less than mere 60 kilometers, the shortest distance between a land locked country and the sea anywhere in the world. Assab is absolutely of no value to Eritrea while it is b is a lifeline for Ethiopia. Current experience as well as history and common sense



point to the lack of sea shores as a substantial handicap in economic and social development of the poorest countries of the world. As the port is for exclusive use of Ethiopia, Eritrea will have no interest in expanding the infrastructure of the port to meet the needs of the Ethiopian exports and imports. Even in recent years the road from Mille to the port of Assab was repaired and widened at tremendous cost to Ethiopia for which it is reported that Ethiopia was sued for twenty five million dollars by a French construction company who built the road. The various charges which will all be paid in hard currency, will be big a burden on the Ethiopian development. Moreover, land locking ninety million people when it is only within walking distance from the sea is simply anathema to equity and fair play in international relations.

Despite the fact that Ethiopia's right of access to the sea through its own port of Assab is fully confirmed by international law and many nations are on record confirming the same which I quoted in other occasions, the leaders of Ethiopia, took an incomprehensible position and chose not to lay a claim on a territory which rightly belongs to them. Their reasons may be found in the logic of power of which Kenneth Galbraith said, "Few things are as immutable as the addiction of

political groups to the ideas by which they have won an office." TPLF may have won office by force of arms in Ethiopia with a little help from their friends. But appeasing Issayas time and again is like keeping throwing meat to a lion hoping he will become a vegetarian.

The vexing question whether Ethiopia will lose its outlet once an agreement guaranteed by the UN and or the US and others is signed needs to be addressed. Such a compact of course puts Ethiopia, if not in an untenable, at least in a very difficult position. However, an agreement singed by the Ethiopian leaders which is universally denounced by all Ethiopians, except for some EPRDF cadres whose loyalty to Ethiopia is suspect at best, an agreement which goes against the kernel of the very fundamental right of survival of the body politic, can be argued not to be binding.

Certain rights are so fundamental and necessary and therefore cannot be derogated by an agreement or a contract. An agreement where I have voluntarily undertaken to have my hands cut off is unenforceable. Such an agreement is repugnant to public policy, *ergo* invalid. By the same token any agreement entered into by Ethiopian authorities which puts the body politic (Ethiopia) in peril, which is over and beyond the power



granted to them by the Constitution is *ultra vires* and therefore null and void. This leaves a window of opportunity, though admittedly narrow, for a future government to challenge the agreement at the International Court of Justice at the Hague. The Agreement that may cede Assab to Eritrea cannot also be binding if the House of representatives could muster some courage and rise up to the occasion and refuse to ratify it and in the process win some credibility, from the very people it purports to represent. Since the Constitution nowhere grants the Executive the power to change Ethiopia's border, the House of the federation which has the authority to declare any agreement or bill which is contrary to the Constitution as null and void can nullify the agreement as being unconstitutional.

Mr. Chairman Ladies and Gentlemen

Ceding Assab to Eritrea has very important global implications. The Red Sea is a very important sea-lane through which 70% of world oil supply passes. It is also one of the most volatile regions in the world. Eritrea with about five million people cannot ensure the safety and security of this important waterway. It will also be difficult for Eritrea to ensure the neutrality of the port and thus Africa may be dragged into the Middle Eastern quagmire. In other words Assab may be a flash point for

Arab Israeli conflict. It was reported just last week in the international media that Israel was desperately looking for a port in the Red Sea to launch missiles from. Eritrea which could not defend its territory even from the Ethiopian onslaught would be helpless to do anything if Israeli commandos suddenly landed in Assab one bright morning, thus bringing about the ire of the Arab countries .

Nobody can deny that Eritrean struggle for secession or liberation, call it what you may, from the day of its inception to its completion has enjoyed the support of the Arabs, without whose support the secession could very well have been a pipe dream. It is not farfetched to think that the piper may someday feel that he has to be paid, thus making the Port of Assab a target for Israeli military action.

In addition since Eritrea has absolutely no use for the Port of Assab, it may pass it over to enemies of Ethiopia, providing yet another opportunity for Assab to become a flash point for conflict.

**Conclusion**

My statements here should by no means be construed as saber rattling or a call for war. On the country, we Ethiopians' want to live with our neighbors in peace and



good neighborliness, particularly with Eritreans with whom we have many inextricable relationships, which could be developed for mutual benefit and growth. Ethiopians and Eritreans are one people who should never have been separated. The Eretria's politicians as well as those of Ethiopia, who in my view could not see beyond the tip of their noses elected for separation. Though we do not know the true sentiment of the Eritreans people we nonetheless wish them peace and prosperity wherever they are. We cannot however, allow ourselves to be landlocked and condemned to perpetual poverty and approbation and leave ten percent of our Afar brothers and sisters under Eritrean rule, especially when they do not want to. Though peace at any-price may be fraught with problems, peace at almost any price is worth the gamble. I therefore challenge Eritreans to take the bold step of effacing forever the dark clouds of war that have been hovering over these two sisterly countries. Real peace is not brought about by formal signatures of dictators executed behind the back of the people, but by purposeful open discussions. We the People can prevail over our leaders to seize the moment and reach equitable and fair agreement on this problem of Ethiopia's access to the sea and banish the possible conflict that will inevitably engulf these two sisterly

nations as long as Ethiopia's sovereign territory is not restored to its rightful owners - the Red Sea Afars, ninety percent of whom are Ethiopians residing in their own country while ten percent are forcibly brought under Eritrean jurisdiction.

Thank you Mr. Chairman.

* Presented at the International Conference on THE CHALLENGES AND OPPORTUNITIES OF GLOBALISATION: THE DAWN OF THE MILLENIUM. April 10-13-2001, Howard University, Washington DC, USA



## 5. <u>የተለያዩ የሕብረት ሰቡ ክፍሎች አስተያየት</u>

## <u>አሰብን ለማስመለስ ለሚደረገው ትግል ንቁ ተሣትፎ እናድርግ</u>

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የቀድሞ የኢፌድሪ ፕሬዘደንት

በአገሮች መካከል የሚደረግ የትኛውም የድንበር ወይም ወሰን ስምምነት የገዢዎችን ወይም የመንግሥታቱን ፍላጎት ሳይሆን የየሀገሮቹን ህዝቦች ጥቅም ማዕከል ያደረገ መሆን እንዳለበት ለሰው ልጅ መብቶች መከበር የሚታገሉ ሁሉ የሚያምኑበትና ለተግባሪዊነቱም የሚከራከሩት መርህ ነው።

የህዝብን ፍላጎትና ጥቅም መከበር ማዕከል ያደረገ የወሰን አከላለል ስምምነት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አንድ ትልቅ ጉዳይ የሰውና የሸቀጥ ነፃ ዝውውርን በተመለከተ ነው። ይህ የሰውና የሸቀጥ ነፃ ዝውውር ለህዝቦች መከበር ያለበት የሰብአዊ መብት ነው። ለዚህም ነው ወደብ አልባ የሆኑት የመሀል አውሮፓ አገሮች፤ ማለትም እነ ሀንጋሪ፤ ቼክና፤ ስሎቫክና አውስትሪያ ከጀርመን ጋር በልዩ የዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት የጀርመኑን የሀምቡርግ ወደብ በመጠቀም በአድሪያኒ ባህር በኩል ወደ ዓለም ገበያ እንዲደርሱ መብታቸው የተከበረላቸው ሌሎችም ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል።

ከዚህም መርህ በመነሳት ነበር የተባበሩት የዓለም መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በታህሳስ 1950 ዓ.ም እ.ኤ.አ የኤርትራን ህዝብ ፍላጎትና ጥቅም (Welfare) የአካባቢውን ሠላምና ደህንነት እና በተለይም የኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት ህጋዊ መብት (legitimate right) ከግንዛቤ በመውሰድ ኤርትራና ኢትዮጵያ በፌዴሬሽን መልክ አብረው እንዲኖሩ የወሰነው። ይህ ውሳኔ አሰብን ወደብ የሚመለከት መሆኑ ግልጽ ነው።

በኔ በኩል የአሰብ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ይዞታ መሆንዋ ከጥያቄ ውስጥ ሊገባ የማይችል ሃቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ የህዝቦች መብት ስምምነቶች አኳያም ሆነ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ህጋዊ የኢኮኖሚና የደህንነት ፍላጎትና ጥቅም አኳያ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ ይዞታነት እንድትመለስ የሚደረግ የሕጋዊና የዲፕሎማሲያዊ እንቀስቃሴ መጠናከር አለበት።

ይህን የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት፣ ጥቅምና መብት ማስከበር ኢህዴግ አልቻለም። ኢህዴግ ይህን ለማድረግ ያለመቻል ብቻ ሳይሆን ከዚህ አኳያ ትላልቅ ስህተቶችንም ፈጽሞል። የመጀመርያው ጥፋት የኤርትራ ጥያቄ የኮሎኒያሊዝም ጥያቄ ስለሆነ ኤርትራ ነፃነት ይገባታል የሚለውን አመለካከት መያዙ እና የኮሎኒያሊዝም ሆነ የሌላ ዓይነት የብሔር ጭቆና የሚፈታው አንድነትን፣ፌዴሬሽንን ኮንፌዴሬሽንን፣ ነፃ መንግሥትን የማቋቋም አማራጮች ቀርበውላቸው በህዝቦች የራስን የመወሰን መብት በማስከበር መሆኑ ትኩረት ያለመስጠት አካሄድ ነው።

ሁለተኛው ጥፋት በሕዝብ የተመረጠ ዴሞክራሲዊ ሕጋዊ መንግሥት ሳይቋቋም በሽግግር ወቅት የኤርትራ ሬፈራንደም እንዲካሄድ ሁኔታን ማመቻቸቱ ነበር። ኤርትራ ነፃነትዋን ስታውጅ ኢትዮጵያ የአሰብን ጉዳይ ጨምሮ በሌሎች ጉዳዮችም የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት ጥቅምና መብቶች የሚያስከብር አግባብነት ያለው ስምምነት እንዲፈረም ያለማድረግ ነው።

ሦስተኛው የኢህአዴግ ስህተት በባድመ ጦርነት ማግባደጃ ወቅት ኢትዮጵያ የተፈፀመባትን ወረራ ለመቀልበስ ስታደርግ በነበረው እንቅስቃሴ አሰብንና ምጽዋን ጨምሮ ሌሎች የኤርትራን የቀይ ባህር ጠረፍ አካባቢዎች የመያዝ አቀም ነበራት። ኢትዮጵያ ይህን አቅም በመጠቀም አሰብን የማግኘት ድረድርና ስምምነት ማድረግ ትችል ነበር። ሆኖም ግን "አሰብ የአንድ የሉዓላዊ ሀገር ይዞታ ስለሆነች አሰብን ከያዛችሁ ጥሉ ከኤርትራ ጋር ሳይሆን ከኔ ጋር ነው" ብላ አሜሪካ አስጠንቅቃናለች በማለት የኢትዮጵያ ሠራዊት ከኢትዮጵያ ኤርትራ ድንበር አልፎ አሰብን እንዳይዝ ታዘዘ። ይህ ትልቅ ስህተት ነበር።

በመጨረሻም በጦርነቱ ፍፃሜ የተፈረመው የአልጀርሱ ስምምነት ጊዜ የተፈፀመ ስህተት ነው። ስምምነቱ የአሰብን ጉዳይ ትኩረት ያለመስጠቱ ብቻ ሳይሆን ስምምነቱን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተግባራዊ አደርጋለሁ ብሎ መፈረም ነው። የኢትዮጵያ



ሕዝብ የአጭርና የረጅም ጊዜ ፍላጎት ጥቅምና መብት የማያስከብር ስምምነት ከመፈራረም ይልቅ ለሌሎች ኃይሎች የመንበርከክ ተግባር ተፈጽሞአል።

እነዚህ ሁሉ ስህተቶች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ስለሆኑ ኢህአዴግ ከተጠያቂነት አይድንም። እኔን ጨምሮ በውቅቱ የኢህአዴግ አባለት የነበርነውም ሆነ ከዚያም በኋላ ኢህአዴግን እያገለገሉ ያሉት አባላት በተጠያቂነት መንፈስ እነዚህ ስህተቶች በማመን ለስህተታችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ እየጠየቅን አሰብን በሠላማዊ፣ በህጋዊና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ለማስመለስ በሚደረገው ትግል ንቁ ተሳትፎ እንድናደርግ አሳስባለሁ።

እኔ በኢህአዴግ ውስጥ በነበርኩ ጊዜ አብዛኛ የኢህአዴግ አመራርና አባለት አሰብን በተመለከተ ስለ አሰብ ያለውን ታሪካዊና ሕጋዊ የባለቤትነትችን መከራከሪያዎች በቂ እውቀት አልነበርም ለዘህም ትኩረት አልሰጠንም። ስለሆነም የጉዳዩን ክብደት በመገንዘብ ክእንቅልፋችን እንድንነቃና በጉዳዮ በቂ እውቀት እንዲኖረን ይህ የዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማሪያም መጽሐፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለኝ። ስለሆነም መጽሐፉን በጥሞና እንድናነብ አደራ እላለሁ።

## 7.7. የባህር በር ጥያቄ

መሐመድ እሲ መሐመድ

የባህር በር ጉዳይ የብሔራዊ ፀጥታ ጉዳይ ነው፡፡ የባህር በር ጉዳይ የአንድ አገር ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ሊሰኝ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ የባህር በር ጉዳይ የአንድን አገር የውጭ ግንኙነት ሊወስን የሚችል ትልቅ ጉዳይ ነው፡፡ የባህር በር ያለው አገር ብሔራዊ ደህንነቱን ለመጠበቅ ጠንካራ የባህር ኃይል የማደራጀትና የባህር ክልሉን የመቆጣጠር እድሉና አቅሙ ይኖረዋል፡፡ የባህር በር ባለቤት መሆን ዓለማቀፍ የባህር ህግ በሚፈቅደው መሠረት ከባህር ክልሉ በርካታ ኢኮኖሚዊ ጥቅሞችን ማግኘት ያስችላል፡፡ የባህር በር ያለው አገር የተቀላጠፈ የወጭና ገቢ ንግድ ማካሄድ ይችላል፡፡ የባህር በር ያለው አገር በሌሎች አገሮች ዓይን የሚሰጠው ግምትና ሊኖረው የሚችለው ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ የባህር በር በአንድ አገር ብሔራዊ ፀጥታ፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴና ዕድገት፣ የውጭ ግንኙነት ውስጥ ያለው ድርሻና ሚና እንዲህ በቀላሉ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያ ባላት ተፈጥሯዊና መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ታሪካዊ የባህር በር ባለቤት መሆን አስችሏታል፡፡ የኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤትነትና ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ የተረዱ ባዕዳን ኃይሎች በተለያዩ ዘመንት በተለያየ መንገድ ሲፈታተኗትና ብሔራዊ ፀጥታዋን ሲያውኩዋት ኖረዋል፡፡ ኢትዮጵያውያንም የባህር በራቸውንና ብሔራዊ ፀጥታቸውን ለመጠበቅ በቀላሉ ሊሰላ የማይችል ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ እነሆ ዛሬ ኢትዮጵያን በሚመሩና በሚያስተዳድሩ ኃይሎች ሁለንተናዊ ትብብርና ይሁንታ አያት ቅድመ አያቶቻችን ለዘመናት ብዙ መስዋዕትነት ከፍለውና ጠብቀው ያቆዩንን የባህር በር አጥተናል፡፡ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነቷን ለማረጋገጥ በርካታ ህጋዊ፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ መልክዓ-ምድራዊና ተፈጥሯዊ መብቶች ቢኖሯትም እነዚህን መብቶች ተጠቅሞ ብሔራዊ



ጥቅሟን ለማስከበር አሁን በሥልጣን ላይ ያሉ መሪዎች መልካም ፈቃድ አልሆነም፡፡ እንዳውም ጉዳዩ የሚያሳስባቸው ወገኖች የሚያነሱትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ «ጦርነት ከፈለጋችሁ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ፤ አሰብን ከፈለጉ አፋሮች ግመሎቻቸውን ውሀ ያጠጡበት» በማለት ሲያፌዙና ሲሳለቁ ቆይተዋል፡፡

በዚህም ምክንያት አሰብና ምፅዋ ላይ የተገነቡት ወደቦችና እንጡራ ሀብቶች ያለጠያቂ ቀርተዋል፡፡ ለዘመናት የተገነባው የሀገሪቱ የባህር ኃይልም እንደዋዛ ፈርሶና ተበታትኖ ቀርቷል፡፡ ይህም በመሆኑ የሀገሪቱ ብሔራዊ ደህንነት ለውጭ ኃይሎች ጥቃትና ለአደጋ የተጋለጠ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የገቢና ወጭ ንግድ በጎረቤት አገሮች ቁጥጥር፣ መልካም ፈቃድና ይሁንታ ሥር የወደቀ ነው፡፡ አገሪቱ ከፈለጉ ወታደራዊና ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሣሪያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ለመከልከል ዕድሉና መብቱ በእጃቸው ነው፡፡ ከዚህም በቀር ባለፉት ሃያ ዓመታት ለወደብ ኪራይና ተያያዥ አገልግሎቶች አገሪቱ ያወጣችው ገንዘብ በንት ግድቦች፣ ሆስፒታሎች፣ ፋብሪካዎችና ሌሎች ተቋማትን መገንባት ያስችለን እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡ ይበልጥ የሚከብደውና የሚያንገበግበው ደግሞ ሀገሪቱ ከዚህ በኋላም ለወደብ ኪራይና ተያያዥ አገልግሎቶች ገና የምትከፍለው ገንዘብ በዘመናት ሲሰላ ነው፡፡ ለልጆቻችን የምናወርሳቸውም ይህንኑ ዕዳና ታሪክ ነው፡፡

መሐመድ እሰ መሐመድ (በህግ ኤል.ኤል.ቢ./የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በአማቀፍ ህግ ኤል.ኤል.ኤም./የማስተርስ ዲግሪ እና የቀድሞ ፓርላማ አባል)

## 5.2. የባህር በር ጥያቄ ከኢትዮጵያ አንድነት፣ የሕዝብ ሉዐላዊነት፣ ከጸጥታና ከልማት እድገት ጋር የተገናኘ ጥያቄ

አያልሰው ደሴ፣(ዋሺንግተን ዲ.ሲ)

"....... በአሁኑ ጊዜ ብቻ ሳይሆን የሕወሓት መሪዎች አገሪቱን ወደጦርነት ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ የሚነሣው ጥያቄ ኢትዮጵያን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሷ ልጆች የተነፈገችውን የባሕር በር ባለቤትነት ጉዳይ አግባብዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል የሚል ነው።

እንደሚታወቀው ሕወሓት/ኢሕአዴግ ከሻዕብያ መንግሥት ጋር ወዳጅነቱ ሲያከትም እና በተለይም እራሱ ሻዕብያ በተነኮሰው ጦርነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ-አንድ ሰው ተነስቶ አብረተኛውን የሻዕብያ ወራሪ አይቀጡ-ቅጣት ቀጥቶ ድባቅ በመታበትና አዋራጅ ሽንፈትን ባከናነበበት ወቅት ይኸው አንገብጋቢ የወደብ ጉዳይ መነሣቱና ቢያንስ አሰብን ማስመለስ አመቺውና ሁለንተናዊ ሕጋዊና ታሪካዊ መሠረት ያለው ብዙም ሊያስጠይቅ የማይችል ሥነ ምክንያትና በአካሄድም ተቀባይነት ያለው ሁኔታ ሲፈጠር የሕወሓት/ኢሕአዴግ ቁንጮዎች መደንገጣቸው ግልጥ ነበር። ድንጋጤው ያንን ማድረግ የማይቻል ስለሆነ ሳይሆን አገሪቱን የባሕር-በር ባለቤት የመሆን እንጡራ መብቷን ካለመገንዘብ ቢያንስ ግን ፍላጎቱ ጨርሶ ስለሌላቸው ነው። ያንን "ታሪካዊ አጋጣሚ" ባለመጠቀምና ኢትዮጵያ የራሷ ወደብ ባለቤት እንዳትሆን ለመገርገራቸው በምክንያትነት የቀረቡ አዲስ ዙር የማሣመኛ ነጥቦች ደግሞ "ኢትዮጵያ እንደ ወራሪ እንድትታይ ያደርጋል ........ የምንጠቀምበት የወደብ ችግር የለብንም፤ጅቡቲን በርበራን ሞምባሣን ፓርት ሱዳንን መጠቀም እንችላለን ..." የሚል ዓይነኸን አሣየኝ ሲሉት እግርን እንደማሣየት የሚቆጠር የአልተገናኘቶም አቀራረብ ነበር የሚሰነዘረው።

ኢትዮጵያ በባለቤትነትና በራሷ ቀጥተኛ ቁጥጥር ሥር ያለ/ያሉ የባሕር ወደብ /ወደቦች እስከሌላት/ሏት ድረስ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ሰላም፤ ደኅንነት፤ፀጥታ፤ የኤኮኖሚ እድገትና ልማት ሊኖራት አትችልም ። ያ ሣይሆን የሚደርግ "የልማት"



ጥረት ሁሉ ድንጋይ አንገት ላይ በሸምቀቆ አሥሮ ለመዋኘት ወይም በባዶ እግር በእሾህ ላይ ለመሮጥ የመሞከርን ያኸል ወይም በወንፊት ውሃ ለመቅዳት እንደመሞከር ከንቱ ድካምና ቀቢፀ-ተስፋ ይሆናል"።

- ይህ አስተያየት ከሰይ በአርቡ ከተጠቀሰው ሰፋ ካለና ጥልቅ ጽሁፍ የተወሰደ ነው። በቦታ ጥበት ምክንያት በሙሉ ባለመታተሙ ይቅርታ እንጠይቃለን

## 5.3. ትንሽ አሰ'ብ ያልተደረገበት አሰብ

ወ/ት ርዕዮት ዓለሙ

ኢትዮጵያን ያለባህር በር ማስቀረት ኢህአዴግ ከሚወቀስባቸዉ ትላልቅ ጥፋቶቹ መሀል አንዱ ነዉ።ይህንን ጥፋት የፈጸመው ደግሞ በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ አልነበረም። የሻዕቢያን "ውለታ" ለመመለስ የፈጸመው አድርባይነት እንጂ! ገዢዉ ፓርቲ ኢትዮጵያ አሰብን እንድታጣ ሲያደርግ ሶስት ትልልቅ ጥፋቶችን ደረጃ በደረጃ ሰርቷል። የመጀመርያው ጥፋቱ ከሻዕቢያ ጋር በመተባበር ለኤርትራ ህዝብ ነጻነት ወይስ ባርነት የሚል አሳሪ ምርጫ ማቅረቡ ነው። ኢትዮጵያና ኤርትራ ከመለያየት ወይም ደግሞ እንደቀድሞ አብሮ ከመኖር ውጭ ሌላ አይነት ይዘት ያለዉ ግንኙነት ሊኖራቸው እንደማይችል አድርጎ ሁለት ምርጫዎች ብቻ ማስቀመጡና ምርጫዎቹ የቀረቡባቸዉ ቃላት በራሳቸዉ መለያየትን እንጂ አብሮ መኖርን የማያበረታቱ መሆናቸው የመጀመርያ ደረጃ ጥፋቱ ነዉ። ይህን ጥፋት እንዳይሰራ በርካታ ሀገር ወዳድ ዜጎች አስቀድመው ምክር የለገሱ ቢሆንም የሰማቸው አልነበረም። በወቅቱ ውሳኔዉን የተቃወሙ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም በጥይት ተቆሉ። በዚህ አይነት መንገድ ወያኔ /ኢህአዴግ አሰብን ለሻዕቢያ አስረከበ። ኢትዮጵያ በሁለቱ ዝሆኖች ፈላጭ ቆራጭነት ልጆቿን ማጣቷ ሳያንስ አሰብን ያህል እጅግ የሚያስፈልጋትን የባህር በሯንም አጣች።

የኢህአዲግ ሁለተኛ ጥፋት የሚከተለው ይሄኔ ነው። መነጣጠል የማይገባቸዉ እናትና ልጅ መለያየታቸው አይቀሬ ከሆነ አሰብን በተመለከተ ኢትዮጵያንም ተጠቃሚ የሚያደረግ ስምምነት እንዲደረግ ብዙዎች አጥብቀው ቢወተዉቱም ኢህአዲግ ግን ጆሮ ዳባ ልበስ አለ። ይልቁንም አሰብን የግመል መፈንጫ በማለት አጣጣለው። ያኔ ኢህአዴግ በዚህ መል፤ ያጣጣለዉ አሰብ ግን ኢትዮጲያን ለወደብ አገልግሎት ብቻ ተጨማሪ ብዙ ገንዘብ እንድታወጣ በማድረግ ለሌላ የኢኮኖሚ ድቀት ምክንያት ሆኗል። ኢህአዴግ በወቅቱ ከሻእቢያ ጋር የነበረዉ ፍቅር ስላልወጣለት ሁሉም ነገር ወደኤርትራ ቢጓዝና ኢትዮጵያ ባዶዋን ብትቀር ጉዳዩ አልነበረም። መስከረም 1996 ዓ.ም የወጣው ጦቢያ መጽሄት ይህንኑ እውነት ኢህአዴግ ራሱ በ1984 ዓ.ም "አብዮታዊ ዴሞክራሲ በኤርትራና በአንድነት ጥያቄ ላይ" በሚል ርእስ ያወጣዉን መጽሃፍ በመጥቀስ ያብራራል። መጽሐፉ በገጽ 90 ላይ በወቅቱ ኢህአዴግ ሲቀርብበት የነበረዉን የኢትዮጵያን ንብረቶች ወደ ኤርትራ የማጓዝ ውንብድናን የተመለከተ ጥያቄ የመለሰ መስሎት የሚጓዙት ንብረቶች ደርግ ከኤርትራ የወሰዳቸዉ በመሆናቸው ሊመለሱ እንደሚገባ "ዛሬ ሰላም በሚሰፍንበት ጊዜ ከኤርትራ እንዲመጡ የተደረጉት ንብረቶች ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባቸዋል።" በማለት ያስረዳል። ሻዕቢያ ከኢትዮጲያ እንደወሰዳቸዉ ያመናቸውን ንብረቶች በተመለከተ ግን በዚሁ መጽሃፍ በገፅ91 ላይ "ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ አሰብ በገባበት ጊዜ እዚያ የነበረውን ንብረት አስመልክቶ ያለው ሁኔታ ማንኛውም የታጠቀ የተቃዉሞ ሀይል አንድን አካባቢ ከደርግ ነጻ አዉጥቶ በሚቆጣጠርበት ጊዜ የሚያገኘውን የመንግስት ንብረት በምርኮ እንደተያዘ ንብረት ቆጥሮ መውሰዱ የተለመደ ነገር ነዉ።" የሚል ፍርደ ገምድል ውሳኔ እንደምናነብ መጽሄቱ ያስረዳል። ኢህአዴግ ለሻዕቢያ የነበረዉ እንዲህ አይነቱ ጭፍን ፍቅርና ዉለታ መላሽነት አሰብን ለማጣታችን ምክንያት መሆኑ ያሳዝነኛል። ሶስተኛዉ ጥፋቱ ደግሞ ኢትዮጲያ ገንዘቧን ከፍላ አሰብን መጠቀም እንዳትችል እንኳ አድርጓታል። "ሌባ ሲካፈል እንጂ ሲሰርቅ አይጣላም" እንደሚባለዉ ኢህአዴግና ሻዕቢያ የነበራቸዉ ግንኙነት ጥቅምን ታሳቢ ያደረገ ነበረና የስልጣን መንበሩን ከተቆናጠጡ በኋላ ፍቅራቸው ሊዘልቅ አልቻለም። በዚህ የተነሳም ኢህአዴግ ኢትዮጵያና ኤርትራ መልካም ጉርብትና ቢኖራቸዉ ኖሮ ሀገራችን ልታገኝ ትችል የነበረዉንም ጥቅም አሳጥቶናል። ስለዚህ ጉዳይ ባሰብ ይበልጥ የሚያስገርመኝ ደግሞ ኢህአዴግ ከዚህ በፊት የተጠቀሱትንና ሌሎችም ጥፋቶች መፈጸሙ ሳያንስ አሁንም በግትር አቋሙ መቀጠሉ ነዉ። ኢትዮጵያ በአሰብ ልትጠቀም የምትችልባቸዉ አለም አቀፍ ህጋጋቶች እንዳሉና አሁንም እድሏ እንዳልተሟጠጠ በማስረዳት የሀገራቸዉን ጉዳይ ጉዳዬ ብለዉ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ ምሁራንን ለመተባበር እንኳ ፍቃደኛ አይደለም። በተቃራኒዉ "ከአፈርኩ አይመልሰኝ" እንዲሉ የጥፋቶቹን ትክክለኛነት ለማስረዳት እየዳከረ እንጂ! ይህን ደግሞ ኢህአዴግ በሀገር ላይ እየፈጸመ እንዳለዉ ታላቅ ክህደት እቆጥረዋለሁ። ትንሽ እንኳ አሰ'ብ አለማድረጉ አሰብን እሷማድረጉ አሰብን አሳጥቶናልና!

## 5.4. ለኤርትራ አሳልፈን የሰጠነው ስጦታ መጣት እንዳልካቸው ተስፋዬ

ስለ ወደብ ጥቅም እና አገልግሎት፣ ለአንድ ሃገር እድገት እና ብልጽግና እሚያደርገው አስተዋጽኦ፣መዘርዘር ብዙም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም ሁሉም ሰው በሚገባ በነቅቶ የሚያውቀው ሀሁ ነው። ነገር ግን የኢትዮጵያ የባህር በር አልባ አገር መሆን ግን የሚያስከፍላት ኢኮኖሚያዊ ዋጋ እጅግ በጣም ከባድ ቢሆንም ጉዳቱ ግን ከኢኮኖሚ ጉዳት በተጨማሪ ትልቅ የደህንነት እና ከውጪ ለሚቃጣ ወረራ ተጋላጭነትም ጭምር ነው። የዚህ ወደብ አልባ ወይንም የባህር በር አልባ የሆንነው የራሳችን የሆነውን የባህር በር በራሳችን መልካም ፈቃድ ጭምር ለተገንጠለችው ኤርትራ አሳልፈን የሰጠነው ስጦታ መሆኑም ጭምር ነው።

ከዚህ በፊት የነገሱ የኢትዮጵያ ነገስታት እና ገዢዎችን እሚያመሳስላቸው አንድ መሠረታዊ ጉዳይ ቢኖር በአገር ጉዳይ ወይንም የኢትዮጵያን ጥቅም ሊነካ በሚችል ጉደይ ላይ በፍጹም የማይደራደሩ መሆናቸው ነው። ሁሉም ይህችን አገር የመምራት እድል ያገኙ መሪዎች፣ አጼ ቴዎድሮስ የውጪ ዜጎች ከአገራችን አፈሯን እንኳን ይዘው እንዳይወጡ ያደረጉበትን የታሪክ ክስተት እንደሚጋሩ አያጠራጥርም። ሆኖም ግን የኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት የመሆን መብቷን በፈቃደኝነት አሳልፎ ለሌላ አገር የሰጠ እና ብሔራዊ ጥቅሟን ለአደጋ አጋልጦ የጣለ የኢትዮጵያ ገዢ በመሆን ኢህአዲግን እሚስተካከለው አይገኝም። ኢህአዲግ በዚህ ረገድ የሠራው ታሪካዊ ስህተት የትሮይ ፈረስን ታሪክ እንድናስታውስ ያደረገ ነው።

የባህር በር ባለቤትም መብት ማስጠበቅ አለመፈለጉ ሳይሆን ከስህተቱ አለመማሩ እና ጉዳዩን በሰከነ መንፈስ መርምሮ የባህር በር ባለቤትነት መብታችንን በህጋዊ መንገድ ለማስመለስ ከመጣር ይልቅ ይግባኝ እንኳን የማይጠየቅበትን የአልጀርሱን ስምምነት በመፈረም የትሮይ ፈረስነቱን በሆዱ የጠላቶቻችንን ጦር ጓዶችን ድረስ ይዞ በመግባት እና በሌሊት በራችንን ለጠላት ክፍት በማድረግ አስመስክሯል። ጠላትን ማዳከም የሁሉም ተገዳዳሪ



ሃይሎች እስትራቴጂ እስከሆነ ድረስ ኢትዮጵያን ያለወደብ ማስቀረት የኢትዮጵያ ጠላቶች ብቻ ብቸኛ ምርጫ ሲሆን ይህን የፈጸሙ እና ያስፈጸሙ ደግሞ የትሮይ ፈረስ ሆነው ለጠላት በማገልገላቸው የታሪክ ተጠያቂነታቸው አይቀሬ ነው።

የአሰብ ጉዳይ የፖለቲካ ጉዳይ አይደለም። የአሰብ ጉዳይ የወደብ ወይም የባህር በር ናፋቂነት ጉዳይ አይደለም። የአሰብ ጉዳይ የሌላ አገር መሬት ናፋቂነት ጉዳይም አይደለም። የአሰብ ጉዳይ የራሷን መሬት በታሪክ ስህተት የተነሳ አሳልፋ በመስጠቷ ምክንያት ለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ የተዳረገችውን እና አገራዊ ድህንነቷን ለከፍተኛ አደጋ አጋልጣ የሰጠችውን አገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በህጋዊ መንገድ የማስመለስ ጉዳይ ነው። ብሄራዊ ጥቅም ደግሞ ሁሌም ከፖለቲካ፣ ከዘር እና ከመሳሰሉት ልዩነቶች ሁሉ በላይ ነው። ይህን ብሔራዊ ጥቅም የማስጠበቅ ኃላፊነት ደግሞ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። የአባይ ወንዝ አጠቃቀምን በተመለከተ ግብጽ በአገራችን ላይ አንዳች አይነት ወረራ ለመፈጸም ብትሞክር በእስራኤል ከደረሰባት የከፋ ሽንፈት ነው የሚገጥማት ብለን የምንፎክርበት ትልቁ መሳሪያችን የእኛ

የኢትዮጵያዊያን አልደፈር ባይነት እና በብሔራዊ ጥቅማችን ላይ አልደራደር ባይነታችንን ነው። ይህንን አልደፈር ባይነት እና በብሔራዊ ጥቅማችን ዙሪያ አልደራደር ባይ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን በባህር በር ባለቤትነት መብታችን ዙሪያም ልንጠቀምበት ይገባል። በአሰብ ወደብ ዙሪያ ላለው ቁጭታችን ትንሽ መጽናኛ የሚሆነን ወደባችንን የማስመለሻ ህጋዊ መንገዶች አሁንም በእጃችን ያሉ መሆናቸው ነው። ስለሆነም ማንም ኢትዮጵያዊ የባህር በራችንን እስከምናስመልስበት ጊዜ ድረስ አሰብን እንኳን ሊረሳት ይቅር እና ለአፍታም እንቅልፍ ይወስደዋል ብዬ አልገምትም። እኔም በበኩሌ በፍጹም አይወስደኝም።

1. "ራሱን በተጠሪነት ያቀረበው የኢሕአዲግ መንግሥት ታሪክ ይቅር በማይለው ደረጃ ክህደት ፈጽሞአል። ይህ ይግባኝ የሌለው ውሳኔ ያደረሰው ጉዳት 1ኛ) የኢትዮጵያ ዜጐች የሆኑ ሕዝቦች ከፈቃዳቸውና ከፍላጐታቸው ውጭ ለማይፈልጉት ወገን አሳልፎ መስጠቱ 2ኛ) ካለአግባብ የኢትዮጵያን ሉዐላዊ መሬት አሳልፎ መስጠቱ 3ኛ) የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት መብት ለድርድር እንዳይቀርብ አፍና በመያዝ ጉዳዩ ዳግመኛም እንዳይነሳ በሚያስር መልኩ ማስወሰኑ ጉልተው የወጡ ናቸው"።

ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ <u>አዲስ ዘመን</u> ግንቦት 3 ቀን 1994 ዓ.ም

---

2. በአሰብ ዙርያ የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ለውጥ ይኖረዋል ብለው ያምናሉ ወይ ብለው ለተጠየቁት ፕሮፌሰሩ "ከምምንቱን በመቃወም ባነሳነው የባህር በር ጥያቄ አማካኝነት ውሳኔው የሚለወጥ አይመስለኝም። መፍትሔ የሚገኘው ብሔራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ መንግሥት ሲመጣ ነው። እስከዚያው ድረስ ትግላችን ይቀጥላል።

ፕሮፌሰር መራራ ጉዲና የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግሬስ ሊቀመንበር <u>አዲስ አድማስ</u> መጋቢት 21 ቀን 1994 ዓ.ም

---

3. "ጥንት በቁጥጥራችን ስር የነበረው የቀይ ባህር ቢለማም ቢከፋም አሰብን እንኳን ሳናስቀር የባህር በር ማጣታችን አሳዛኝ ድርጊት ነው። በዚህ ዓለም አገርዋን ቁርጣ ነፃ ሁኚ ብላ የሰጠች አገር ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ጊዜ ይፍጅ እንጂ የባህር በር እንዳጣን አንቀርም። የኢትዮጵያ ጠላቶችም መጥፋታቸው አይቀርም"

ፍቅሩ ኪዳኔ <u>የፒያሣ ልጅ</u> አዲስ አበባ 2009 ገጽ 222



## <u>(ዋቢ ሰነዶች)</u>

### 1.<u>አማርኛ መጽሐፍት</u>

1. በዛብህ አስፋው ዶ/ር <u>ከፍጥጫው በስተጀርባ</u> አዲስ አበባ የካቲት 1997
2. እሥራት አብርሃም <u>ከአገር በስተጀርባ ሕወሓትና ሻቢያ የትሮይ ፈረስና የባለፈረሱ ተልዕኮ</u> 2ኛ ዕትም ሕዳር 2003
3. <u>የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የምርጫ ማኒፌስቶ፣</u> አዲስ አበባ 1997 ዓ.ም
4. <u>የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አንድነት መድረክ መሰስተኛ ፕሮግራም</u> አዲስ አበባ 2001 ዓ.ም
5. <u>የዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ሉዐላዊነት ፕሮግራም</u> ነሐሴ 22 ቀን 2002 ዓ.ም
6. ተወልደ ገብረ ትንሳይ (ኮሎኔል) <u>ባድመ እንደ ምክንያት ፤የፍፃሜው መባቻ</u> (የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እውነተኛ ታሪክ) አዲስ አበባ (2009)
7. <u>የኤርትራ ቅኝ ግዛት የህግ መጽሐፍ ከአራተኛው ጥራዝ</u> ከገጽ 779-780 በጣልያንኛ የተጻፈው (1962)
8. ኃይሉ ወልደጊዮርጊስ (አምባሰደር) <u>ለአባይ ውሃ ሙግት</u> አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ (2001
9. <u>ትዕዛዝ ቁ.27/1962 ነጋሪት ጋዜጣ ፳ኛው ዓመት ቁ 27 1962 ዓ.ም</u> አዲስ አበባ
10. ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ <u>የአክሊሉ ማስታወሻ፣</u> መስከረም 10 ቀን 1967 ዓ.ም. (ለመርማሪ ኮሚሽን ያቀረቡት ማስታወሻ፣) አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ (2002 ዓ.ም.)
11. ዘውዴ ረታ (አምባሳደር) <u>የኤርትራ ጉዳይ 1941-1963</u> ዓ.ም አዲስ አበባ (1990)
12. መለስ ዜናዊ <u>የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት</u>? (ግምገማ)፤ (1979 ዓ.ም),

13. እምባሉ ገብረዝጊ (ኮሎኔል) የኤርትራ መዘዝ አዲስ አበባ ጥር 11 ቀን (2002) ዓ.ም

14. ተፈራ ኃይለ ሥላሴ (አምባሳደር) ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ 1970-1996፤ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ አዲስ አበባ፤ (1999 ዓ.ም).

15. ታደሰ ገድሌ ከአስደናቂዎቹ የነገሥታትና የመሳፍንት ደብዳቤዎች ፤ (ከዲፕሎማሲና ከወዳጅነት አንጻር) አዲስ አበባ (2002 ዓ.ም)

16. ሸህ ጀማለዲን ኢብራሂም ኸሊል ኡሻሚና በልጃቸው ሃሺም ጀማለዲን ኢብራሂም ኡሻሚ (ዶ/ር) (የተጻፈ) የአፍር/ ደናኪል ታሪክና መረጃ አርኪ ምንጭ፤ አዲስ አበባ (2000) ዓ.ም

17.[1] መስፍን ወልደ ማርያም ፕሮፌሰር ፤የክህደት ቀልቁለት አዲስ አበባ (2003) ዓ.ም

18. ተክለጻዲቅ መኩሪያ፤አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት፤ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት አ.አ (1981) ዓ.ም

19. ታደሰ ገድሌ ከአስደናቂዎቹ የነገሥታትና የመሳፍንት ደብዳቤዎች ፤(ከዲፕሎማሲና ከወዳጅነት አንጻር) አዲስ አበባ (2002) ዓ.ም

20. ተወልደ ትኩእ ዶ/ር ፤የኢትዮጵያ አንድነትና ኢጣልያ፤አዲስ አበባ (ሚያዝያ1990) ዓ.ም

21. ኢትዮጵያ ጠረፍዋና የባህር ኃይሏ አዲስ አበባ 2000 ዓ.ም.



## 2. ጋዜጦችና መጽሄቶችና ውይይቶች

1. አዲስ ነገር፤
2. ህብረት ጋዜጣ ፤ሐምሌ 9 ቀን 1993 ዓ.ም
3. አትኩሮት ፤ጥቅምት 14 ቀን 1993 ዓ.ም
4. ክብሪት ፤የካቲት 7 ቀን 1994
5. ትኩሳት፤ የካቲት 27 ቀን 1994 ዓ.ም
6. ጦቢያ፤ የካቲት፤ 14ቀን 1994 ዓ.ም
7. አዲስ አድማስ፤ ሚያዝያ 12 ቀን 1994
8. ኔሽን ፤ጥቅምት 28 ቀን 1996 ዓ.ም
9. ሪፖርተር ፤ ሚያዝያ 2 ቀን 2003
10. አዲስ አድማስ ፤ሚያዝያ 29 ቀን 2003 ዓ.ም
11. አውራምባ ታይምስ፤ሚያዝያ 1 ቀን 2003 ዓ.ም
12. ኢትዮጵ፤ ጥቅምት 18 ቀን 1996 ዓ.ም
13.[1] አውራምባ ታይምስ ፤ሚያዝያ 15/2003 ዓ.ም.
14. ሪፖርተር ፤የካቲት 24ቀን 2002 ዓ.ም.
15. ጦቢያ መጽሔት፤ጥር 6 ቀን 1993 ዓ.ም
16. ምኒልክ፤ ሐምሌ 1992 ዓ.ም
17. አባይ ሚድያ፤ ሰኔ 11ቀን 2000 ዓ.ም
18. አቶ መለስ ዜናዊ አ.አ በጁን 20 ቀን 2000 ዓ.ም ከአሜሪካን ድምጽ ሬድዮ ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ
19. ብርጋዴር ጀኔራል ተሰፋዬ ሃብተ ማርያም የአብዮታዊት ወደር የሌለው ጀግና ጋር ግንቦት 5 ቀን 2003 የተደረገ ውይይት

### 3. Bibliography


1. Abebe T. Kahsay, "Ethiopia's Sovereign Right of Access to the Sea Under International Law", A Thesis, University of Georgia, Athens, Georgia (2007) (unpublished).
2. Aklog Birara, Ph.D Endemic Poverty that Globalization Can't Tackle But Ethiopians Can, Signature Printing (2010).
3. Andargachew Tiruneh, The Ethiopian Revolution 1974-1987 A Transformation From an Aristocratic to a Totalitarian Autocracy. Press Syndicate of the University of Cambridge, Cambridge (1993).
4. "Arbitral award in the Dispute Concerning certain Boundary Pillars between Arab Republic of Egypt and the State of Israel", 80 ilr 226 (27ilm 142 (1421) (1998).
5. Belai Abbai, The Ethiopian Regime Cedes National Territories, Washington D.C (2001).
6. Cassese, Antonio, International Law, 2nd edition, Oxford University Press, (2005).
7. Cassese Antonio, "Self Determination of Peoples: A Legal Reappraisal," University Press,1955 cited in Moges Solomon.
8. Concerning the Case of the Land and Maritime Boundary between Cameroon and Nigeria (Cameroon V. Nigeria and Equatorial Guinea Intervening), 10 October 2000 Judgment.
9. Djibouti Port may Divorce DPWorld, Capital, June 15, 2011.
10. Eritrea-Ethiopia Boundary Commission Decision Regarding Delimitation of the Border between the State of Eritrea and the Federal Democratic Republic of Ethiopia, The Hague 13th day of April (2002) (unpublished).





11. Faye, M. Macarthur, J. Sachs, J. Show. T., "The Challenges Facing Land Locked Developing Countries, "Journal of Human Development, (1) (2004).
12. Gebru Tareke, The Ethiopian Revolution: War in the Horn of Africa, Yale University Press, New Haven & London, (2009).
13. Handbook on the Delimitation of Maritime Boundaries, Division for Ocean Affairs and the Law of the Sea, Office of the Legal Affairs, United Nations, Newark, (2003).
14. International Court of Justice, Article 31, para. 2 and 3.
15. International Court of Justice, General List 94 ), International Court of Justice, the Case Concerning the Land and Maritime Boundary between Cameroon and Nigeria, (Cameroon V Nigeria Equatorial Guinea intervening, (10 October 2002).
16. Jefferson, T. Opinion on the French Treaties (Qpr.28,1793) in Merril P. D. Peterson, ed., The Political Writings of Thomas Jefferson,113-114 (Thomas Jefferson Memorial Foundation,(1993).
17. Minase Haile, "Legality of Secession: The Case of Eritrea," 8 Emory INt'l Law Review, 479,(1994).
18. Moges Solomon, Outlet to the Sea and the Ethiopia's Claim over the Port of Assab," LL.M. Thesis, Addis Ababa University Law School, Thesis (Unpublished), (2000).
19. Pankhurst "Ethiopia and The Red Sea and The Gulf of Aden Forts in the Nineteenth Century Ethiopia, The Observer, vol.8 no.1 (1964).
20. Pankhurst, Richard, "Images of Ethiopia over the Centuries, Capital, Sunday October 31, 2010.
21. Pankhurst, Richard, An Introduction to the Economic History of Ethiopia: From Early Times to 1800 (1961).
22. Petrides, Pierre, The Boundary Question Between Ethiopia and Somalia: A Legal and Diplomatic Survey, (1983).

23. Report of the United Nations Commission For Eritrea, General Assembly, Official Records: Fifth Session Supplement No. 8 (A/1285).
24. Rubenson,S King of Kings: Tewodros of Ethiopia, London (1966)
25. Schoff ed. W.H The Periplus of the Erythrean Sea,1912 cited in Moges Solomon "Outlet to the Sea and Ethiopia's claim over the port of Assab," Thesis, Addis Ababa University Faculty of Law, (May 2003) (Unpublished).
26. Shaw, Malcolm, International Law, Cambridge University Press, 5th edition, (2003).
27. Shumet Sishagne, Unionists and Separatists: The Vagaries of Ethiopian Eritrean Relations 1940-1991 Hollywood, CA 900078,1982.
28. Tekeste Negash. , Brothers at War: Making sense of Eritrean-Ethiopian War (Eastern African Studies), (April 1, 2001).
29. Tekola W.Hagos, "Aklilu Habtewold: In the Footsteps of a Great International Law Jurist Disqualification of Lauterpacht: Nullification of Algiers Agreement, and Rejection of the Decision of the Border Commission." Phineaus Claire Washington DC. October 30, 2003,
30. Tesfation Medhane, Dynamics of the National Question, B.R gunner, Amsterdam(1986)
31. United Nations Resolutions, No. 1028 (x1) 2002 and 2003
32. Uprety, Kishor "Right of Access to the Sea of Land Locked States: Retrospect and Prospect for Development". Journal of international Legal Studies, 21(1995).
33. U.N Charter Article 10.
34. Vienna Convention on the Law of the Sea, Article 25 (1982)
35. Vallily, Panel "Assab, The Life line that could Feed Ethiopia, Report from Assab", (May 1, 2000).



1. "የምጽዋ በር የአባቶቼ የነገሥታት ኢትዮጵያን ነው፡፡ አሁንም እንበለ በር ቤተ መንግሥት አይቀናምና በእርስዎ ወኪልነትና እርዳታ የምጽዋን በር እንድይዝ ያድርጉልኝ ብዬ እለምናለሁ"፡፡
   **አፄ ዮሐንስ 4ኛ ለንግሥት ቪክቶርያ ከጻፉት ዳብዳቤ፡፡**
**ታደለ ገድሌ ጽጋዬ፤ ከአስደናቂዎቹ የነገሥታትና የመሳፍንት ደብዳቤዎች፤ ከዲፕሎማሲና ከወዳጅነት አንጻር አዲስ አበባ (2002) ዓ.ም ገጽ 61.**

2. "የዘይላን በር ነገር በሚቻልዎ ነገር ሁሉ ተጣጥረው በእኔ እጅ ቢሆን እንኳን በሐረርጌና፣ በአሩሲ፣ በከንባታ፣በጅማ፣ በከፋ ያለን ንግድ ሁሉ በዘይላ አደርገው ነበር፡፡ ስለዚህ ጠንቅቀው ቢያስለቅቁልኝ እወዳለሁ፡፡ ይህም ማለቴ ለእርስዎ እንዳይቸግርዎ ባውቀው የኢትዮጵያ ልጆች በንጉሥ ኡምቤርቶ ብርታት የዘይላ በር እጃችን ተመልሶ ገባ እንዲሉ ስምዎ በነገሥታት ታሪካችን ይተከላል፡፡"
   **ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለንጉሥ ኡምቤርቶ እ.አ.አ በ1876 ዓ.ም ከጻፉት ደብዳቤ**
**ታደሰ ገድሌ ጸጋዬ ዝኒ ከማሁ ገጽ 71.**

3. "ለብዙ ዓመታት የሁለቱን ወንድማማች ሕዝቦች ለያይቶ የኖረውን የመከራ ምዕራፍ በዛሬው ቀን እንዘጋለን"
   **ከቀዳማዊ አጼ ኃ.ሥላሴ ንግግር**
**ዘወዴ ረታ(አምባሳደር) የኤርትረ ጉዳይ እ.አ.አ 1941-1963፤ 1990 ዓ.ም አዲስ አበባ**

4. በዚህ በቀይ ባህር ወደብ እና ጠረፍ ላይ ሆነን ካሌብን ጥንታዊ የባህር ኃይላችንና የንግድ መርከቦቻችን በቀይ ባህር የነበረን ገናናነት አዱሊስን እና መጠራን፣ ዳህላክን፣ እና ናኩራን በአጠቃላይ የታሪክ ኩራታችንን አሉላን ጭምር እንመለከታለን ቀይ ባህርና [የባህር] በሮቻችን የታሪካችን ልዩ አሻራዎች ናቸው፡፡
   **ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አዲስ ዘመን ጥር 22 ቀን 1969 ዓ.ም**

5. እነዚህ ስህተቶች /ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ማድረግ/ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተመረጠ ዲሞክራሲዊ ህጋዊ መንግስት ሳይቋቋም የሽግግር ወቅት የኤርትራ ሪፈረንደም እንዲካሄድ ማመቻቸት ነበር፡፡ ኤርትራ ነፃነቷን ስታውጅ ኢትዮጵያ የአሰብን ጉዳይ ጨምሮ በሌሎች ጉዳዮችም የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጎት፤ ጥቅምና መብቶች የሚያስከብር አግባብነት ያለው ስምምነት እንዲፈረም ያለማድረግ ነው፡፡
   **ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ (የቀድሞው የኢፌድሪ ፐሬዘዳንት)**

6. "ይህ አሰብን እንይዛለን እንወርራለን የሚል አካሄድ ከዚያው ከዘውዳዊ ትምክህታዊ አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ይህ አስተሳሰብ የተጠናወታቸው ሰዎች ከዘመን ግሎባላይዜሽን ጋር አብረው ሊሄዱ ያልቻሉ ከድንጋይ ዘመን አስተሳሰብ ያልተላቀቁ ናቸው፡፡ አሰብን ካልያዝን እያሉ ይፎክራሉ፤ተግባራዊ ለማድርግ በአሰብ ላይ ወረራ እስካልተፈጸመ ድረስ እርምጃ ልንወስድባቸው አንችልም"
   **አቶ መለስ ዜናዊ**
**ከአስማሪና ድረ ገጽ ባለቤት ከአቶ ተሰፋ ልደት መሃረነ ጋር አቶ መለስ ዜናዊ ያደረጉት ቃል ምልልስ 2000 ዓ.ም.**

ዋጋ 50.60

Jacket design by Araya Getachew